# ለማማከር አገልግሎት የሚሆን

# ፈጣን የመጽሐፍ ቅዱስ ማጣቀሻ

ጆን ጂ. ክሩዝ

BIBLE BASED BOOKS
SIM PUBLISHING

መጽሐፍ ቅዱስን መሠረት ያደረጉ መጻሕፍት
የኤስ ኣይ ኤም ሥነ ጽሑፍ

Copyright © 1988, 1994, 2000 by John G. Kruis.
Originally published in English by Baker Books,
a division of Baker Book House Company,
P.O.Box 6287, Grand Rapids, MI 49516-6287, USA.
All rights reserved.

የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች የተወሰዱት መጽሐፍ ቅዱስ አዲሱ መደበኛ ትርጉም© 2001 በኢንተርናሽናል መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር ታተመ፣ 1993 ዓ.ም የቅጂ መብት ከሚለው የአማርኛ መጽሐፍ ቅዱስ ነው።

ትርጉም:- ሰላመአብ አሰፋ
እርማት:- ዮዲት ኃይሉ
አርትዖት:- ዘነበ ገብረሐና
የኮምፒውተር ለቀማና የገጽ አቀማመጥ:- ዓለምፀሐይ እውነቱ

አሳታሚና አከፋፋይ:-
የኤስ አይ ኤም ሥነ ጽሑፍ ክፍል
የፖ.ሣ. ቁጥር 127፣ አዲስ አበባ
የስልክ ቁጥር 011-349-3252፣ 011-551-2973
ፋክስ 251-1-11 551-1242
ኢ-ሜይል:- simmedia@ethionet.et

# መግቢያ

## ይህ መጽሐፍ ለምን አስፈለገ?

### ለመጽሐፍ ቅዱሳዊ ምክር።

«ቅዱሳት መጻሕፍት ሁሉ የእግዚአብሔር መንፈስ ያለባቸው ናቸው፤ ለማስተማር፣ ለመገሠጽ፣ ለማቅናት በጽድቅም መንገድ ለመምከር ይጠቅማሉ፤ ይኸውም የእግዚአብሔር ሰው ለመልካም ሥራ ሁሉ ብቁ ሆኖ እንዲገኝ ነው።» (2ኛ ጢሞ. 3:16-17)። «የእግዚአብሔር ቃል ሕያውና የሚሠራ ነውና፤ በሁለት በኩል ስለት ካለው ሰይፍ ሁሉ ይልቅ ስለታም ነው፤ ነፍስንና መንፈስን፣ ጅማትንና ቅልጥምን እስኪለያይ ድረስ ዘልቆ ይወጋል፤ የልብንም አሳብና ምኞት ይመረምራል።» (ዕብ. 4:12)።

የእግዚአብሐርን ሥራ ስትሠራ፣ ሁል ጊዜ የመጀመሪያው አማካሪ መንፈስ ቅዱስ ነው፣ እርሱም በኃይልና በሉዓላዊነት፣ በራሱ ቃል አማካኝነት ይሠራል። በቃሉ አማካኝነት ሰዎችን ስለ ኃጢአት ይወቅሳል፣ እንዲሁም አዳኝ ወደ ሆነው ወደ ኢየሱስ ክርስቶስ እውቀት ያመጣቸዋል። ሰዎች እግዚአብሔርንና ባልንጀራቸውን እንደ ራሳቸው አድርገው እንዲወድዱ፣ እንዲሁም ለአዳኝ ጸጋው ምላሽን በመስጠት የእምነትንና የመታዘዝን ኑሮ እንዲኖሩ ለማድረግ የሚያስተምራቸው በቃሉ አማካኝነት ነው። በቅዱሳት መጻሕፍት አማካኝነት መንፈስ ቅዱስ ያጽናናል፣ ይገሥጻል፣ ያቀናል፣ በጽድቅ መንገድም ያሠለጥናል። በዚህ መንገድ በሁሉም ዘመናት የነበሩና በተለያዩ የሕይወት እርምጃዎች ውስጥ ያሳለፉ ሰዎች ታግዘዋል፤ ሁሉም ዓይነት የግል፣ የጋብቻና የቤተሰብ ችግሮች ተፈትተዋል፤ እግዚአብሔርም ከብሯል።

ስለዚህ፣ በቃሉ ሥር ሰድደህ መሠልጠንህና ለመልካም

ሥራዎች ሁሉ መዘጋጀትህ እጅግ በጣም አስፈላጊ ነው::

### ለግል፣ ለጋብቻና ለቤተሰብ ፍላጐቶች

ይህ ለማማከር አገልግሎት የሚውል ፈጣን የመጽሐፍ ቅዱስ ማጣቀሻ ለመጀመሪያ ጊዜ በእንግሊዝኛ ቋንቋ የታተመው (እ.ኤ.አ) በመጋቢት ወር 1988 ነው:: ወደ 3ኛው እትም ሲያመራ በዓለም አቀፍ ደረጃ 175,000 የእንግሊዝኛ ቅጂዎች ተሸጠዋል:: በተጨባጭ እንደታየውም፣ ከማማከር አገልግሎት ውጪም ጥቅም ላይ ውሏል:: ብዙ ሰዎች ይህን መጽሐፍ ለግል፣ ለጋብቻና ለቤተሰብ ፍላጐቶቻቸው ማሟያ፣ እንዲሁም በቤት ውስጥ ያሉትን ያለመስማማቶች ለመፍታት ጉዳይ አውለዋቸዋል:: ሌሎች ደግሞ ለግልና ለቤተሰብ የጥሞና ጊዜ እንደ መምሪያ መጽሐፍ ተጠቅመውበታል::

### የዚህ መጽሐፍ ልዩ ባሕርይ (መለያ)

ይህ ለማማከር አገልግሎት የሚውለው ፈጣን የመጽሐፍ ቅዱስ ማጣቀሻ የተዘጋጀው እግዚአብሔር ሰዎች በሙሉ መጽሐፍ ቅዱስን በማማከር አገልግሎት ውስጥ ይበልጥ ውጤታማ በሆነ መንገድ እንዲጠቀሙበት ለማድረግ ነው:: መጽሐፉ ከሌሎች የሚለይባቸው በርካታ ባሕርያት አሉት:: የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎችና መጻሕፍቶች ከርእሰ ጉዳይ በታች ተዘርዝረዋል:: እነዚህ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች የተደራጁት አንድ ጊዜ ብቻ በመቃኘት በተጠቀሰው ርእሰ ጉዳይ ሥር ያሉትን ጥቅሶች ፍሬ አሳብና አስፈላጊነት ማየት እንድትችሉ ተደርገው ነው:: አብዛኛውን ጊዜ የመጽሐፍ ቅዱስ ቁጥሮችን ከሙሉ ክፍላቸው ጋር በአፋጣኝ ማግኘት እንድትችሉ ተደርገው ቀርበዋል:: ረጃጅም ክፍሎች

## ይህ መጽሐፍ የተዘጋጀው . . .

ለግል ጥቅማችሁና በማማከር ወቅት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶችን በውጤታማ መንገድ እንድትጠቀሙባቸው ለመርዳት ነው::

«ቅዱሳት መጻሕፍት ሁሉ የእግዚአብሔር መንፈስ ያለባቸው ናቸው፤ ለማስተማር፣ ለመገሠጽ፣ በማቅናት በጽድቅም መንገድ ለመምከር ይጠቅማሉ፤ ይኸውም የእግዚአብሔር ሰው ለመልካም ሥራ ሁሉ ብቁ ሆኖ እንዲገኝ ነው።»

(2ኛ ጢሞ. 3:16-17)

# የርእስ ጉዳይ ማውጫ


| | |
|---|---|
| ለራስ መሳሳት | 211 |
| ሌሎችን መውደድና ማገልገል | 118 |
| ሌሎችን ይቅር ማለት | 99 |
| ልጆች | 35 |
| ልጆችን ማሠልጠን | 220 |
| ሐሜት | 51 |
| ሐሰተኛ ነቢያት፤ | |
| ሐሰተኛ አስተማሪዎች | 83 |
| መለወጥ (እግዚአብሔርን ለማስደሰት) | 142 |
| መስጠት | 104 |
| መታመን | 224 |
| መታዘዝ | 136 |
| መከራ | 15 |
| መጨፍገግ/ድብርት | 74 |
| መጽናናት | 46 |
| ማመካኘት | 34 |
| ማስጠንቀቂያዎች | 232 |
| ምሬት | 31 |
| ምሳሌነት (መልካም ወይም ክፉ) | 80 |
| ምኞት | 57 |
| ሞት | 64 |
| ሥራ | 239 |
| ራስን መግዛት፤ | |
| ራስን ማሠልጠን | 208 |
| ሰላም | 148 |
| ሰላም ጠባቂዎች | 151 |
| ሰውን ወደ ክርስቶስ መምራት | 192 |
| ሴሰኝነት | 127 |
| ስንፍና | 239 |
| ስደት | 158 |
| ስጋት | 243 |
| ቀዳሚ ነገሮች | 57 |
| ቁጣ | 26 |
| ቅሬታ | 31 |
| የቅዱሳን ኅብረት | 37 |
| ቅጣት | 15 |
| የባልና ሚስት ግንኙነቶች | 129 |
| ቤተ ክርስቲያን | 37 |
| የቤተክርስቲያን ተግሣጽ | 43 |
| ተስፋ | 112 |
| ተግሣጽ | 15 |
| ተግባቦት | 51 |
| ትእዛዛት | 136 |
| ኃጢአትን ማሸነፍ | 142 |
| የኃጢአቶች ይቅርታ | 90 |
| ኀሊና | 55 |
| ንስሐ | 186 |
| የንስሐና የመታዘዝ ጥሪዎች | 232 |
| ንዴት | 26 |
| አመንዝራነት | 11 |
| አስታራቂዎች | 151 |
| አስካሪ መጠጥ | 23 |
| እዘኔታ | 211 |
| አደንዛዥ ዕጽ | 23 |
| ኢየሱስን መምሰል | 114 |
| እረፍት | 148 |
| የወሲብ ሕይወት | 213 |
| ዘማዊነት | 214 |
| የዘላለም ሕይወት | 64 |
| ደኅንነት | 192 |
| የደኅንነት ማረጋገጫ | 29 |
| ድብልቅ ጋብቻ | 133 |

| | | | |
|---|---|---|---|
| እርካታ | 57 | ጋብቻ | 129 |
| እድገታዊ ቅድስና | 170 | ግለኝነት | 206 |
| እግዚአብሔርን መውደድ | 125 | ግብረ ሰዶማዊነት | 109 |
| የእግዚአብሔር መጋቢነት | 176 | ጓደኝነት | 102 |
| እግዚአብሔርን መጠበቅ | 166 | ክፉን ማሸነፍ | 139 |
| እግዚአብሔርን ማመን | 224 | ጥላቻ | 31 |
| ክፉ ምኞቶች | 127 | ጭንቀት | 243 |
| ወጣትነት | 245 | ጸሎት | 166 |
| ውሳኔ መስጠት | 72 | ፈተና | 217 |
| ውሸት | 51 | ፍርሃት | 88 |
| | | ፍቺ | 77 |


# ደኅንነት

## ሰውን ወደ ክርስቶስ መምራት

I. ከክርስቶስ ውጪ እኛ ረዳት የለሽና ኃጢአተኞች ነን::
- ሀ. ሁላችንም ኃጢአተኞች ነን::
- ለ. ሁላችንም በመንፈሳዊ እሥራት ውስጥ እንገኛለን::
- ሐ. ከእግዚአብሔር ተለይተናል::
- መ. የኃጢአት እውቀት የሚመጣው የእግዚአብሔርን ሕግ ከማወቅ ነው::
- ሠ. እግዚአብሔር፣ በጽድቁ፣ ኃጢአተኞችን ይቀጣል::
- ረ. በየትኛውም መንገድ ራሳችንን ማዳን አንችልም::

II. ኢየሱስ በእምነትና በጸጋ አማካኝነት ያድነናል::
- ሀ. ኢየሱስ ስለ ኃጢአተኞች ተሠቃየ እንዲሁም ሞተ::
- ለ. በእምነት በጸጋ አማካኝነት የዳኑ ሰዎች ምሳሌዎች::

III. እንደ እናንተ እንደ እኔ ያሉትን ኃጢአተኞች ጌታ ይጠራል::

IV. እኛ የዳንነው በደስታ ጌታን እንታዘዘውና እናገለግለው ዘንድ ነው::

ሲዘረዘሩ፣ የተጠቀሱት ቁልፍ የሆኑት ክፍሎች ብቻ ናቸው::

የመጽሐፉን ጠቀሜታ ከፍ ለማድረግ በእያንዳንዱ ርእስ ጉዳዮች ሥር ያሉ መግቢያዎች አንድን ሰው ለማማከር በምትዘጋጁበት ጊዜ በጣታችሁ ጫፍ በመታገዝ አግባብነት ያላቸውን ጥቅሶች በቀላሉ እንድታገኙ ቁጥር ተሰጥቷቸዋል:: ለምሳሌ አንድን ሰው ወደ ኃጢአት ይቅርታ ወይም ማረጋገጫ ለመምራት ስትፈልግ ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ዓይነት ነገሮች በማስታወሻ ደብተርህ ላይ ልታሰፍር ትችላለህ:-

የኃጢአቶች ይቅርታ - ገጽ 90

1. አማኞች ልክ እንደ በረዶ ነጭ ተደርገዋል (ኢሳ. 1:18)::

6. እግዚአብሔር የተሰበረውን መንፈስና የተዋረደውን ልብ አይንቅም (መዝ. 51:17)::

9. እግዚአብሔር ኃጢአተኞች እንዲፈልጉት ይጠይቃቸዋል፣ ብሎም ከተመለሱ ይቅር እንደሚላቸው ተስፋ ይሰጣቸዋል (ኢሳ. 55:6-7)::

11. ኢየሱስ የተጸጸተችውን ሴት ይቅር አላት (ሉቃ. 7:36-50)::

26. እግዚአብሔር በክርስቶስ ደም አማካኝነት ኃጢአታችንን ሁሉ ይቅር በማለትና እኛን በመምረጥ ጸጋውን ሰጠን (ኤፌ. 1:3-10)::

እነዚህ ጉዳዮች የእያንዳንዱን ተመካሪ ችግር ያማከሉ ቤት ውስጥ የሚሠሩት ጥናቶችን ለማዘጋጀት ያግዙዋችኋል::

ጸሎቴ፣ ይህ መጽሐፍ ብዙዎች የማማከር አገልግሎትን ሲሰጡ መጽሐፍ ቅዱስን ይበልጥ ውጤታማ በሆነ መንገድ

ለመጠቀም ያውም ለብዙዎች ለመጽናናታቸው፣ ለደስታቸው፣ ለሰላማቸውና ለዘላለማዊ ደኅንነታቸው፣ ከዚያም በላይ ለእግዚአብሔር ክብርን በሚያመጣ መንገድ እንዲጠቀሙ እንዲያግዛቸው ነው::



# አመንዝራነት

አንድ ሰው በአመንዝራነት ባህሕርይ ቢቀጥል፣ በተጨማሪ ዘማዊነት የሚለውን በገጽ 214፣ ማስጠንቀቂያዎች በገጽ 232፣ እና መታዘዝ በገጽ 136 ላይ ተመልከቱ:: አንድ ሰው ከኃጢአቱ ንስሐ ቢገባ፣ ገጽ 90 ላይ የሚገኘውን የኃጢአቶች ይቅርታን እና ሰላምን በገጽ 148 ላይ ተመልከቱ::

**1. አመንዝራነት ከልብ ይመነጫል::**

ማቴ. 15:19 ክፉ አሳብ፣ ነፍስ መግደል፣ ማመንዘር፣ ዝሙት፣ መስረቅ፣ በሐሰት መመስከርና ስም ማጉደፍ ከልብ ይመነጫል::

**2. አመንዝራዎች ወደ መንግሥተ ሰማይ አይገቡም::**

1ኛ ቆሮ. 6:9-10:: «ዓመፀኞች የእግዚአብሔርን መንግሥት እንደማይወርሱ አታውቁምን? በዚህ ነገር አትታለሉ፤ ሴሰኞች፣ ጣዖት አምላኪዎች፣ አመንዝሮች፣ ወንደቃዎች፣ ግብረ ሰዶማውያን፣ ወይም ሌቦች፣ ስግብግቦች፣ ሰካራሞች፣ ተሳዳቢዎችና ቀማኞች የእግዚአብሔርን መንግሥት አይወርሱም::»

**3. እግዚአብሔር በአመንዝራዎች ላይ ይፈርዳል::**

ዕብ. 13:4:: «ጋብቻ በሁሉም ዘንድ ይከበር፣ መኝታውም ንጹሕ ይሁን፤ ምክንያቱም እግዚአብሔር በአመንዝሮችና በሴሰኞች ሁሉ ላይ ይፈርዳል::»

**4. አመንዝራነት ሊወገድ ይችላል::**

ምሳ. 4:23:: «ከሁሉም በላይ ልብህን ጠብቅ፤ የሕይወት ምንጭ ነውና::» ምሳ. 4:13-27 (ከክፋት መንገድ ራቅ::)

ምሳ. 6:27-28 (በእሳት አትጫወት::) ለመሆኑ ልብሱ ሳይቃጠል፣ በጉያው እሳት መያዝ የሚችል ሰው አለን? አንድ ሰው እግሮቹ ሳይቃጠሉ፣ በፍም ላይ መሄድ ይችላልን?

**5. ከአመንዝራነት ሽሽ::**

ምሳ. 6:20-35

**6. የአመንዝራ ሴት ወጥመድ ወደ ችግር ይመራል::**

ምሳ. 7:1-27::

**7. የአመንዝራ ሴት ወጥመድ እንደ ጥልቅ ጉድጓድ ነው::**

ምሳ. 22:14:: «የአመንዝራ ሴት አፍ ጥልቅ ጉድጓድ ነው፤ እግዚአብሔር የተቈጣውም ይገባበታል::»

**8. ዳዊት ነበልባሉን አነሣሣ::**

2ኛ ሳሙ. 11:2-3:: «አንድ ቀን ማታ፣ ዳዊት ከዐልጋው ተነሥቶ በቤተ መንግሥቱ ሰገነት ወዲያና ወዲህ ይመላለስ ነበር፤ ከሰገነቱ ላይ እንዳለም፣ አንዲት ሴት ገላዋን ስትታጠብ አየ፤ ሴቲቱም እጅግ በጣም ውብ ነበረች:: ዳዊትም ሰው ልኮ ስለ ሴቲቱ አጠያየቀ::»

**9. ዳዊት የአመንዝራነት ኃጢአቱን ከመናዘዙ በፊት በጨፈገገ ስሜት ውስጥ ነበር::**

መዝ. 32: 3-5::

**10. ናታን ዳዊት ከአመንዝራነት ኃጢአት ንስሐ እንዲገባ ጥሪ አቀረበለት::**

2ኛ ሳሙ. 12:1-14:: ዳዊት ከቤርሳቤህ ጋር ካመነዘረ በኋላ ነቢዩ ናታን በምሳሌ ተናገረው::)

**11. ዳዊት የአመንዝራነት ኃጢአቱን ተናዘዘ፣ እግዚአብሔርም በጸጋ ይቅር አለው::**

መዝ. 32፤ መዝ. 51:: ዳዊት እግዚአብሔር ይቅር እንዲለው ተማጸነ፣ ይቅር ከተባለም በኋላ ደስታውን ገለጸ::)

**12. እግዚአብሔር የምንዝርናን ኃጢአት ይቅር ይላል፣ ኃጢአተኛ ውንም ከዚያ ነፃ ያወጣዋል::**

1ኛ ቆሮ. 6:11:: «ከእናንተ አንዳንዶቻችሁ እንደዚህ (አመንዝራ) ነበራችሁ፤ አሁን ግን በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ስምና፣ በአምላካችን መንፈስ ታጥባችኋል፤ ተቀድሳችኋል፤ ጸድቃችኋል::»

**13. ሴትን በምኞት ዓይን መመልከት አመንዝራነት ነው፤ መንፈሳዊ ቀዶ ጥገና ያሻዋል::**



ማቴ. 5:27-30:: «አታመንዝር እንደ ተባለ ሰምታችኋል:: እኔ ግን እላችኋለሁ፤ ሴትን በምኞት ዓይን የተመለከተ ሁሉ በልቡ ከእርሷ ጋር አመንዝሮአል:: ቀኝ ዓይንህ የኀጢአት ሰበብ ቢሆንብህ፣ አውጥተህ ወዲያ ጣለው፤ ሰውነትህ በሙሉ ወደ ገሃነም ከሚጣል ከሰውነትህ አንዱን ክፍል ብታጣ ይሻልሃል:: ቀኝ እጅህ የኀጢአት ሰበብ ቢሆንብህ ቈርጠህ ወዲያ ጣለው፤ ሰውነትህ በሙሉ ወደ ገሃነም ከሚጣል ከሰውነትህ አንዱን ክፍል ብታጣ ይሻልሃል::»

**14. ከአሳሳች ሴት ተጠንቀቅ::**

ምሳ. 23:26-28:: «ልጄ ሆይ፤ ልብህን ስጠኝ፤ ዐይኖችህም ከመንገዴ አይውጡ፤ ዘልዛላ ሚስት ጠባብ ጉድጓድ፣ አመንዝራም ሴት ዐዘቅት ናትና፤ እንደ ወንበዴ ታደባለች፤ በሰዎችም መካከል ወስላቶችን ታበዛለች::»

**15. የስርቆት ውኃ ይጣፍጣል፣ ነገር ግን**

ምሳ. 9:17-18:: «የስርቆት ውኃ ይጣፍጣል፤ ተሸሽገው የበሉት ምግብ ይጥማል:: እነርሱ ግን ሙታን በዚያ እንዳሉ፣ ተጋባዦቿም በሲኦል ጥልቀት ውስጥ እንደ ሆኑ አያውቁም::»

**16. ሰባተኛውን ትእዛዝ ጠብቅ::**

ዘፀ. 20:14:: አታመንዝር::

**17. አላግባብ የተፈታችን ሴት የሚያገባ ሰው ያመነዝራል::**

ማቴ. 5:31-32:: 'ሚስቱን የሚፈታ ሁሉ የፍቺ ወረቀት መስጠት አለበት' እንደተባለ ሰምታችኋል:: እኔ ግን እላችኋለሁ፤ በላዩ ላይ ስታመነዝር ካላገኛት በስተቀር፣ ሚስቱን የሚፈታ ሁሉ እንድታመነዝር ያደርጋታል፤ በዚህ ሁኔታ የተፈታችውን ሴት ያገባም እንዳመነዘረ ይቆጠራል::»

**18. ሚስቱን ወይም ባሏን ከማመንዘር ውጭ በሆነ በማናቸውም ምክንያት የሚፈታና ሌላ ሚስት (ባል) የሚያገባ ሁሉ ያመነዝራል::**

ማቴ. 19:9:: «እላችኋለሁ፤ በትዳሯ ላይ ዝሙት ፈጽማ እስካልተገኘች ድረስ ሚስቱን ፈትቶ ሌላ ሴት የሚያገባ ሁሉ

**አመንዝራ ይሆናል፤ እርሷንም አመንዝራ ያደርጋታል፣ የተፈታችውንም ሴት የሚያገባ ያመነዝራል::**

**ሮሜ 7:2-3:: አንዲት ያገባች ሴት ከባሏ ጋር በሕግ የታሰረች የምትሆነው እርሱ በሕይወት እስካለ ድረስ ነው፤ ባሏ ቢሞት ግን ከጋብቻ ሕግ ነጻ ትሆናለች:: ነገር ግን ባሏ በሕይወት እያለ ሌላ ሰው ብታገባ አመንዝራ ትባላለች፤ ባሏ ቢሞት ግን ሌላ ሰው ብታገባም እንኳ፣ ከዚህ ሕግ ነጻ ትሆናለች፤ አመንዝራ አትባልም::**

**19. ዮሴፍ፣ በጲጥፋራ ሚስት እንዲያመነዝር በተፈተነ ጊዜ፣ በእግዚአብሔር ላይ ኃጢአት አልሠራም አለ::**

**- ዘፍ. 39:6-20**

**- ዘፍ. 39:9-10::**

**«. . . ታዲያ፣ እኔ ይህን ክፉ ድርጊት ፈጽሜ እንዴት በእግዚአብሔር ፊት ኃጢአት እሠራለሁ?» ምንም እንኳ ዮሴፍን በየቀኑ ብትጐተጐተውም፣ አልሰማትም፤ ከእርሷ ጋር መተኛቱ ይቅርና አብሯትም ለመሆን አልፈቀደም::**



# መከራ፣ ተግሣጽ፣ ቅጣት፣ ፈተና

**በተጨማሪ መጽናናት በገጽ 46፣ ጸሎትን በገጽ 166 እና መታመን በገጽ 224 ላይ ተመልከት::**

**1. ሁሉም መከራ የሚመጣው በተወሰነ ዓይነት የኃጢአት ምክንያት አይደለም:: ብዙ ጊዜ እግዚአብሔር መከራን የሚልከው ለክብሩ ሲል እምነታችንን ለማጥራትና ለማጐልበት ነው::**

**1ኛ ጴጥ. 1:6-7:: «አሁን በብዙ ዐይነት ፈተና ውስጥ ሆናችሁ ለጥቂት ጊዜ መከራን ብትቀበሉም እንኳ በዚህ እጅግ ደስ ይላችኋል:: እነዚህ ነገሮች በእናንተ ላይ የደረሱት፣ በእሳት ተፈትኖ ቢጠራም፣ ጠፊ ከሆነው ወርቅ ይልቅ እጅግ የከበረው እምነታችሁ እውነተኛ መሆኑ እንደተረጋገጠና ኢየሱስ ክርስቶስ በሚገለጥበት ጊዜ ምስጋናን ክብርንና፣ ውዳሴን እንዲያስገኝላችሁ ነው::»**

**ዮሐ. 9:1-3:: በመንገድ ሲያልፍም ከተወለደ ጀምሮ ዐይነ ስውር የሆነው ሰው አየ:: ደቀ መዛሙርቱም፣ «ረቢ፤ ይህ ሰው ዐይነ ስውር ሆኖ እንዲወለድ ኀጢአት የሠራ ማን ነው? እርሱ ራሱ ወይስ ወላጆቹ?» ብለው ጠየቁት:: ኢየሱስም እንዲህ ሲል መለሰ፣ «እርሱ ወይም ወላጆቹ ኀጢአት አልሠሩም፤ ይህ የሆነው ግን የእግዚአብሔር ሥራ በእርሱ ሕይወት እንዲገለጥ ነው::**

**2. የእግዚአብሔር ሰው የሆነው ኢዮብ በከፍተኛ ሁኔታ ተፈትኗል፣ ንብረቱንና ልጆቹንም አጥቷል::**

**ኢዮብ 1:1-22::**

**ኢዮብ 1:1:: «ዖፅ በሚል አገር የሚኖር ኢዮብ የተባለ ሰው ነበረ፤ ይህ ሰው ነቀፋ የሌለበት፣ ቅን፣ እግዚአብሔርን የሚፈራና ከክፋት የራቀ ነበር::»**

**ኢዮብ 1:8:: «እግዚአብሔም ሰይጣንን፣ «አገልጋዬን ኢዮብን ተመለከትኸውን? በምድር ላይ እንደ እርሱ ነቀፋ የሌለበት፣ ቅን፣ እግዚአብሔርን የሚፈራና ከክፋት የራቀ ሰው የለም» አለው::**

**3. ኢዮብ በእግዚአብሔር ላይ አልተቆጣም (ኃጢአትን አላደረገም)::**

ይልቁንም ሁኔታውን በእምነት ተቀበለ፣ እግዚአብሔርንም አመሰከ።

ኢዮብ 1:20-22። ኢዮብም ተነሣ፤ ልብሱን ቀደደ፤ ራሱን ተላጨ፤ በምድርም ላይ ተደፍቶ ሰገደ፤ እንዲህም አለ፤ «ራቍቴን ከእናቴ ማሕፀን ወጣሁ፤ ዕራቍቴንም እሄዳለሁ። እግዚአብሔር ሰጠ፤ እግዚአብሔር ነሣ፤ የእግዚአብሔር ስም ብሩክ ይሁን።» በዚህ ሁሉ፣ ኢዮብ አልበደለም፤ በእግዚአብሔር ላይ ክፉ አልተናገረም።

4. አንዳንድ ጊዜ እግዚአብሔር ትዕግሥትን ሊጨምርልን ፈተና ይሰድድብናል።

ያቆብ 1:2-4። «ወንድሞች ሆይ፣ ልዩ ልዩ መከራ ሲደርስባችሁ እንደ ሙሉ ደስታ ቍጠሩት ምክንያቱም የእምነታችሁ መፈተን ትዕግሥትን እንደሚያስገኝ ታውቃላችሁ። ምንም የማይጐድላችሁ ፍጹማንና ምሉኣን እንድትሆኑ ትዕግሥት ሥራውን ይፈጽም።

5. ዘማሪው ስለ መከራው ያመሰግን ነበር፣ ምክንያቱም የእግዚአብሔርን ሕግ እንዲጠብቅ አድርጐታል።

መዝ. 119:67-68። «እንዲያው ሳይቸግረኝ መንገድ ስቼ ሄድሁ፤ አሁን ግን ቃልህን እጠብቃለሁ። አንተ መልካም ነህ፤ የምታደርገው መልካም ነው፤ እንግዲህ ሥርዐትህን አስተምረኝ።

መዝ. 119:71-72። «ሥርዐትህን እማር ዘንድ፣ በመከራ ውስጥ ማለፌ መልካም ሆነልኝ። ከአእላፋት ብርና ወርቅ ይልቅ፣ ከአፍህ የሚወጣው ሕግ ይሻለኛል።

መዝ. 119:75-76። እግዚአብሔር ሆይ፤ ፍርድህ የጽድቅ ፍርድ፣ ያስጨነቅኸኝም በታማኝነት እንደ ሆነ ዐውቃለሁ። ለአገልጋይህ በገባኸው ቃል መሠረት፣ ምሕረትህ ለመጽናናት ትሁነኝ»

6. እኛ የእግዚአብሔርን ተግሣጽ ማቅለልም ሆነ በተቀጣን ጊዜ ተስፋ መቁረጥ የለብንም።

ዕብ. 12:5-6። «ልጆች እንደመሆናችሁ እንዲህ በማለት የተናገራችሁን ማበረታቻ ቃልም ረስታችኋል፦ «ልጄ ሆይ፤ የጌታን ቅጣት አታቃል፤ በሚገሥጽህም ጊዜ ተስፋ አትቍረጥ፤ ምክንያቱም



ጌታ የሚወደውን ይገሥጻል፤ እንደ ልጅ የሚቀበለውንም ይቀጣል።»

7. እግዚአብሔር ቅድስናን ሊያሳድግ ልጆቹን ይቀጣል።

ዕብ. 12:5-11።

ዕብ. 12:10-11። «አባቶቻችን መልካም መስሎ እደታያቸው ለጥቂት ጊዜ ይቀጡን ነበር፤ እግዚአብሔር ግን የቅድስናው ተካፋዮች እንድንሆን ለእኛ ጥቅም ሲል ይቀጣናል። ቅጣት ሁሉ በወቅቱ የሚያሳዝን እንጂ ደስ የሚያሰኝ አይመስልም፤ በኋላም ግን ለለመዱት ሰዎች የጽድቅና የሰላም ፍሬ ያስገኝላቸዋል።»

8. እግዚአብሔር ጠቃሚ ትምህርት ሊያስተምራቸው ወደ ተስፋይቱ ምድር ባደረጉት ጕዞ ላይ ሕዝቡን ገሠጻቸው እንዲሁም ፈተናቸው።

ዘዳ. 8:2-5። «አምላክህ እግዚአብሔር (ያህዌ ኤሎሂም) ትእዛዞቹን መጠበቅህንና በልብህ ያለውን ለማወቅ፣ ትሑት ሊያደርግህና ሊፈትንህ በእነዚህ አርባ ዓመታት በዚህ ምድረ በዳ ጕዞህ ሁሉ እንዴት እንደ መራህ አስታውስ። ሰው ከእግዚአብሔር (ያህዌ) አፍ በሚወጣው በእያንዳንዱ ቃል እንጂ፣ በእንጀራ ብቻ እንደማይኖር ሊያስተምርህ አስራበህ፤ አንተም ሆንህ አባቶችህ የማታውቁትን መና መገበህ፤ በእነዚህ አርባ ዓመታት ውስጥ ልብስህ አላለቀም፤ እግርህም አላበጠም። ስለዚህ ሰው ልጁን እንደሚቀጣ፣ አምላክህ እግዚአብሔር (ያህዌ ኤሎሂም) አንተን እንደሚቀጣህ በልብህ ዕወቅ።»

9. እግዚአብሔር መራራውን ውኃ ወደ ጣፋጭ በለወጠበት በማራ ፈተናቸው፣ ከዚያም ወዲያው በኤሊም የእርካታን ጊዜ ሰጣቸው።

ዘፀ. 15:22-27።

ዘፀ. 15:25። «ከዚያም ሙሴ ወደ እግዚአብሔር (ያህዌ) ጮኸ፤ እግዚአብሔርም (ያህዌ) አንዲት ዛፍ አሳየው፤ እርሷንም ወደ ውኃው ጣላት፤ ውሃውም ጣፋጭ ሆነ። በዚያም እግዚአብሔር (ያህዌ) ሕግና ሥርዐት አበጀላቸው። በዚያም ሥፍራ ፈተናቸው።

ዘፀ. 15:27። ከዚያም ዐሥራ ሁለት ምንጮችና ሰባ የዘንባባ

ዛፎች ወዳሉት ወደ ኤሊም መጡ፤ እነርሱም በውኃው አጠገብ በዚያ ሰፈሩ።»

10. ለብ ላለችው ቤተ ክርስቲያን ኢየሱስ የሚወዳቸውን ሁሉ እንደሚገሥጻቸውና እንደሚቀጣቸው ተናገረ።

ራእይ 3:14-22። (ለሎዶቂያ ቤተ ክርስቲያን የተላከ ደብዳቤ)

ራእይ 3:19-20። «እኔም የምወዳቸውን እገሥጻለሁ፤ እቀጣለሁም። ስለዚህ ትጋ፤ ንስሐም ግባ። እነሆ፤ በደጅ ቆሜ አንኳኳለሁ፤ ማንም ድምፄን ሰምቶ በሩን ቢከፍትልኝ ወደ እርሱ ገብቼ ከእርሱ ጋር እበላለሁ፤ እርሱም ከእኔ ጋር ይበላል።

11. ጳውሎስ ለሥጋው መውጊያ ቀጣይነት ያለው መከራ ተሰጠው። እግዚአብሔር የእርሱ ጸጋ ሁልጊዜም እንደሚበቃው ቃል ገባለት።

2ኛ ቆሮ. 12:7-10። ከዚህ ታላቅ መገለጥ የተነሣ እንዳልታበይ የሥጋዬ መውጊያ እርሱም የሚያሠቃየኝ የሰይጣን መልእክተኛ ተሰጠኝ። ይህ ነገር ከእኔ እንዲወገድልኝ ጌታን ሦስት ጊዜ ለመንሁት፤ እርሱ ግን፣ «ጸጋዬ ይበቃሃል፤ ኀይሌ ፍጹም የሚሆነው በድካም ጊዜ ነውና» አለኝ። ስለዚህ የክርስቶስ ኀይል በእኔ ያድር ዘንድ፣ ይበልጥ ደስ እያለኝ በድካሜ እመካለሁ። ስለ ክርስቶስ በድካም፣ በስድብ፣ በመከራ፣ በስደትና በጭንቀት ደስ የምሰኘው ለዚህ ነው፣ ስደክም ያን ጊዜ ብርቱ ነኝና።

12. እግዚአብሔር ለሚወዱት ነገርን ሁሉ ለበጐ ይለውጣል።

ሮሜ 8:28። «እግዚአብሔር፣ ለሚወዱትና እንደ አሳቡ ለተጠሩት፣ ነገር ሁሉ ተያይዞ ለበጐ እንዲሠራ እንደሚያደርግላቸው እናውቃለን።»

13. እግዚአብሔር ልትሸከሙት ከምትችሉት በላይ ፈጽሞ አያሸክማችሁም።

1ኛ ቆሮ. 10:13። በሰዎች ሁሉ ላይ ከደረሰው የተለየ ፈተና አልደረሰባችሁም፤ እግዚአብሔር ታማኝ ነው፤ ስለዚህ ከምትችሉት በላይ እንድትፈተኑ አይተዋችሁም፤ ነገር ግን በምትፈተኑበት ጊዜ



ፈተናውን መታገሥ እንድትችሉ፣ መውጫ መንገዱን ያዘጋጅላችኋል።

14. እግዚአብሔር ነገሮችን ሁሉ በዓላማው መሠረት በጥበብ እንዴት እንደሚያስኬዳቸው የእግዚአብሔርን መንገድ ልናውቅ አንችልም።

ሮሜ. 11:33-36። «የእግዚአብሔር የጥበቡና የዕውቀቱ ባለጠግነት እንዴት ጥልቅ ነው! ፍርዱ አይመረመርም፤ ለመንገዱም ፈለግ የለውም! የጌታን ልብ ያወቀ ማነው? አማካሪውስ የነበረ ማን ነው? እግዚአብሔር መልሶ እንዲሰጠው፣ ለእግዚአብሔር ያበደረ ከቶ ማን ነው? ሁሉም ከእርሱ፣ በእርሱ፣ ለእርሱ ነውና፤ ለእርሱ ለዘላለም ክብር ይሁን፤ አሜን።

15. ንጉሥ ሕዝቅያስ እግዚአብሔርን ፍቅር ስለ ተሞላው ተግሣጽ አመሰገነው።

ኢሳ. 38:15-19።

ኢሳ. 38:15። «እንግዲህ ምን እላለሁ? እርሱ ተናግሮኛል፤ ራሱ ደግሞ ይህን አድርጓል፤ ስለ ነፍሴ ጭንቀት ፣ ዕድሜዬን ሁሉ በትሕትና እሄዳለሁ።»

ኢሳ. 38:17። «እነሆ፤ በሥቃይ የተጨነቅሁት፣ ለጥቅሜ ሆነ፤ ከጥፋት ጕድጓድ፣ በፍቅር ጠበቅኸኝ፤ ኀጢአቴንም ሁሉ፣ ወደ ኋላህ ጣልኸ።

16. ጽናትን በሚፈጥረው መከራችን መደሰት እንችላለን።

ሮሜ 5:3። «በዚህ ብቻ ሳይሆን በመከራችንም ሐሤት እናደርጋለን፤ ምክንያቱም መከራ ትዕግሥትን እንደሚያስገኝ እናውቃለን። ትዕግሥት ጽናትን፣ ጽናት የተፈተነ ባሕርይን፣ የተፈተነ ባሕርይ ተስፋን።»

ያዕ. 1:2-4። «ወንድሞቼ ሆይ፤ ልዩ ልዩ መከራ ሲደርስባችሁ እንደ ሙሉ ደስታ ቊጠሩት፣ ምክንያቱም የእምነታችሁ መፈተን ትዕግሥትን እንደሚያስገኝ ታውቃላችሁ። ምንም የማይጐድላችሁ ፍጹማንና ሙሉአን እንድትሆኑ ትዕግሥት ሥራውን ይፈጽም።»

17. እግዚአብሔር በፈተና ውስጥ የሚጸኑትን ይባርካል::

ያዕ. 1:12:: «በፈተና የሚጸና ሰው የተባረከ ነው፤ ምክንያቱም ፈተናን ሲቋቋም እግዚአብሔር ለሚወዱት የሰጠውን ተስፋ፣ የሕይወትን አክሊል ያገኛል::»

18. ሊገለጥልን ካለው ክብር ጋር አሁን የምንቀበለው መከራ ሊወዳደር እንኳ አይገባውም::

ሮሜ 8:18:: «የአሁኑ ዘመን ሥቃያችን ወደ ፊት ሊገለጥ ካለው ለእኛ ከተጠበቀልን ክብር ጋር ሲነጻጸር ምንም እንዳይደለ እቈጥራለሁ::

19. ጳውሎስ በእግዚአብሔር ላይ መደገፍን ይማር ዘንድ በከባድ መከራ ውስጥ እንዳለፈ ይናገራል::

2ኛ ቆሮ. 1:8-9:: «ወንድሞች ሆይ፤ በእስያ ስለ ደረሰብን መከራ እንድታውቁ እንወዳለን፤ በሕይወት ለመኖር እንኳ ተስፋ እስከምንቈርጥ ድረስ ከዐቅማችን በላይ የሆነ ጽኑ መከራ ደርሶብን ነበር:: በእርግጥም የሞት ፍርድ እንደ ተፈረደብን ይሰማን ነበር፤ ይህም የሆነው ሙታንን በሚያስነሣ በእግዚአብሔር እንድንታመን እንጂ፣ በራሳችን እንዳንታመን ነው::»

20. ጳውሎስ እግዚአብሔር እንዳዳነውና ሁልጊዜም እንደሚያድነው ይናገራል::

2ኛ ቆሮ. 1:10-11:: «እርሱ እንዲህ ካለው የሞት አደጋ አድኖናል፤ ያድነናልም፤ ወደ ፊትም ደግሞ እንደሚያድነን ተስፋችንን በእርሱ ላይ ጥለናል:: እናንተም በጸሎታችሁ ደግፉን፤ በብዙዎች ጸሎት ስለ ተሰጠን ስጦታ ብዙ ሰዎች ስለ እኛ ምስጋና ያቀርባሉ::»

21. አንዳንድ ጊዜ እምነታችን ወርቅ በእሳት ውስጥ የሚፈተነውን ያህል የነጠረ እንዲሆንና በዚህም ምክንያት ክርስቶስ ይከብርና ከፍ ከፍ ይል ዘንድ እግዚአብሔር ይፈትነናል::

1ኛ ጴጥ. 1:7-8:: እነዚህ ነገሮች በእናንተ ላይ የደረሱት፣ በእሳት ተፈትኖ ቢጠራም፣ ጠፊ ከሆነው ወርቅ ይልቅ እጅግ የከበረው እምነታችሁ እውነተኛ መሆኑ እንደ ተረጋገጠና ኢየሱስ ክርስቶስ በሚገለጥበት ጊዜ ምስጋናን፣ ክብርንና ውዳሴን እንዲያስገኝላችሁ ነው:: እርሱንም ሳታዩት ትወዱታላችሁ፤ አሁን ባታዩትም በእርሱ ታምናላችሁ መግለጽ በማይቻልና ክብር በሞላበት ሐሤት ደስ ብሎአችኋል::

22. በመከራችሁ ጊዜ እንኳን የእግዚአብሔርን ጥበቃና ጥንቃቄ ትለማመዳላችሁ:: በእንባ ብትሆኑም እንኳ ለእግዚአብሔር ምስጋናን ትዘምራለችሁ::

መዝ. 27:5-6:: በመከራ ቀን፣ በድንኳኑ ውስጥ ይሰውረኛልና፤ በድንኳኑም ጓዳ ይሸሽገኛል፤ በዐለትም ላይ ያቆመኛል:: በዚህ ጊዜ በዙሪያዬ ባሉ ጠላቶቼ ላይ፣ ራሴ ከፍ ከፍ ይላል፤ በድንኳኑም ውስጥ የእልልታ መሥዋዕት እሠዋለሁ፤ ለእግዚአብሔር እቀኛለሁ፤ እዘምርለታለሁም::

23. ጳውሎስና ሲላስ ለወንጌል ብለው መከራን ሲቀበሉ ሳሉ ለእግዚአብሔር ምስጋናን ይዘምሩ ነበር::

የሐዋ. 16:16-28:: (ጳውሎስና ሲላስ በመጥፎ ሁኔታ ተገርፈው፣ ወደ እሥር ቤት ተጥለው፣ እግሮቻቸውም በእግር ብረት ተጠርቀው ነበር::)

የሐዋ. 16:25:: «እኩለ ሌሊት አካባቢ ጳውሎስና ሲላስ እየጸለዩና እየዘመሩ እግዚአብሔርን ሲያመሰግኑ ነበር፤ ሌሎቹ እስረኞችም ያደምጧቸው ነበር::

24. ጳውሎስ በሮም እስር ቤት ውስጥ መከራን እየተቀበለ በነበረበት ወቅት፣ እግዚአብሔር በዚህ ሁሉ ውስጥ ያደርግ ስለነበረው ነገር ይደሰት ነበር::

ፊል. 1:12-26::

ፊል. 1:12-14:: «አሁንም ወንድሞች ሆይ፤ በእኔ ላይ የደረሰው ነገር ወንጌል በይበልጥ እንዲስፋፋ መርዳቱን ታውቁ ዘንድ እወዳለሁ:: ከዚህ የተነሣ እስራቴ ስለ ክርስቶስ እንደ ሆነ፣ በቤተ መንግሥት ዘበኞችና በሌሎችም ሁሉ ዘንድ ታውቋል:: በእኔ

መታሰር ምክንያት በጌታ ካሉት ወንድሞች ብዙዎች የእግዚአብሔርን ቃል ያለ ፍርሀት፣ በድፍረት ለመናገር ብርታት አግኝተዋል::

25. ጳውሎስ በብዙ መልኩ መከራን ቢቀበልም እንኳ፣ ተስፋ አልቆረጠም:: እግዚአብሔርም በየዕለቱ ማበርታቱን ስለቀጠለ ከፊቱ ያለውን ዘላለማዊ ሽልማቱን መመልከት ችሎአል::

2ኛ ቆሮ. 4:8-18::

2ኛ ቆሮ. 4:16-18:: «ስለዚህ ተስፋ አንቈርጥም፤ ውጫዊው ሰውነታችን እየጠፋ ቢሄድም እንኳ፣ ውስጣዊው ሰውነታችን ዕለት ዕለት ይታደሳል፤ ምክንያቱም ቀላልና ጊዜያዊ የሆነው መከራችን ወደር የማይገኝለት ዘላለማዊው ክብር ያስገኝልናል:: ስለዚህ ዓይናችን የሚያተኲረው በሚታየው ነገር ላይ ሳይሆን በማይታየው ላይ ነው፤ የሚታየው ጊዜያዊ ነውና፤ የማይታየው ግን ዘላለማዊ ነው::

መከራን እንዴት መቋቋም እንደሚቻል በበለጠ ለመረዳት መጽናናትን ገጽ 46፤ ሞትንና የዘለዓለም ሕይወትን ገጽ 64፤ ጸሎትን ገጽ 166፤ የእግዚአብሔርን መጋቢነት ገጽ 176፤ እንዲሁም መታመንን ገጽ 224 ላይ ተመልከት::



# አስካሪ መጠጥና አደንዛዥ ዕፆችን ያለ አግባብ መጠቀም

ኃጢአትን ስለ ማሸነፍ ገጽ 142 ላይ ተመልከተ::

1. ሥጋችሁ የመንፈስ ቅዱስ ቤተ መቅደስ ነው::

1ኛ ቆሮ. 6:15:: «ሰውነታችሁ የክርስቶስ የአካሉ ብልቶች እንደ ሆነ አታውቁምን?»

1ኛ ቆሮ. 6:19-20:: «ለመሆኑ ሰውነታችሁ በውስጣችሁ የሚኖረው የመንፈስ ቅዱስ ቤተ መቅደስ እንደሆነ አታውቁምን? ይህም መንፈስ ከእግዚአብሔር የተቀበላችሁት ነው:: እናንተም የራሳችሁ አይደላችሁም፤ በዋጋ ተገዝታችኋልና፤ ስለዚህ በሰውነታችሁ እግዚአብሔርን አክብሩ::»

2. ኢየሱስ፣ አስካሪ መጠጥን ያለ አግባብ ስለመጠቀም ያስጠነቅቃል::

ሉቃስ 21:34:: እንግዲህ በገደብ የለሽ ሕይወት፣ በመጠጥ ብዛትና ስለ ኑሮ በመጨነቅ ልባችሁ እንዳይዝልና ያ ቀን እንደ ወጥመድ ድንገት እንዳይደርስባችሁ ተጠንቀቁ::

3. ወይን ጠጭ ፌዘኛ ብርቱ መጠጥም ጠበኛ ያደርጋል::

ምሳ.20:1:: «የወይን ጠጅ ፌዘኛ፣ ብርቱ መጠጥም ጠበኛ ያደርጋል፤ በእነዚህ የሳተ ሁሉ ጠቢብ አይደለም::»

4. ወይንን አትውደድ::

ምሳ. 21:17:: «ቅንጦትን የሚወድ ይደኸያል፤ የወይን ጠጅና ዘይት የሚወድም ባለጠጋ አይሆንም::»

5. ከበድ ያለ መጠጥ ሕይወትን ያበላሻል

ምሳ. 23:29-35::

6. የሰካራምን አሳዛኝ ገጽታ ተገንዘቡ:: (መጽሐፍ ቅዱስ ልክ እንዳለ ያስቀምጠዋል!)

ምሳ.23:32-35::

7. እስራኤላውያን ሰካራሞች በነበሩበት ሁኔታ ላይ የእግዚአብሔር

ቁጣ ተገልጾአል::

ኢሳ. 28:1-4::

8. ሰካራም ግብረ ገባዊውን ፍርድ እንደሚዘነጋ የሚያሳይ ጉልህ ሥዕልን ኢሳይያስ ያሳያል::

ኢሳ. 28:7-8:: «እነዚህም በወይን ጠጅ ይንገዳገዳሉ፤ በሚያሰክርም መጠጥ ይወላገዳሉ፤ ካህናቱና ነቢያቱ በሚያሰክር መጠጥ ተንገዳገዱ፤ በወይን ጠጅ ነገር ተምታታባቸው፤ በሚያሰክር መጠጥ ተወላገዱ፤ ራእይ ሲያዩ ይስታሉ፤ ፍርድ ሲሰጡም ይሰናከላሉ:: የማዕድ ገበታቸው ሁሉ በትፋት ተሞልቶአል፤ ከትውኪያም የጸዳ ቦታ የለም::»

9. ጳውሎስ የጊዜውን ማስጠንቀቂያና ትምህርት ይሰጣል::

ኤፌ. 5:15-18:: እንግዲህ ጥበብ እንደሌላቸው ሳይሆን እንደ ጥበበኞች እንዴት እንደምትኖሩ ተጠንቀቁ:: ቀኖቹ ክፉ ናቸውና ዘመኑን በሚገባ ዋጁ:: ስለዚህ ሞኞች አትሁኑ፤ የጌታ ፈቃድ ምን እንደሆነ አስተውሉ እንጂ:: በመንፈስ ተሞሉ እንጂ በወይን ጠጅ አትስከሩ፤ ይህ ብክነት ነውና::

10. ሰካራምነት ግብረ ገባዊነትን ያበላሻል::

ዘፍ. 9:20-23:: (የኖኅ ምሳሌ)

ዘፍ. 19:30-38:: (የሎጥ ምሳሌ)

11. ሰካራም ወደ እግዚአብሔር መንግሥት አይገባም::

1ኛ ቆሮ. 6:9-10:: «ዐመፀኞች የእግዚአብሔርን መንግሥት እንደማይወርሱ አታውቁምን? «በዚህ ነገር አትታለሉ፤ ሴሰኞች፣ ጣዖት አምላኪዎች አመንዝሮች፣ ወንደቃዎች፣ ግብረ ሰዶማውያን፣ ወይም ሌቦች፣ ስግብግቦች፣ ሰካራሞች፣ ተሳዳቢዎችና ቀማኞች የእግዚአብሔርን መንግሥት አይወርሱም»

12. አንድ ሰው ከሰካራምነት ሊድንና ነፃ ሊወጣ ይችላል::

1ኛ ቆሮ. 6:11:: «ከእናንተ አንዳንዶቻችሁ እንደዚህ ነበራችሁ፤ አሁን ግን በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ስምና፣ በአምላካችን መንፈስ



ታጥባችኋል፤ ተቀድሳችኋል፤ ጸድቃችኋል::»

13. ከሰከራሞች ጋር አትተባበሩ::

1ኛ ቆሮ. 5:11:: «ነገር ግን አሁን የጻፍሁላችሁ «ወንድም ነኝ» እያለ ከሚሴስን ወይም ከሚስገበገብ ወይም ጣዖትን ከሚያመልክ ወይም ከሚሳደብ ወይም ከሚሰክር ወይም ከሚቀማ ጋር እንዳትተባበሩ ነው፤ ከእንደዚህ ዐይነቱ ሰው ጋር ምግብ እንኳ አትብሉ::»

14. ጠቢባን ሁኑ! አስካሪ መጠጥን ያለ አግባብ ከሚጠቀሙ ጋር አትተባበሩ::

ምሳ. 23:19-20:: «ልጄ ሆይ አድምጥ፤ ጠቢብም ሁን፤ ልብህም ከትክክለኛው መንገድ አይውጣ:: ብዙ የወይን ጠጅ ከሚጠጡ፣ ሥጋ ከሚሰለቅጡ ጋር አትወዳጅ::»

# ቁጣ፣ ንዴት

ቁጣንና ንዴትን እንዴት ለመቆጣጠር እንደሚቻል ለማወቅ እንዲረዳህ ኃጢአትን ማሸነፍ በገጽ 142፣ እድገታዊ ቅድስናን በገጽ 170፣ እንዲሁም ራስን መግዛትን በገጽ 208 ላይ ተመልከት::

**1. ቁጣ በራሱ ኃጢአት አይደለም::**

መዝ. 7:11:: (እግዚአብሔር በኃጢአተኞች ላይ ይቆጣል::)

1ኛ ነገ. 11:9:: (እግዚአብሔር በሰሎሞን ላይ ተቆጣ::)

2ኛ ነገ. 17:18:: (እግዚአብሔር በእስራኤል ላይ ተቆጥቶ ነበር::)

ማር. 3:5 (ኢየሱስ በፈሪሳውያን ላይ ተቆጥቷል::)

**2. ለመቆጣት የዘገያችሁ ሁኑ::**

ምሳ. 14:16-17:: «ጠቢብ ሰው ጥንቁቅ ነው፤ ከክፉም ይርቃል፤ ተላላ ግን ችኩልና ደንታ ቢስ ነው:: ግልፍተኛ ሰው የቂል ተግባር ይፈጽማል፤ መሠሪም ሰው አይወደድም::»

ምሳ. 14:29፤ «ታጋሽ ሰው ትልቅ ማስተዋል አለው፤ ግልፍተኛ ሰው ግን ቂልነትን ይገልጣል::»

ያዕ. 1:19-20:: «የተወደዳችሁ ወንድሞቼ ሆይ፤ ይህን አስተውሉ፤ ሰው ሁሉ ለመስማት የፈጠነ ለመናገር የዘገየ፣ ለቍጣም የዘገየ ይሁን፤ የሰው ቍጣ የእግዚአብሔርን ጽድቅ አያመጣምና::»

**3. ፍቅር የኃጢአት ብዛትን ይሸፍናል፣ ብዙ ጉዳትንም ያልፋል::**

ምሳ. 10:12:: «ጥላቻ ጠብን ያነሣሣል፤ ፍቅር ግን ስሕተትን ሁሉ ይሸፍናል::»

ምሳ. 12:16:: «ተላላ ሰው ቍጣው ወዲያውኑ ይታወቅበታል፤ አስተዋይ ሰው ግን ስድብን ንቆ ይተዋል::»

ምሳ. 17:9:: «በደልን የሚሸፍን ፍቅርን ያዳብራል፤ ነገርን የሚደጋግም ግን የልብ ወዳጆችን ይለያያል::»

ምሳ. 19:11:: «ጥበብ ሰውን ታጋሽ ታደርገዋለች፣ በደልን ንቆ መተውም መከበሪያው ነው::»



1ኛ ጴጥ. 4:8:: ፍቅር ብዙ ኀጢአትን ይሸፍናልና ከሁሉ በላይ እርስ በርሳችሁ ከልብ ተዋደዱ፤

**4. የፍቅርን መንገድ ፈልጉ::**

1ኛ ቆሮ. 13:4-5:: «ፍቅር ታጋሽ ነው፤ ደግሞም ቸር ነው:: ፍቅር አይመቀኝም፤ አይመካም፤ አይታበይም፤ ተገቢ ያልሆነ ነገር አያደርግም፤ ራስ ወዳድ አይደለም፤ አይበሳጭም፣ በደልን አይቈጥርም::»

**5. የቃየን ቁጣ ወደ ጥላቻና ግድያ ተቀየረ::**

ዘፍ. 4:3-8::

ዘፍ. 4:4:: «አቤልም መጀመሪያ ከተወለዱት በጎች መካከል ስባቸውን መሥዋዕት አድርጎ አቀረበ:: እግዚአብሔም (ያህዌ) ወደ አቤልና ወደ መሥዋዕቱ ተመለከተ::»

ዘፍ. 4:8:: ቃይንም ወንድሙን አቤልን «እስቲ ና፤ ወደ መስኩ እንውጣ» አለው፤ በመስኩም ሳሉ፣ ቃየን ወንድሙን አቤልን አጠቃው፤ ገደለውም::

**6. ክፉ ቃላት ቁጣን ያባብሳሉ::**

ምሳ. 15:1:: «የለዘበ መልስ ቍጣን ያበርዳል፤ ክፉ ቃል ግን ቍጣን ይጭራል::»

**7. ግልፍተኛ ሰው ጠብ ያነሣሣል፤**

ምሳ. 15:18:: «ግልፍተኛ ሰው ጠብ ያነሣሣል፤ ታጋሽ ሰው ግን ጠብን ያበርዳል::»

**8. ከግልፍተኛ ሰው ጋር አትተባበር::**

ምሳ. 22:24-25:: ከግልፍተኛ ጋር ወዳጅ አትሁን፤ በቀላሉ ቱግ ከሚልም ሰው ጋ አትወዳጅ፤ አለበለዚያ መንገዱን ትማራለህ፤ ራስህም ትጠመድበታለህ::

**9. ራስህን ተቆጣጠር::**

ምሳ. 25:28:: «ራሱን የማይቈጣጠር ሰው፣ ቅጥሩ እንደ ፈረሰ ከተማ ነው::»

ምሳ. 29:22:: «ቍጡ ሰው ጠብን ይጭራል፤ ግልፍተኛም ብዙ ኀጢአት ይሠራል::»

ምሳ. 30:33:: «ወተት ሲናጥ ቅቤ እንደሚወጣው፣ አፍንጫን ሲያሹት እንደሚደማ፣ ቍጣን ማነሣሣትም ጥልን ይፈጥራል::

10. ድንገት የሚነድድ ቁጣ የኃጢአተኛው ተፈጥሮአችሁ ባሕርይና የኃጢአት መንገድ ነው::

ገላ. 5:19-21::

11. የምሥራች! በመንፈስ ቅዱስ ኃይል የግልፍተኝነትን ኃጢአት ማሸነፍ ትችላላችሁ::

ገላ. 5:22-25:: «የመንፈስ ፍሬ ግን ፍቅር፣ ደስታ፣ ሰላም፣ ትዕግሥት፣ ቸርነት፣ በጎነት፣ ታማኝነት፣ ገርነት፣ ራስን መግዛት ነው:: እንደነዚህ ያሉትንም የሚከለክል ሕግ የለም:: የክርስቶስ ኢየሱስ የሆኑት ሥጋን ከክፉ ምኞቱና መሻቱ ጋር ሰቅለውታል:: በመንፈስ የምንኖር ከሆን፣ በመንፈስ እንመላለስ:: እርስ በርሳችን እየተጎነታተልንና እተቀናናን በከንቱ ውዳሴ አንመካ::

ቆላ. 3:8:: «አሁን ግን ቍጣን፣ ንዴትን፣ ስድብን፣ ሐሜትንና አሳፋሪ ንግግርን የመሳሰሉትንም ሁሉ አስወግዱ::

12. ቁጣን በመንፈሳዊ መንገድ ያዙት:: በቁጣችሁ ላይ ፀሐይ አይግባ::

ኤፌ. 4:26:: ተቈጡ፤ ነገር ግን ኀጢአት አትሥሩ፤ በቍጣችሁ ላይ ፀሐይ አይግባ::

13. ኢየሱስ፣ ያለ ምክንያት በወንድሙ ላይ የሚቆጣ ፍርድ ይገባዋል አለ::

ማቴ. 5:21-22:: «ለቀደሙት ሰዎች፣ 'አትግደል፤ የገደለ ይፈረድበታል' እንደ ተባለ ሰምታችኋል፤ እኔ ግን እላችኋለሁ፤ ወንድሙን ያለ አግባብ የሚቈጣ ይፈረድበታል፤ ማንም ወንድሙን «ጅል» የሚለው በሸንጐ ፊት ይጠየቅበታል፤ 'ደደብ' የሚለው ደግሞ የገሃነም እሳት ፍርድ ይጠብቀዋል::



# የደኅንነት ማረጋገጫ

1. ኢዮብ ማረጋገጫ ነበረው::

ኢዮብ 19:25-27:: «የሚቤዠኝ ሕያው እንደ ሆነ፣ በመጨረሻም በምድር ላይ እንደሚቆም ዐውቃለሁ:: ቈዳዬም ቢጠፋም፣ ከሥጋዬ ብለይም፣ <u>እግዚአብሔርን</u> እየዋለሁ፤ ሌላ ሳይሆን እኔው በገዛ ዐይኔ እኔ ራሴ እየዋለሁ፤ ልቤ በውስጤ ምንኛ ዛለ!»

2. መንፈስ ቅዱስ ከመንፈሳችን ጋር ሆኖ ይመሰክራል::

ሮሜ 8:16-17:: «የእግዚአብሔር ልጆች መሆናችንን ያ መንፈስ ራሱ ከመንፈሳችን ጋር ሆኖ ይመሰክርልናል:: ልጆች ከሆን ወራሾች ደግሞ ነን፤ የክብሩ ተካፋዮች እንሆን ዘንድ በእርግጥ የመከራው ተካፋዮች ብንሆን፣ <u>የእግዚአብሔር</u> ወራሾች ከክርስቶስ ጋር አብረን ወራሾች ነን::»

3. በእርሱ እንደምንኖር እናውቃለን፤ እግዚአብሔር ለእኛ ያለውን ፍቅር እናውቃለን፣ እንደገፍበትማለን::

1ኛ ዮሐ. 4:13-16:: «መንፈሱን ስለ ሰጠን፣ እኛ በእርሱ እንደምንኖር እርሱም በእኛ እንደሚኖር እናውቃለን:: አብ ልጁን የዓለም አዳኝ ይሆን ዘንድ እንደላከው ዐይተናል፤ እንመሰክራለንም:: ኢየሱስ <u>የእግዚአብሔር</u> ልጅ እንደ ሆነ አምኖ በሚመሰክር ሁሉ፣ <u>እግዚአብሔር</u> በእርሱ ይኖራል፤ እርሱም <u>በእግዚአብሔር</u> ይኖራል:: ስለዚህም እግዚአብሔር ለእኛ ያለውን ፍቅር እናውቃለን፤ በፍቅሩም እናምናለን::

4. የዘላለም ሕይወት እንዳላችሁ እንድታውቁ::

1ኛ ዮሐ. 5:13:: «<u>በእግዚአብሔር</u> ልጅ ስም የምታምኑ እናንተ፣ የዘላለም ሕይወት እንዳላችሁ ታውቁ ዘንድ ይህን እጽፍላችኋለሁ፤»

5. ጳውሎስ የዘላለም ሕይወት ማረጋገጫ ነበረው::

2ኛ ጢሞ. 1:12:: «መከራን የምቀበለውም ለዚሁ ነው፤ ሆኖም ያመንሁትን እርሱን ስለማውቅ አላፍርበትም፤ የሰጠሁትንም ዐደራ እስከዚያች ቀን ድረስ መጠበቅ እንደሚችል ተረድቻለሁ::»

6. አሁን የእግዚአብሔር ልጆች ነን፣ እርሱንም እንመስላለን::

1ኛ ዮሐ. 3:1-3:: «የእግዚአብሔር ልጆች ተብለን እንድንጠራ አብ አትረፍርፎ ያፈሰሰልን ፍቅር ምንኛ ታላቅ ነው! እኛም እንዲሁ ልጆቹ ነን:: ዓለም እኛን የማያውቀንም እርሱን ስላላወቀው ነው:: ወዳጆች ሆይ፤ እኛ አሁን የእግዚአብሔር ልጆች ነን፤ ወደ ፊት ምን እንደምንሆን ገና አልተገለጠም:: እርሱ በሚገለጥበት ጊዜ እናየዋለንና፣ እርሱን እንደምንመስል እናውቃለን:: በእርሱ ይህን ተስፋ የሚያደርግ ሁሉ፣ እርሱ ንጹሕ እንደ ሆነ ራሱን ያነጻል::

7. ክርስቲያን፣ በክርስቶስ ትንሣኤ አማካይነት ሕያው ተስፋ አለው::

1ኛ ጴጥ. 1:3-5:: የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ አባትና አምላክ ይባረክ፤ እርሱ ከታላቅ ምሕረቱ የተነሣ በኢየሱስ ክርስቶስ ከሞት መነሣት ምክንያት ለሕያው ተስፋ በሚሆን አዲስ ልደት፣ እንዲሁም በሰማይ ለማይጠፋ፣ ለማይበላሽና ለማይለወጥ ርስት እንደገና ወለደን:: እናንተም በመጨረሻው ዘመን ሊገለጥ የተዘጋጀው ድነት እስከመጣ ድረስ በእምነት አማካይነት በእግዚአብሔር ኀይል ተጠብቃችኋል::



# ምሬት፣ ቅሬታ፣ ጥላቻ

1. በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ምክንያት ሁሉም ክርስቲያን ምሬትንና ጥላቻን አስወግዶ ደግ፣ ርኅሩኅ፣ ይቅር ባይ ሊሆን ይችላል፣ ይገባልም::

ኤፌ. 4:31-32:: መራርነትን ሁሉ፣ ቍጣና ንዴትን፣ ጭቅጭቅና ስድብን ከማንኛውም ክፋት ጋር ከእናንተ ዘንድ አስወግዱ:: እግዚአብሔር በክርስቶስ ይቅር እንዳላችሁ፣ እናንተም ይቅር ተባባሉ፤ እርስ በርሳችሁ ቸሮችና ርኅሩኆች ሁኑ::

2. እርስ በርሳችሁ መጣላትንና መነካከስን አቁሙ::

ገላ. 5:15:: «ነገር ግን እርስ በርሳችሁ የምትነካከሱና የምትበላሉ ከሆነ፣ እርስ በርሳችሁ እንዳትጠፋፉ ተጠንቀቁ::»

3. መራርነት የኃጢአተኛው ተፈጥሮ ባሕርይ ነው::

ገላ. 5:19:: «የሥጋ ሥራ ግልጽ ነው:- ይኸውም ዝሙት፣ ርኵሰት፣ መዳራት፣ ጣዖትን ማምለክ፣ ሟርት፣ ጥላቻ፣ ጠብ፣ ቅናት፣. . . እንዲሁም እነዚህን የመሰለው ነው::»

4. መራራ ሥር እንዳይበቅል አድርጉ::

ዕብ. 12:15:: «ከእናንተ ማንም የእግዚአብሔር ጸጋ እንዳይጐድልበት ደግሞም መራራ ሥር በቅሎ ችግር እንዳያስከትልና ብዙዎችን እንዳይበክል ተጠንቀቁ::

5. የዮሴፍ ወንድሞች መራርነት ወደ ጥላቻና ወደ ነፍስ መግደል እንዲያድግ ፈቀዱ::

ዘፍ፣ 37::

6. የቃየን ቁጣ ወደ መራርነት፣ ጥላቻና ነፍስ ግድያ ተለወጠ::

ዘፍ. 4:3-8::

7. ጥላቻ የተከለከለ ነው::

ዘሌዋ. 19:16-17 «በሕዝብህ መካከል ሐሜት አትንዛ፤ «የባልንጀራህን ሕይወት አደጋ ላይ የሚጥል ማንኛውንም ነገር

አታድርግ፤ እኔ እግዚአብሔር (ያህዌ) ነኝ:: «ወንድምህን በልብህ አትጣለው፤ የበደሉ ተካፋይ እንዳትሆን ባልንጀራህን በግልጽ ገሥጸው::»

**8. የሚጠላ በጨለማ ውስጥ ይኖራል::**

1ኛ ዮሐ. 2:9-11:: «በብርሃን አለሁ የሚል፣ ወንድሙን ግን የሚጠላ አሁንም በጨለማ ውስጥ አለ:: ወንድሙን የሚወድ በብርሃን ይኖራል፤ በእርሱም ዘንድ የመሰናከያ ምክንያት የለውም:: ነገር ግን ወንድሙን የሚጠላ በጨለማ ውስጥ ነው፤ በጨለማ ይመላለሳል፤ ጨለማው ስላሳወረውም የት እንደሚሄድ አያውቅም::»

**9. የተንኰለኛ ሰው መንገድ ሸንገላ ነው::**

ምሳ. 26. 24-26:: «ተንኰለኛ በከንፈሩ ይሸነግላል፤ በልቡ ግን ክፋትን ይቋጥራል:: ንግግሩ ማራኪ ቢሆንም አትመነው፤ ሰባት ርኵሰት ልቡን ሞልቶታልና:: ተንኰሉ በሽንገላው ይሸፈን ይሆናል፤ ነገር ግን ክፋቱ በጉባኤ ይገለጣል::»

**10. ጥላቻ ነፍስ ግድያ ነው::**

1ኛ ዮሐ. 3:11-20::

1ኛ ዮሐ. 3:15:: «ወድሙን የሚጠላ ነፍሰ ገዳይ ነው፤ ነፍሰ ገዳይም የዘላለም ሕይወት እንደሌለው ታውቃላችሁ::»

**11. ኢየሱስ ጠላቶቻችንን እንዳንጠላ፣ ይልቁንም እንድንወዳቸውና እንድንጸልይላቸው አሳሰበን::**

ማቴ. 5:43-48::

**12. እግዚአብሔርን እወዳለሁ እያልክ ወንድምህን የምትጠላ ብትሆን፣ ውሸተኛ ነህ?**

1ኛ ዮሐ. 4:20-21:: ማንም፣ «<u>እግዚአብሔርን</u> እወደዋለሁ» እያለ ወንድሙን ቢጠላ፣ እርሱ ሐሰተኛ ነው፤ ያየውን ወንድሙን የማይወድ ያላየውን <u>እግዚአብሔርን</u> መውደድ አይችልምና:: እርሱም «እግዚአብሔርን የሚወድ ሁሉ ወንድሙን መውደድ ይገባዋል» የሚለውን ይህን ትእዛዝ ሰጥቶናል::

**13. ጥላቻን በልብ ውስጥ በመሸሸግ ወይም መያዝ በእግዚአብሔር ፊት መዋሸት ነው::**



ምሳ. 10:18:: «ጥላቻውን የሚሸሽግ ሐሰተኛ አንደበት ያለው ነው፤ ሐሜትን የሚዘራ ሁሉ ተላላ ነው::»

**14. ጥላቻ ጠብን ያነሣሣል::**

ምሳ. 10:12:: «ጥላቻ ጠብን ያነሣሣል፤ ፍቅር ግን ስሕተትን ሁሉ ይሸፍናል::»

# ማመካኘት

**1. አዳምና ሔዋን አንዳቸው በሌላኛቸው ሊያሳብቡ ሞከሩ፡፡**

ዘፍ. 3:12-13፡፡ «አዳምም፣ «ይህች ከእኔ ጋር እንድትኖር የሰጠኸኝ ሴት፣ እርሷ ከዛፍ ፍሬ ሰጠችኝና በላሁ» አለ፡፡ <u>እግዚአብሔር</u> አምላክ (ያህዌ ኤሎሂም) ሴቲቱን፣ «ይህ ያደረግሽው ምንድን ነው?» አላት፡፡ እርሷም፣ «እባብ አሳሳተኝና በላሁ» አለች፡፡»

**2. አንዳንዶች በእግዚአብሔር ላይ ሊያሳብቡ ይሞክራሉ፡፡**

ምሳ. 19:3፡፡ «ሰው በራሱ ተላላነት ሕይወቱን ያበላሻል፤ በልቡ ግን <u>እግዚአብሔርን</u> ያማርራል፡፡»

**3. የራሳችሁን ኃጢአት ማስተዋል ተስኗችሁ እያለ በሌሎች ላይ አትፍረዱ፡፡**

ማቴ. 7:1-5፡፡ «እንዳይፈረድባችሁ በማንም ሰው ላይ አትፍረዱ፤ በምትፈርዱበትም ዐይነት ይፈረድባችኋል፤ በምትሰፍሩበትም መስፈሪያ ይሰፈርላችኋል፡፡ በዐይንህ ውስጥ ያለውን ግንድ ሳትመለከት፣ በወንድምህ ዐይን ያለውን ጉድፍ ለምን ታያለህ? በዐይንህ ውስጥ ግንድ እያለ ወንድምህን <ዓይንህ ውስጥ ያለውን ጉድፍ ላውጣልህ> ማለት እንዴት ትችላለህ? አንተ ግብዝ፤ አስቀድመህ በዐይንህ ውስጥ ያለውን ግንድ አውጣ፤ ከዚያም በወንድምህ ዐይን ውስጥ ያለውን ጉድፍ ለማውጣት አጥርተህ ታያለህ፡፡



# ልጆች

በተጨማሪ ልጆችን ማሠልጠን የሚለውን በገጽ 220 ላይ፣ እንዲሁም ወጣቶች የሚለውን በገጽ 245 ላይ ተመልከት፡፡

**1. ልጆች በመጀመሪያ ደረጃ የእግዚአብሔር ሲሆኑ፣ ለእኛም የተሰጡ የእርሱ ስጦታዎች ናቸው፡፡**

መዝ. 127:3-5፡፡

መዝ. 127:3፡፡ «እነሆ፤ ልጆች <u>የእግዚአብሔር</u> ስጦታ ናቸው፤ የማሕፀንም ፍሬ ከቸርነቱ የሚገኝ ነው፡፡»

**2. የአማኞች ልጆች የእግዚአብሔር ናቸው፡፡ በእርሱም ቃል ኪዳን ውስጥ የተካተቱ ናቸው፡፡**

ዘፍ. 17:7፡፡ «በእኔና በአንተ፣ ከአንተም በኋላ ከዘርህ ጋር ከትውልድ እስከ ትውልድ የዘላለም ኪዳኔን እመሠርታለሁ፤ በዚህም የእናንተና ከአንተም በኋላ የዘርህ አምላክ (ኤሎሂም) እሆናለሁ፡፡

የሐዋ. 2:39፡፡ «የተስፋው ቃል ለእናንተና ለልጆቻችሁ እንዲሁም <u>ጌታ አምላካችን</u> ወደ ራሱ ለሚጠራቸው፣ በሩቅ ላሉትም ሁሉ ነውና፡፡»

**3. እግዚአብሔር በልጆች ምስጋናና አምልኮ ይደሰታል፡፡**

መዝ. 8:2፡፡ «ከልጆችና ጡት ከሚጠቡ ሕፃናት አፍ፣ ምስጋናን አዘጋጀህ፤ ከጠላትህ የተነሣ፤ ባላንጣንና ቂመኛን ጸጥ ታሰኝ ዘንድ፡፡»

**4. ኢየሱስ የልጆን ምስጋና ተቀበለ፡፡**

ማቴ. 21:15-16፡፡ «ነገር ግን የካህናት አለቆችና የኦሪት ሕግ መምህራን ያደረጋቸውን ታምራትና፣ «ሆሣዕና፤ ለዳዊት ልጅ» እያሉ የሚጮኹትን ሕፃናት ባዩ ጊዜ በቍጣ ተሞሉ፡፡ እነርሱም፣ «እነዚህ ሕፃናት የሚሉትን ትሰማለህ» አሉት፡፡ ኢየሱስም፣ «አዎን እሰማለሁ፤ እንዲህ የሚለውን ከቶ አላነበባችሁምን?» «ከልጆችና ጡት ከሚጠቡ፣ ሕፃናት አፍ ምስጋናን አዘጋጀህ፡፡»

**5. ኢየሱስ ልጆችን ይወዳል፡፡ የእግዚአብሔር መንግሥት እንደ እነርሱ ላሉት ናት፡፡**

ማቴ. 19:13-15:: ከዚያም እጆቹን በላያቸው ላይ ጭኖ እንዲጸልይላቸው ሕፃናትን ወደ እርሱ አቀረቧቸው:: ደቀ መዛሙርቱ ግን ሕፃናቱን ያመጡትን ሰዎች ገሠጿቸው:: ኢየሱስም፣ «ሕፃናት ወደ እኔ ይምጡ፤ አትከልክሏቸው፤ መንግሥተ ሰማይ እንደ እነርሱ ላሉት ናትና» አላቸው:: እጁንም ከጫነባቸው በኋላ ከዚያ ስፍራ ተነሥቶ ሄደ::

6. **ዳዊት ልጁ እንደ ሞተ ወደ ሰማይ እንደ ሄደና እርሱም እዚያው እንደሚያገኘው በማወቁ ተጽናና::**

2ኛ ሳሙ. 12:18-23::

2ኛ ሳሙ. 12:23:: «አሁን ግን ሕፃኑ ስለ ሞተ፣ የምጾመው ለምንድን ነው? መልሼ ላመጣው እችላለሁን? እኔ ወደ እርሱ እሄዳለሁ እንጂ፣ እርሱ ወደ እኔ አይመለስ!»



# ቤተ ክርስቲያን፣ የቅዱሳን ኅብረት

በተጨማሪ ሌሎችን መውደድና ማገልገል የሚለውን በገጽ 118 ላይ፣ እንዲሁም የቤተ ክርስቲያን ተግሣጽ (እርማት) የሚለውን በገጽ 43 ላይ ተመልከት::

1. **ቤተ ክርስቲያን አንድ ናት::**

ኤፌ. 4:3-6:: «በሰላም ማሰሪያ የመንፈስን አንድነት ለመጠበቅ ትጉ:: በተጠራችሁ ጊዜ ወደ አንድ ተስፋ እንደተጠራችሁ ሁሉ አንድ አካልና አንድ መንፈስ አለ፤ አንድ ጌታ፣ አንድ እምነትና አንድ ጥምቀት አለ፤ ከሁሉም በላይ የሆነ፣ በሁሉም የሚሠራ፣ በሁሉ የሚኖር የሁሉም አባት የሆነ አንድ አምላክ አለ::»

2. **ቤተ ክርስቲያን ብዙ አገልግሎት ያላት አንድ አካል ናት፣ እያንዳንዱም አባል ዓላማ አለው::**

ሮሜ 12:4-8:: «እያንዳንዳችን በአንዱ አካላችን ብዙ ብልቶች እንዳሉን፣ እነዚህም ብልቶች አንድ ዐይነት ተግባር እንደ ሌላቸው ሁሉ፣ እንዲሁም እኛ ብዙዎች ስንሆን በክርስቶስ አንድ አካል ነን:: እያንዳንዳችንም የሌላው ብልት ነን:: እንደ ተሰጠን ጸጋ የተለያዩ ስጦታዎች አሉን፤ ለአንዱ የተሰጠው ስጦታ ትንቢት መናገር ከሆነ፣ እንደ እምነቱ መጠን ይናገር:: ማገልገል ቢሆን ያገልግል፤ ማስተማርም ከሆነ ያስተምር፤ መምከር ከሆነ ይምከር፤ ለሌላቸው መለገስ ከሆነም አብዝቶ ይለግስ፤ ማስተዳደር ከሆንም በትጋት ያስተዳድር፤ ምሕረት ማድረግ ከሆነም በደስታ ይማር::»

3. **በኅብረት፣ ክርስቲያኖች እግዚአብሔር በመንፈሱ የሚኖርበትን ቤተሰብ ይመሠርታሉ::**

ኤፌ. 2:19-22:: «ከዚህ የተነሣ እናንተ ከቅዱሳን ጋር የአንድ አገር ዜጋ፣ የእግዚአብሔርም ቤተሰብ አባል ናችሁ እንጂ፣ ከእንግዲህ ወዲህ መጻተኞችና እንግዶች አይደላችሁም:: በሐዋርያትና በነቢያት መሠረት ላይ ታንጻችኋል፤ የማእዘኑ ራስ ድንጋይም ክርስቶስ ኢየሱስ ራሱ ነው፤ በእርሱ ሕንፃ ሁሉ አንድ ላይ ተገጣጥሞ በጌታ ቅዱስ ቤተ መቅደስ እንዲሆን ያድጋል::» እናንተም ደግሞ

እግዚአብሔር በመንፈሱ የሚኖርበት ማደሪያ ትሆን ዘንድ አብራችሁ እየተገነባችሁ ነው።»

4. **የአማኞች አንድነት ጠብቁ፤ ሰዎችን ሳይሆን ክርስቶስን ተከተሉ።**

1ኛ ቆሮ. 1፡10-17።

1ኛ ቆሮ. 1፡11-13። «ወንድሞች ሆይ፤ በመካከላችሁ ክርክር እንዳለ ከቀሎዔ ቤተሰብ ሰምቻለሁ፤ ነገሩም እንዲህ ነው፤ ከእናንተ አንዱ፣ «እኔ የጳውሎስ ነኝ» ሲል፣ ሌላው፣ «እኔ የአጵሎስ ነኝ» ይላል፤ ደግሞም አንዱ፣ «እኔ የኬፋ ነኝ» ሲል፣ ሌላው ደግሞ፣ «እኔስ የክርስቶስ ነኝ» ይላል። ለመሆኑ ክርስቶስ ተከፍሎአልን? ጳውሎስስ ለእናንተ ተሰቅሎአልን? ወይስ በጳውሎስ ስም ተጠምቃችኋልን?»

5. **የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች ይለያያሉ። እያንዳንዱ አባል ስጦታውን ሌሎችን ለማገልገል መጠቀም አለበት።**

ኤፌ. 4፡11-13። «አንዳንዶቹ ሐዋርያት፣ አንዳንዶቹ ነቢያት፣ አንዳንዶቹም ወንጌል ሰባኪዎች፣ ሌሎቹ ደግሞ እረኞችና አስተማሪዎች ይሆኑ ዘንድ የሰጠ እርሱ ነው፤ ይኸውም የክርስቶስ አካል ይገነባ ዘንድ፣ ቅዱሳንን ለአገልግሎት ሥራ ለማዘጋጀት ሲሆን፣ ይህም የሚሆነው፣ ሁላችንም የእግዚአብሔርን ልጅ በማመንና በማወቅ ወደሚገኘው አንድነት በመምጣትና ሙሉ ሰው በመሆን፣ በክርስቶስ ወዳለው ፍጹምነት ደረጃ እስከምንደርስ ነው።»

1ኛ ቆሮ. 12፡1-11።

1ኛ ቆሮ. 12፡4-7። «ስጦታዎች ልዩ ልዩ ሲሆኑ፣ መንፈስ ግን አንድ ነው፤ አገልግሎትም ልዩ ልዩ ሲሆን፣ ጌታ ግን አንድ ነው፤ አሠራርም ልዩ ልዩ ሲሆን፣ ሁሉን በሁሉ የሚሠራው ግን ያው አንዱ እግዚአብሔር ነው። ነገር ግን መንፈስ ቅዱስን መግለጥ ለእያንዳንዱ ሰው የሚሰጠው ለጋራ ጥቅም ነው።»

6. **እያንዳንዱ የአካል ክፍል አስፈላጊ ነው። አንዳችን ሌላችን እንፈልጋለን። ሁሉም ሰው ለሌላው ሰጡ ጥልቅ ሸክም**



**ሊኖረው ይገባል።**

1ኛ ቆሮ. 12፡12-31።

1ኛ ቆሮ. 12፡25-26። ይህንም ያደረገው በአካል ብልቶች መካከል መለያየት ሳይኖር፣ እርስ በርሳቸው እኩል እንዲተሳሰቡ ነው። አንድ ብልት ቢሠቃይ ብልቶች ሁሉ አብረው ይሠቃያሉ፤ አንድ ብልት ቢከብር ሌሎችም ብልቶች አብረው ደስ ይላቸዋል።

7. **ክርስቶስ አካሉ የሆነችው የቤተ ክርስቲያን ራስ ነው።**

ኤፌ. 1፡22-23። «እግዚአብሔርም ሁሉን ከእግሩ በታች አስገዛለት፤ በቤተ ክርስቲያንም፣ በማንኛው ነገር ላይ ራስ አድርጎ ሾመው። እርሷም ሁሉን ነገር በሁሉም ረገድ የሚሞላው፣ የእርሱ ሙላት የሆነች አካሉ ናት።»

ኤፌ. 5፡23። «ክርስቶስ፣ አካሉ ለሆነችውና አዳኟ ለሆናት ቤተ ክርስቲያን ራስ እንደ ሆነ ሁሉ፣ ባልም የሚስቱ ራስ ነውና።

8. **ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያንን ይወዳል።**

ኤፌ. 5፡25። «ባሎች ሆይ፤ ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያንን እንደ ወደዳትና ራሱንም ስለ እርሷ አሳልፎ እንደ ሰጠ፣ እናንተም ሚስቶቻችሁን ውደዱ፤»

9. **የአምልኮ ሥርዓቶችን በታማኝነት ተከታተል።**

ዕብ. 10፡25። «አንዳንዶች ማድረጉን እንደተዉት መሰብሰባችንን አንተው፤ ይልቁንም ቀኑ እየተቃረበ መምጣቱን ስታይ እርስ በርሳችን እንበረታታ።»

10. **ዘማሪው በእግዚአብሔር ቤት ለመሆን ተመኘ።**

መዝ. 84።

መዝ. 84፡1-2። «የሰራዊት አምላክ ሆይ፤ ማደሪያህ ምንኛ የተወደደ ነው! ነፍሴ የእግዚአብሔርን አደባባዮች ትናፍቃለች፤ እጅግም ትጓጓለታለች፤ ልቤና ሥጋዬም ለሕያው አምላክ እልል በሉ።»

መዝ. 84፡10። «በሌላ ስፍራ ሺህ ቀን ከመኖር፣ በአደባባይህ

እንዲት ቀን መዋል ይሻላል፤ በክፉዎችም ድንኳን ከመቀመጥ ይልቅ፣ በአምላኬ ቤት ደጅ መቆም እመርጣለሁ።»

11. ሐዋርያው ጳውሎስ ወደ ፊልሞና በላከው መልእክት ላይ ስለ ቅዱሳን ኅብረት ውብት ያለው ትምህርት ተሰጥቶታል።

የፊልሞና መልእክት (ጳውሎስ ይህን መልእክት የጻፈው አናሲሞስን በተመለከተ ሲሆን፣ የተጻፈውም ለቅርብ ወዳጁና አብሮት ለሚሠራው ፊልምና ነው፣ መልእክቱም ፊልሞና አናሲሞስን ተወዳጅ ወንድም አድርጐ እንዲቀበለው የሚለምን ነበር።)

ቁ. 10-12። «በእስር እያለሁ ስለ ወለድሁት ልጄ ስለ አናሲሞስ እለምንሃለሁ። አስቀድሞ የሚጠቅምህ አልነበረም፤ አሁን ግን ለአንተም ሆነ ለእኔ የሚጠቅም ሰው ሆኖአል። የልቤ ሰው የሆነውን እርሱን መልሼ ወደ አንተ ልኬዋለሁ።»

ቁ. 15-16። «ምናልባት ለጥቂት ጊዜ ከአንተ የተለየው፣ ተቀብለህ ለዘለቄታው አንተ ዘንድ እንድታቈየው ነው፤ ከእንግዲህ ወዲህ ግን እንደ ባሪያ ሳይሆን ከባሪያ በላይ የሆነ ተወዳጅ ወንድም ነው። ለእኔ ተወዳጅ ነው፤ ለአንተ ግን በሥጋም በጌታም ይበልጥ ተወዳጅ ነው!።»

12. ሽማግሌዎች በኢየሱስ ክርስቶስ መንጋ ላይ የበላይ ተቆጣጣሪ ሆነው በእግዚአብሔር የተሾሙ እረኞች ናቸው።

ሐዋ 20:28። ለራሳችሁና መንፈስ ቅዱስ ጠባቂ አድርጎ በላዩ ለሾማችሁ መንጋ ሁሉ ተጠንቀቁ፤ በገዛ ደሙ የዋጃትን የእግዚአብሔርን ቤተ ክርስቲያን ጠብቁ።

13. ባለ ቢሮዎች ሰዎች በትክክለኛው መንገድ ላይ እንዲሄዱ ማስጠንቀቅ አለባቸው።

ሕዝ. 33:7-9። «የሰው ልጅ ሆይ፤ አንተን ለእስራኤል ቤት ጉበኛ አድርጌሃለሁ፤ ስለዚህ የምናገረውን ቃል ስማ፤ ማስጠንቀቂያዬንም ስጣቸው። ክፉውን፣ <አንተ ክፉ ሰው፤ በእርግጥ ትሞታለህ> ባልሁት ጊዜ፣ እርሱን ከመንገዱ እንዲመለስ



ባታደርገው፣ ያ ክፉ ሰው በኀጢአቱ ይሞታል፤ አንተ ግን ስለ ደሙ ተጠያቂ ትሆናለህ። ነገር ግን ክፉውን ሰው ከመንገዱ እንዲመለስ ነግረኸው እሺ ባይል፣ እርሱ ስለ ኀጢአቱ ይሞታል፤ አንተ ግን ራስህን አድነሃል።»

14. እግዚአብሔር ታማኝነት ያጐደሉ እረኞችን ይኮንናቸዋል እንዲሁም ያስጠነቅቃቸዋል።

ሕዝ. 34:1-16።

15. የቤተ ክርስቲያን አባላት እግዚአብሔር፣ ሥልጣናቸውን ተግባራዊ ያደርጉ ዘንድ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የሾማቸውን ሽማግሌዎች ማክበርና መታዘዝ አለባቸው።

1ኛ ጢሞ. 5:17። ቤተ ክርስቲያንን በሚገባ የሚያስተዳድሩ፣ ይልቁንም በመስበክና በማስተማር የሚተጉ ሽማግሌዎች ዕጥፍ ክብር ይገባቸዋል፤

ዕብ. 13:17። ለመሪዎቻችሁ ታዘዙ፤ ተገዙላቸውም። ምክንያቱም እነርሱ በብርቱ የሚያስጠይቃቸው ነገር ስላለባቸው፣ ስለ ነፍሳችሁ ጉዳይ ይተጋሉ። ስለዚህ ሥራቸውን በሐዘን ሳይሆን በደስታ ማከናወን እንዲችሉ ታዘዟቸው። አለበለዚያ አይበጃችሁም።

16. የእግዚአብሔር ሹመት ያላቸው ሰዎች ሌሎች ነገሮችን እንዲናገሩ ጫና ቢበዛባቸውም እግዚአብሔር የሚጠብቅባቸውን ብቻ መናገር አለባቸው።

1ኛ ነገ. 22:1-14።

1ኛ ነገ. 22:8-9። የእስራኤልንም ንጉሥ ለኢዮሳፍጥ፣ «መኖሩንማ በእርሱ አማካይነት <u>የእግዚአብሔርን</u> ፈቃድ የምንጠይቀው አንድ ሰው አሁንም አለ፤ ነገር ግን ምን ጊዜም ቢሆን ስለ እኔ ክፉ እንጂ እንዳችም መልካም ትንቢት ተናግሮ ስለማያውቅ እጠላዋለሁ፤ ይህም ሰው የይምላ ልጅ ሚክያስ ነው» አለ። ኢዮሣፍጥም «ንጉሡ እንዲህ ማለት አይገባውም» ሲል መለሰ። ስለዚህ የእስራኤል ንጉሥ ከሹማምቱ አንዱን ጠርቶ፣ «በል የይምላን ልጅ ሚክያስን በፍጥነት አምጣው» አለው።

1ኛ ነገ. 22:13-14:: ከዚያም ሚክያስን ሊጠራ የሄደው መልእክተኛ፣ «እነሆ፣ ሌሎቹ ነቢያት ንጉሡ ድል እንደሚያደርግ በአንድ ቃል ትንቢት እየተናገሩለት ነውና ያንተም ቃል ከእነርሱ ጋር አንድ እንዲሆን እባክህ መልካም ነገር ተናገር» አለው:: ሚክያስ ግን፣ «ሕያው <u>እግዚአብሔርን</u>! ለእርሱ የምነግረው <u>እግዚአብሔር</u> የነገረኝን ብቻ ነው» አለ::

17. ኢየሱስ ለቤተ ክርስቲያን ይጸልይላታል::

ዮሐ. 17:6-26:: (የኢየሱስ ሊቀ ካሕናዊ ጸሎት)

18. ቤተ ክርስቲያን ከሁሉም ሕዝቦችና ከሁሉም ነገዶች የተውጣጣች የብዙ ሕዝብ ክምችት ናት::

ራእይ 7:9:: «ከዚህም በኋላ አየሁ፤ እነሆ፤ በዙፋኑና በበጉ ፊት ማንም ሊቈጥራቸው የማይችል ከሕዝብ፣ ከነገድ፣ ከወገን፣ ከቋንቋም ሁሉ እጅግ ብዙ ሕዝብ ቆመው ነበር፤ እነርሱም ነጭ ልብስ ለብሰው፣ የዘንባባ ዝንጣፊ በእጃቸው ይዘው ነበር::»



# የቤተ ክርስቲያን ቅጣት (ተግሣጽ)

1. ተግሣጽ የሚጀምረው ራስን ከማስጠንቀቅ ነው::

ሮሜ 15:14:: ወንድሞቼ ሆይ፤ እናንተ ራሳችሁ በበጎነት የተሞላችሁ፣ በዕውቀት ሁሉ እንደ ተሞላችሁና አንዱ ሌላውን ለመምከር ችሎታ ያላችሁ መሆናችሁን እኔ ራሴ እርግጠኛ ሆኜ አለሁ::

ቈላ. 3:16:: «የክርስቶስ ቃል በሙላት ይኑርባችሁ፤ እርስ በርሳችሁ በጥበብ ሁሉ ተማማሩ፤ ተመካከሩ፤ በመዝሙርና በማሕሌት፣ በመንፈሳዊም ቅኔ በማመስገን በልባችሁ ለእግዚአብሔር ዘምሩ::»

2. የወደቀውን በገርነት መልሱት::

ገላ. 6:1:: «ወንድሞች ሆይ፤ አንድ ሰው በኀጢአት ውስጥ ገብቶ ቢገኝ፣ መንፈሳውያን የሆናችሁ እናንተ በገርነት ልትመልሱት ይገባል:: ነገር ግን አንተም እንዳትፈተን ራስህን ጠብቅ::»

3. የተሳሳተውን ኃጢአተኛ ለማዳን እሹ::

ያዕቆብ 5:19-20:: «ወንድሞቼ ሆይ፤ ከእናንተ አንዱ ከእውነት ቢስትና ሌላው ቢመልሰው፣ ይህን አስተውሉ፤ ኀጢአተኛን ከተሳሳተበት መንገድ የሚመልስ ሰው ነፍሱን ከሞት ያድነዋል፤ ብዙ ኀጢአትንም ይሸፍናል::»

4. ንስሐ የሚገባውን ሰው በይቅርታ አድሱት፤ ውደዱትም::

2ኛ ቆሮ. 2:7-8:: «ደግሞም ከልክ በላይ አዝኖ ተስፋ እንዳይቈርጥ፣ ይቅር ልትሉት ልታጽናኑት ይገባችኋል:: ስለዚህ አሁንም የምትወዱት መሆናችሁን እንድትገልጹለት እለምናችኋለሁ::

5. ንስሐ ከማይገባ ሰው ጋር አትተባበሩ::

1ኛ ቆሮ. 5:11 ነገር ግን አሁን የጻፍሁላችሁ፣ «ወንድም ነኝ» እያለ ከሚሴስን ወይም ከሚስገበገብ ወይም ጣዖትን ከሚያመልክ ወይም ከሚሳደብ ወይም ከሚሰክር ወይም ከሚቀማ ጋር እንዳትተባበሩ ነው፤ ከእንደዚህ ዐይነቱ ሰው ጋር ምግብ እንኳ

አትብሉ::

**6. ኢየሱስ የቤተ ክርስቲያን ቅጣትን ቅደም ተከተል ሰጥቶናል::**

ማቴ. 18:15-18:: «ወንድምህ ቢበድልህ ሄደህ አንተና እርሱ ብቻ ሆናችሁ ጥፋቱን ንገረው:: ቢሰማህ፣ ወንድምህን እንደ ገና የራስህ ታደርገዋለህ:: ባይሰማህ ግን ቃል ሁሉ በሁለት ወይም በሦስት ምስክሮች ፊት ስለሚጸና፣ አንድ ወይም ሁለት ሰው ይዘህ አነጋግረው:: እነርሱን ባይሰማ ለቤተ ክርስቲያን ንገር፤ ቤተ ክርስቲያንንም ባይሰማ እንደ አሕዛብና እንደ ቀረጥ ሰብሳቢ ቍጠረው:: እውነት እላችኋለሁ፤ በምድር ያሰራችሁት ሁሉ በሰማይ የታሰረ ይሆናል፤ በምድርም የፈታችሁት ሁሉ በሰማይ የተፈታ ይሆናል::»

**7. ክርስቶስ የመንግሥተ ሰማይን ቁልፍ ለቤተ ክርስቲያን ሰጥቷል::**

ማቴ. 16:19:: «የመንግሥተ ሰማይን መክፈቻዎች እሰጥሃለሁ፤ በምድር ያሰርኸው ሁሉ በሰማይ የታሰረ ይሆናል፤ በምድርም የፈታኸው ሁሉ በሰማይ የተፈታ ይሆናል::»

**8. አሮጌውን እርሾ አስወግዱት::**

1ኛ ቆሮ. 5:1-13::

**9. ማስወገድ አንዳንድ ጊዜ አስፈላጊ ነው::**

2ኛ ተሰ. 3:14:: «በዚህ መልእክት ላይ ላለው ቃላችን የማይታዘዝ ማንም ቢኖር:: እንደዚህ ያለውን ሰው በጥንቃቄ ተከታተሉት፤ በሥራውም እንዲያፍር ከእርሱ ጋር አትተባበሩ::»

**10. ኢየሱስ ቤተ ክርስቲያን በታማኝነት ሰዎችን ስለ ቀጣች ያመሰግናታል::**

ራእይ 2:2:: «ሥራህን፣ ጥረትህንና ትዕግሥትህን ዐውቃለሁ:: ክፉዎችንም ችላ ብለህ እንዳላለፍሃቸው፣ ሐዋርያትም ሳይሆኑ ሐዋርያት ነን የሚሉትንም መርምረህ ሐሰተኞች ሆነው እንዳገኘሃቸው ዐውቃለሁ::»



**11. ኢየሱስ፣ ሰዎችን ያልቀጣቸውን ቤተ ክርስቲያን ነቀፈ::**

ራእይ 2:14-16:: «ይሁን እንጂ የምነቅፍብህ ጥቂት ነገር አለኝ፤ የእስራኤል ልጆች ለጣዖት የተሠዋ ምግብ እንዲበሉና እንዲሴስኑ በፊታቸው መሰናከያ ያስቀምጥ ዘንድ ባላቅን ያስተማረውን የበለዓምን ትምህርት የሚከተሉ አንዳንድ ሰዎች በመካከልህ አሉ፤ የኒቆላውያንን ትምህርት የሚከተሉ ሰዎችም በአንተ ዘንድ አሉ:: ስለዚህ ንስሓ ግባ፤ አለዚያ ቶሎ እመጣብሃለሁ፤ በአፌም ሰይፍ እዋጋቸዋለሁ::»

# መጽናናት

በተጨማሪ ሞትን በገጽ 64፣ የኃጢአቶች ይቅርታን በገጽ 90፣ ጸሎትን በገጽ 166፤ የእግዚአብሔርን መጋቢነት በገጽ 176፣ እንዲሁም መታመንን በገጽ 224 ላይ ተመልከት::

1. እግዚአብሔር እረኛችን ነው፣ ሁልጊዜም በተሻለ መንገድ ይመራናል፣ ይጠብቀናልም::

    *መዝ. 23::*

2. ንስር ክንፎቿን ዘርግታ ከጫጩቷ በላይ እንደምትፋፋ፣ ልክ እንዲሁ እግዚአብሔር ለሕዝቡ ይጠነቀቃል::

    ዘዳ. 32:10-12:: «እርሱን በምድረ በዳ፣ ባዶና ጭው ባለ በረሓ ውስጥ አገኘው፤ ጋሻ ሆነው፤ ተጠነቀቀለትም፤ እንደ ዐይኑ ብሌን ጠበቀው:: ንስር ጐጆዋን በትና፣ በጫጩቶቿም ላይ እንደምትረብብ፣ እነርሱን ለመያዝ ክንፎቿን እንደምትዘረጋ፣ በክንፎቿም እንደምትሸከማቸው፣ እግዚአብሔር (ያህዌ) ብቻ መራው፤ ምንም ባዕድ አምላክ አብሮት አልነበረም::

3. አባት ለልጆቹ እንደሚጠነቀቅ፣ እንዲሁ እግዚአብሔር የራሱ ለሆኑት ይጠነቀቃል፤ የእግዚአብሔር ፍቅር ዘላለማዊ ነው::

    *መዝ. 103:8-18::*

4. እግዚአብሔር በእርሱ ለሚተማመኑት የዘወትር መጠለያ ይሆንላቸዋል::

    *መዝ. 91:1-2::* «በልዑል መጠጊያ የሚኖር፣ ሁሉን በሚችል አምላክ ጥላ ሥር ያድራል:: <u>እግዚአብሔርን</u>፣ «መጠጊያዬ፣ ምሽጌ፣ የምታመንብህ <u>አምላኬ</u>» እለዋለሁ::»

5. እግዚአብሔር በጣም በቀረበ ሁኔታ ያውቀናል፣ እኛንም በእጆቹ ያቅፈናል፣ ይመራናልም::

    *መዝ. 139:1-12::*

    *መዝ. 139:1-3::* «<u>እግዚአብሔር</u> ሆይ፤ መረመርኸኝ፤ ደግሞም ዐወቅኸኝ:: አንተ መቀመጤንና መነሣቴን ታውቃለህ፤ የልቤንም አሳብ ገና ከሩቁ ታስተውላለህ:: መሄድ መተኛቴን አጥርተህ ታውቃለህ፤ መንገዶቼንም ሁሉ ተረድተሃቸዋል::»

    *መዝ. 139:9-10::* «በንጋት ክንፍ ተነሥቼ ብበር፣ እስከ ባሕሩ ዳርቻ መጨረሻ ብሄድ፣ በዚያም ቢሆን እጅህ ትመራኛለች፤ ቀኝ እጅህም አጥብቃ ትይዘኛለች::»

6. ጻድቁ ሲቸገር፣ ኃጢአተኛው ግን ለጊዜው የተመቸው ይመስላል፤ ነገር ግን በእርግጠኝነት እግዚአብሔር በተሻለው መንገድ ይመራናል፤ በመገኘቱም ያጽናናል::

    *መዝ. 73::*

    *መዝ. 73:23-24::* «ይህም ሆኖ ዘወትር ከአንተ ጋር ነኝ፤ አንተም ቀኝ እጄን ይዘኸኛል:: በምክርህ መራኸኝ፤ ኋላም ወደ ክብር ታስገባኛለህ::»

7. የአሁኑ ጊዜ መከራ ከሚመጣው ክብር ጋር ሲነጻጸር ምንም አይደለም::

    ሮሜ 8:18:: «የአሁኑ ዘመን ሥቃያችን ወደ ፊት ሊገለጥ ካለው ለእኛ ከተጠበቀልን ክብር ጋር ሲነጻጸር ምንም እንዳይደለ እቈጥራለሁ::»

8. <u>እግዚአብሔር</u> ሁሉን ነገር ለበጐ ያደርገዋል::

    ሮሜ 8:28:: <u>«እግዚአብሔር</u>፣ ለሚወዱትና እንደ ሐሳቡ ለተጠሩት፣ ነገር ሁሉ ተያይዞ ለበጐ እንዲሠራ እንደሚያደርግላቸው እናውቃለን::

9. እግዚአብሔር ለእኛ ከሆነ ከፍቅሩ ምንም ነገር ሊለየን አይችልም::

    ሮሜ 8:31-39:: ሮሜ 8:31:: ታዲያ ለዚህ ምን እንመልሳለን? እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ከሆነ ማን ሊቃወመን ይችላል?

    ሮሜ 8:38-39:: ይህን ተረድቻለሁ፤ ሞትም ይሁን ሕይወት፣ መላእክትም ይሁን አጋንንት፣ ያለውም ይሁን የሚመጣው፣ ወይም ማንኛውም ኀይል፣ ከፍታም ይሁን ጥልቀት፣ ወይም የትኛውም

ፍጥረት፣ በጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ካለው ከእግዚአብሔር ፍቅር ሊለየን አይችልም።»

10. ኢየሱስ፣ መልካሙ እረኛ፣ ለበጐቹ ሲል ሞተ፤ እያንዳንዳቸውን ያውቃል። ይመራል እንዲሁም ይጠብቃቸዋል፤ የዘላለም ዋስትናን ይሰጠናል።

ዮሐ. 10:11። «መልካም እረኛ እኔ ነኝ፣ መልካም እረኛ ሕይወቱን ስለ በጐቹ አሳልፎ ይሰጣል፤»

ዮሐ. 10:14-15። መልካም እረኛ እኔ ነኝ፤ በጎቼን ዐውቃለሁ፤ እነርሱም ያውቁኛል፤ ይህም አብ እኔን እንደሚያውቀኝ እኔም አብን እንደማውቀው ነው። ሕይወቴንም ስለ በጎቼ አሳልፌ እሰጣለሁ።

ዮሐ. 10:27-29። በጎቼ ድምፄን ይሰማሉ፣ እኔ ዐውቃቸዋለሁ፤ እነርሱም ይከተሉኛል፤ እኔ የዘላለም ሕይወት እሰጣቸዋለሁ፤ ከቶ አይጠፉም፤ ከእጀም ሊነጥቃቸው የሚችል ማንም የለም። እነርሱን የሰጠኝ አባቴ ከሁሉ ይበልጣል።

11. ለሁሉም ፍላጐት የእግዚአብሔር ጸጋ በቂ ነው።

2ኛ ቆሮ. 9:8። «ሁልጊዜ በሁሉ ነገር የሚያስፈልጋችሁን ሁሉ አግኝታችሁ ለበጎ ሥራ ሁሉ እንድትተርፉ፣ እግዚአብሔር ጸጋን ሁሉ ሊያበዛላችሁ ይችላል።»

12. ጳውሎስ የሥጋው መውጊያ ነበረው፤ እግዚአብሔር ጸጋዬ ይበቃሃል ሲል ተስፋ ገባለት።

2ኛ ቆሮ. 12:7-10።

2ኛ ቆሮ. 12:9። እርሱ ግን፣ «ጸጋዬ ይበቃሃል፤ ኀይሌ ፍጹም የሚሆነው በድካም ጊዜ ነውና» አለኝ። ስለዚህ የክርስቶስ ኀይል በእኔ ያድር ዘንድ፣ ይበልጥ ደስ እያለኝ በድካሜ እመካለሁ።

13. ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱ እምነት ስለ ጉደላቸው ወቀሳቸውና ማዕበሉን ጸጥ አሰኘ።

ማቴ. 8:23-27።

14. እግዚአብሔር በማይለካው ጥበቡ ሁሉንም ነገር ይመራል፣ መንገዱም ከመታወቅ ያልፋል።

ሮሜ 11:33-36። «የእግዚአብሔር የጥበቡና የዕውቀቱ ባለጠግነት እንዴት ጥልቅ ነው! ፍርዱ አይመረመርም፤ ለመንገዱም ፈለግ የለውም! «የጌታን ልብ ያወቀ ማን ነው?» አማካሪውስ የነበረ ማን ነው?» እግዚአብሔር መልሶ እንደሰጠው፣ ለእግዚአብሔር ያበደረ ከቶ ማን ነው» ሁሉም ከእርሱ፣ በእርሱ፣ ለእርሱ ነውና፣ ለእርሱ ለዘላለም ክብር ይሁን፤ አሜን።»

15. አንድ ቀን ይህ የመከራ ሕይወት ያበቃና ሁሉም ነገር አዲስ ይሆናል።

ራእይ 21:1-4።

ራእይ 21:3-4። ደግሞም እንዲህ የሚል ታላቅ ድምፅ ከዙፋኑ ሲወጣ ሰማሁ፤ «እነሆ፤ የእግዚአብሔር ማደሪያ በሰዎች መካከል ነው፤ እርሱ ከእርሱ ጋር ይኖራል፤ እነርሱም ሕዝቡ ይሆናሉ፤ እግዚአብሔር ራሱም ከእነርሱ ጋር ይኖራል፤ አምላካቸውም የሆናል። እንባን ሁሉ ከዓይናቸው ያብሳል፤ ከእንግዲህ ወዲህ ሞት ወይም ኀዘን ወይም ልቅሶ ወይም ሥቃይ አይኖርም፤ የቀድሞው ሥርዓት አልፎአልናል።

16. ሸክምህን ሁሉ በጌታ ላይ ጣለው፣ ምክንያቱም እርሱ ይደግፍሃል።

መዝ. 55:22። «የከበደህን ነገር በእግዚአብሔር ላይ ጣል፤ እርሱ ደግፎ ይይዝሃል፤ የጻድቁንም መናወጥ ከቶ አይፈቅድም።

17. እግዚአብሔር የመጽናናት ሁሉ ምንጭ ነው።

2ኛ 2ኛ ቆሮ. 1:3-4። «የርኅራኄ አባት፣ የመጽናናትም ሁሉ አምላክ የሆነው የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ አምላክና አባት ይባረክ። እኛ ራሳችን ከእግዚአብሔር በተቀበልነው መጽናናት፣ በመከራ ያሉትን ማጽናናት እንድንችል፣ እርሱ በመከራችን ሁሉ ያጽናናል።»

18. እግዚአብሔር የማይለወጥ ታማኝ ነው።

መዝ. 89:1-8።

*መዝ.* 89:1-2:: «ስለ <u>እግዚአብሔር</u> ምሕረት ለዘላለም እዘምራለሁ፤ በአፌም ታማኝነትህን ከትውልድ እስከ ትውልድ እገልጻለሁ:: ምሕረትህን ለዘላለም እንደምትመሠርት፣ ታማኝነትህንም በሰማይ እንደምታጸና እናገራለሁና::

*መዝ.* 89:8:: የሰራዊት <u>አምላክ እግዚአብሔር</u> ሆይ፤ እንደ አንተ ያለ ማን ነው? <u>እግዚአብሔር ሆይ</u>፤ አንተ ኀያል ነህ፤ ታማኝነትህም ከብቦሃል::»

**19. እግዚአብሔር ሕዝቡን እንደ እረኛ ያሰማራል::**

ኢሳ. 40:10-11:: እነሆ፤ ልዑል <u>እግዚአብሔር</u> በኀይል ይመጣል፤ ክንዱ ስለ እርሱ ይገዛል:: እነሆ፤ ዋጋው ከእርሱ ጋር ነው፤ የሚከፋለውም ብድራት አብሮት አለ:: መንጋውን እንደ እረኛ ያሰማራል፤ ጠቦቶቹን በክንዱ ይሰበስባል፤ በዕቅፉም ይይዛቸዋል፤ የሚያጠቡትንም በጥንቃቄ ይመራል::

**20. የእግዚአብሔር ሞገስ እስከ ዕድሜ ልክ ይዘልቃል:: ለቅሶን ወደ ደስታ ይለውጣል::**

*መዝ.* 30:4-5:: «እናንተ ቅዱሳት፤ ለእግዚአብሔር ዘምሩ፤ ቅዱስ ስሙንም አወድሱ:: ቁጣው ለአጭር ጊዜ ነው፤ ቸርነቱ ግን እስከ ዕድሜ ልክ ነውና፤ ሌሊቱን በልቅሶ ቢታደርም፣ በማለዳ ደስታ ይመጣል::»

**21. እግዚአብሔር ፍላጐቶቻችሁን ሁሉ ለማሟላት የተሰጠ ነው::**

ፊል. 4:19:: <u>አምላኬም</u> እንደ ታላቅ ባለጠግነቱ መጠን የሚያስፈልጋችሁን ሁሉ በክርስቶስ ኢየሱስ ይሞላባችኋል::



# ተግባቦት፣ ሐሜት፣ ውሸት

**1. ዘማሪው ጥሩ የንግግር ጸሎት ምሳሌን ሰጥቶናል::**

*መዝ.* 19:14:: «መጠጊያዬና አዳኜ እግዚአብሔር ሆይ፤ የአፌ ቃልና የልቤ ሐሳብ፣ በፊትህ ያማረ ይሁን::»

*መዝ.* 141:3:: <u>«እግዚአብሔር</u> ሆይ፤ ለአፌ ጠባቂ አድርግ፤ የከንፈሮቼንም መዝጊያ ጠብቅ::»

**2. ትክክልና እውነተኛ የሆነውን ነገር ብቻ ለመናገር ቁረጥ::**

ምሳ. 8:6-8:: «የምንናገረው ጠቃሚ ነገር ስላለኝ አድምጡኝ፤ ቀና ነገር ለመናገር ከንፈሮቼን እከፍታለሁ:: አንደበቴ እውነትን ይናገራል፤ ከንፈሮቼ ክፋትን ይጸየፋሉና:: ከአንደበቴ የሚወጡት ቃሎች ሁሉ ጽድቅ ናቸው፤ አንዳቸውም ጠማማና ግራ የሚያጋቡ አይደሉም::»

**3. እውነትን በሚጐዳ መልኩ ሳይሆን፣ በፍቅር ተናገሩ::**

ኤፌ. 4:15:: «ይልቁንም እውነትን በፍቅር እየተናገርን፣ ራስ ወደ ሆነው ወደ እርሱ በነገር ሁሉ እናድጋለን፤ እርሱም ክርስቶስ ነው::»

ኤፌ. 4:29 :: «እንደ አስፈላጊነቱ ሌሎችን የሚያንጽና ለሚያምኑ የሚጠቅም ቃል እንጂ የማይረባ ቃል ከአፋችሁ አይውጣ::»

**4. ጐጂ ቃላትን አስወግዱ::**

ምሳ. 15:1:: «የለዘበ መልስ ቍጣን ያበርዳል፤ ክፉ ቃል ግን ቍጣን ይጭራል::»

**5. ለመስማት የፈጠናችሁ፣ ለመናገር የዘገያችሁ ሁኑ::**

*ያዕ.* 1:19:: «የተወደዳችሁ ወንድሞቼ ሆይ፤ ይህን አስተውሉ፤ ሰው ሁሉ ለመስማት የፈጠነ፣ ለመናገር የዘገየ፣ ለቍጣም የዘገየ ይሁን::»

*መክ.* 5:3-5:: «በሥራ ብዛት ሕልም እንደሚታይ፣ ብዙ ቃል

ባለበትም የሞኝ ንግግር ይገለጣል። ለእግዚአብሔር ስእለቱን በተሳልህ ጊዜ ለመፈጸም አትዘግይ፤ በሰነፎች ደስ አይለውምና፤ ስእለትህን ፈጽም። ስእለት ተስሎ ካለመፈጸም፣ አለመሳል ይሻላል።»

ምሳ. 10:19። «ከቃላት ብዛት ኀጢአት አይታጣም፤ አንደበቱን የሚገታ ግን ጠቢብ ነው።»

ምሳ. 15:28። «የጻድቅ ሰው ልብ የሚሰጠውን መልስ ያመዛዝናል፤ የክፉ ሰው አፍ ግን ክፋትን ያጉርፋል።»

ምሳ. 17:28። «አላዋቂ እንኳ ዝም ቢል ጠቢብ፣ አንደበቱንም ቢገዛ አስተዋይ ይመስላል።»

6. ከመናገርህ በፊት አድምጥ።

ምሳ. 18:13። «ከማዳመጡ አስቀድሞ የሚመልስ፣ ቂልነትና ዕፍረት ይሆንበታል።»

ምሳ. 29:20። «በችኮላ የሚናገርን ሰው ታያለህን? ከእርሱ ይልቅ ተላላ ተስፋ አለው።»

7. እግዚአብሔር እንዳንዋሽ ይከለክለናል፤ እውነትን እንድንናገር ይፈልጋል።

ዘፀ. 20:16። «በባልንጀራህ ላይ በሐሰት አትመስክር።»

ኤፌ. 4:25። «ስለዚህ ውሸትን አስወግዳችሁ፣ እያንዳንዳችሁ ከባልንጀራችሁ ጋር እውነትን ተነጋገሩ፤ ሁላችንም የአንድ አካል ብልቶች ነንና።»

8. እግዚአብሔር ውሸትን ይጸየፋል።

ምሳ. 12:22። «እግዚአብሔር ሐሰተኛ ከንፈር ይጸየፋል፤ በእውነተኞች ሰዎች ግን ደስ ይለዋል።»

መዝ. 34:11-14። «ልጆቼ ሆይ፣ ኑ፤ ስሙኝ፤ እግዚአብሔርን መፍራት አስተምራችኋለሁ። ሕይወትን የሚወድ፣ በጎውንም ያይ ዘንድ ዕድሜን የሚመኝ ማን ነው? አንደበትህን ከክፉ ነገር ከልክል፤ ከንፈርህንም ከሽንገላ ጠብቅ። ከክፉ ሽሽ፤ መልካሙንም አድርግ፤



ሰላምን ፈልጋት፤ ተከተላትም።»

9. ሁሉም ውሸት ከውሸት አባት ከሰይጣን የሚመጣ ነው።

ዮሐ. 8:44። «እናንተ የአባታችሁ የዲያብሎስ ናችሁ፤ የአባታችሁንም ፍላጎት ለመፈጸም ትሻላችሁ። እርሱ ከመጀመሪያ ነፍስ ገዳይ ነበር፤ በእርሱ ዘንድ እውነት ስለሌለ በእውነት አልጸናም፤ እርሱ ሐሰተኛ፣ የሐሰትም አባት በመሆኑ ሐሰትን ሲናገር፣ የሚናገረው ከራሱ አፍልቆ ነው፤»

10. መዋሸት ያስቀጣል።

ምሳ. 19:9። «ሐሰተኛ ምስክር ከቅጣት አያመልጥም፤ ውሸት የሚነዛም ይጠፋል።»

11. ጥንቃቄ በጐደለው አነጋገርና በሐሜት ጐረቤትህን አትጉዳው፤ አንደበትህን ተቆጣጠር።

ምሳ. 11:11-13። «በቅኖች በረከት ከተማ ከፍ ከፍ ትላለች፤ በክፉዎች አንደበት ግን ትጠፋለች። ማመዛዘን የጐደለው ሰው ባልንጀራውን ያንኳስሳል። አስተዋይ ግን አንደበቱን ይገዛል ሐሜተኛ ምሥጢር አይጠብቅም፤ ታማኝ ሰው ግን ምሥጢር ይጠብቃል።»

ምሳ. 12:18። «ግድ የለሽ ቃል እንደ ሰይፍ ይወጋል፤ የጠቢብ አንደበት ግን ፈውስን ያመጣል።»

ምሳ. 17:27-28። «ዐዋቂ ሰው ንግግሩ ቍጥብ ነው፤ አስተዋይም መንፈሱ የረጋ ነው። አላዋቂ እንኳ ዝም ቢል ጠቢብ፣ አንደበቱንም ቢገዛ አስተዋይ ይመስላል።»

ምሳ. 29:19። «አገልጋይ በቃል ብቻ ሊታረም አይችልም ቢያስተውለውም እንኳ በጅ አይልም።»

ምሳ. 21:23። «አንደበቱንና ምላሱን የሚቈጣጠር፣ ራሱን ከመቅሰፍት ይጠብቃል።»

12. አጥፊ ሊሆን ስለሚችል አንደበታችሁን ግሩ።

ያዕ. 3:1-12።

13. ጠብና ሐሜት እንዲቆሙ መርዳት አለብን።

ምሳ. 26:20:: «ዕንጨት ከሌለ እሳት ይጠፋል፤ አሾክሻኪ ከሌለም ጠብ ይበርዳል::»

14. ተጠንቀቁ:: በችኮላ አትናገሩ::

ምሳ. 13:3:: «አንደበቱን የሚጠብቅ ሕይወቱን ይጠብቃል፤ አፉ እንዳመጣለት የሚናገር ግን ይጠፋል::»

15. ለንቃት የተነገረ ቃልና የጥበብ ተግሣጽ ለሌሎች እጅግ ጠቃሚዎች ሊሆኑ ይችላሉ::

ምሳ. 25:11-12:: «ባግባቡ የተነገረ ቃል፣ በብር መደብ ላይ እንደ ተቀረጸ የወርቅ አንኮይ ነው::»

ምሳ. 15:4:: «ፈውስ የምታመጣ ምላስ የሕይወት ዛፍ ናት፤ አታላይ ምላስ ግን መንፈስን ትሰብራለች::»



# ኅሊና

1. በጐ ኅሊና ይኑራችሁ::

1ኛ ጴጥ. 3:15-16:: «ክርስቶስን ጌታ አድርጋችሁ በልባችሁ ቀድሱት:: እናንተ ስላላችሁ ተስፋ ምክንያትን ለሚጠይቋችሁ ሁሉ መልስ ለመስጠት ሁል ጊዜ የተዘጋጃችሁ ሁኑ፤ ነገር ግን ይህን ሁሉ በትሕትናና በአክብሮት አድርጉት፤ በክርስቶስ ያላችሁን መልካም ጠባይ አክፋፍተው የሚናገሩ ሰዎች በሐሜታቸው እንዲያፍሩ በጎ ኅሊና ይኑራችሁ::»

2. በእግዚአብሔርና በሰዎች መካከል በጎ ኅሊና ይኑራችሁ::

የሐዋ. 24:16:: «ስለዚህ በእግዚአብሔርና በሰው ፊት ንጹሕ ኅሊና እንዲኖረኝ ሁልጊዜ እጥራለሁ::»

3. የእምነትን እውነት ያዙ::

1ኛ ጢሞ. 3:9:: «የእምነትንም ጥልቅ ምሥጢር በንጹሕ ኅሊና መጠበቅ አለባቸው::»

4. ኅሊና ሊደነዝዝ ይችላል::

1ኛ ጢሞ 4:2:: «እንዲህ ያለው ትምህርት የሚመጣው ኅሊናቸው በጋለ ብረት የተጠበሰ ያህል ከደነዘዘባቸው ግብዝ ውሸተኞች ነው::»

5. በጐ ኅሊና ኖራችሁ በልባችሁ ልታርፉ ትችላላችሁ::

ምሳ. 3:21-26:: «ልጄ ሆይ፤ ትክክለኛ ፍርድንና አስተውሎ መለየትን ጠብቅ፤ እነዚህ ከእይታህ አይራቁ፤ ለነፍስህ ሕይወት፣ ለአንገትህም ጌጥ ይሆናሉ:: ከዚያም መንገድህን በሰላም ትሄዳለህ፤ እግርህም አይሰናከልም፤ ስትተኛ አትፈራም፤ ትተኛለህ እንቅልፍህም ጣፋጭ ይሆናል:: ድንገተኛን መከራ፣ በክፉዎች ላይ የሚደርሰውንም ጥፋት አትፍራ፤ እግዚአብሔር መታመኛህ ይሆናልና፤ እግርህንም በወጥመድ ከመያዝ ይጠብቅሃል::»

6. ክርስቶስ በጐ ኅሊናን ሊሰጣችሁ ይችላል::

ዕብ. 9:14:: «በዘላለም መንፈስ አማካይነት ራሱን ነውር አልባ

መሥዋዕት አድርጎ ለእግዚአብሔር ያቀረበው የክርስቶስ ደም ሕያው እግዚአብሔርን እንድናመልክ ኅሊናችንን ከምውት ሥራ እንዴት ይበልጥ ያነጻ ይሆን!»

7. ክፉ ኅሊና ሊነጻ ይችላል::

ዕብ. 10:22:: «ከክፉ ኅሊና ለመንጻት ልባችንን ተረጭተን፣ ሰውነታችንንም በንጹሕ ውሃ ታጥበን፣ በእውነተኛ ልብና በሙሉ እምነት ወደ እግዚአብሔር እንቅረብ::»



# እርካታ፣ ምኞት፣ ቀዳሚ ነገሮች

ማስታወሻ:- መርካት ማለት እግዚአብሔር በጸጋው በጥበቡ የወሰነልንን ነገር በእምነት፣ በምስጋና ልብና በመገዛት መንፈስ መቀበል ማለት ነው::

1. በእርካታ ጋር ያለ መንፈሳዊነት ታላቅ ትርፍ ነው::

1ኛ ጢሞ. 6:6:: ነገር ግን እውነተኛ መንፈሳዊነት ባለን ነገር ከመርካት ጋር ትልቅ ትርፍ ነው::

2. የገንዘብ ፍቅር ችግርን ያመጣልና መርካትን ተማሩ::

1ኛ ጢሞ. 6:7-10:: «ምክንያቱም ወደ ዓለም ያመጣነው ምንም ነገር የለም፤ ምንም ነገር ይዘን መሄድም አንችልም:: ነገር ግን ምግብና ልብስ ካለን፣ ያ ይበቃናል:: ባለጠጋ ለመሆን የሚፈልጉ ግን ወደ ፈተናና ወደ ወጥመድ፣ እንዲሁም ሰዎችን ወደ ማፍረስና ወደ ጥፋት ወደሚያዘቅጠው ወደ ብዙ ከንቱና ክፉ ምኞት ይወድቃሉ:: ምክንያቱም የገንዘብ ፍቅር የክፋት ሁሉ ሥር ነው፤ አንዳንዶች ባለጠጋ ለመሆን ካላቸው ጉጉት የተነሣ ከእምነት መንገድ ስተው ሄደዋል፣ ራሳቸውን በብዙ ሥቃይ ወግተዋል::»

3. ከገንዘብ ፍቅር ነፃ ሁኑ፣ እርካታም ይኑራችሁ::

ዕብ. 13:5:: ራሳችሁን ከፍቅረ ንዋይ ጠብቁ፤ ባላችሁ ነገር ረክታችሁ ኑሩ፤ ምክንያቱም እግዚአብሔር፣ «ከቶ አልተውህም፤ በፍጹም አልጥልህም» ብሎአል::»

4. ጳውሎስ እጅግ ከባድ በሆኑ የሕይወት ሁኔታዎች ውስጥ እንኳን እርካታን ተምሯል::

ፊል. 4:11-13:: «ይህን የምለው ስለቸገረኝ አይደለም፤ ምክንያቱም በማንኛውም ሁኔታ ውስጥ ያለኝ ይበቃኛል ማለትን ተምሬአለሁ፤ ማጣትን ዐውቃለሁ፤ ማግኘትንም ዐውቀዋለሁ:: ብጠግብም ሆነ ብራብም፤ ባገኝም ሆነ ባጣ በማንኛውም ሆነ በየትኛውም ሁኔታ ያለኝ ይበቃኛል የማለትን ምስጢር ተረድቻለሁ:: ኀይልን በሚሰጠኝ በእርሱ ሁሉን ማድረግ እችላለሁ::»

5. እርካታ ሰላምን ያጐለብታል::

ምሳ. 17:1:: «ጠብ እያለ ግብዣ ከሞላበት ቤት ይልቅ፣ በሰላምና በጸጥታ የእንጀራ ድርቆሽ ይሻላል::»

6. የሰው ሕይወት ባለው ንብረት ላይ የተመሠረተ አይደለም::

ሉቃ. 12:15:: ደግሞም፣ «የሰው ሕይወቱ በሀብቱ ብዛት የተመሠረተ ስላልሆነ፣ ተጠንቀቁ፤ ከስግብግብነትም ሁሉ ራሳችሁን ጠብቁ» አላቸው::

7. የሀብታሙ ሞኝ ምሳሌ ሕይወት ከቁሳዊ ሀብት እንደሚበልጥ ያስተምራል::

*ሉቃ. 12:16-21:: (ሀብታሙ ሞኝ ለራሱ ብዙ ነገሮችን ሰበሰበ፤ ነገር ግን በእግዚአብሔር ነገር ሀብታም አልነበረም:: ስለዚህም ሕይወቱ ይጠይቀው ነበር::)*

8. የሀብት ማባበል ዓለምን እንዲያስጨንቃት አትፍቀዱለት::

ማር. 4:1-20 (የዘሪው ምሳሌ)::

ማር. 4:7፣ 18-20:: «ሌላው ዘር ደግሞ በእሾኽ መካከል ወደቀ፤ እሾኹም አድጎ የዘሩን ተክል ስላነቀው ፍሬ አላፈራም::. . . ሌሎቹ (ሰዎች) ደግሞ በእሾኽ መካከል የተዘራውን ዘር ይመስላሉ፤ ቃሉን መስማት ይሰማሉ፤ ነገር ግን የዚህ ዓለም ውጣ ውረድ፣ የሀብት አንጊነት እንዲሁም የሌሎች ነገሮች ምኞት ቃሉን አንቀው በመያዝ ፍሬ እንዳያፈራ ያደርጉታል::»

9. ምኞትን ግደሉ::

ቈላ. 3:5:: «ስለዚህ ምድራዊ ምኞቶቻችሁን ግደሉ፤ እነዚህም:- ዝሙት፣ ርኵሰት፣ ፍትወት፣ ክፉ ምኞትና አምልኮተ ጣዖት የሆነው መጐምጀት ናቸው::»

10. ምደራዊ መዝገብ አታከማቹ፣ ነገር ግን ሰማያዊ መዝገብን አከማቹ::

ማቴ. 6:19-20:: «ብል ሊበላው፣ ዝገት ሊያበላሸው፣ ሌባም ቈፍሮ ሊሰርቀው በሚችሉበት በዚህ ምድር ላይ ለራሳችሁ ሀብት አታከማቹ:: ነገር ግን ብል ሊበላው፣ ዝገት ሊያበላሸው፣ ሌባም



ቈፍሮ ሊሰርቀው በማይችለበት በዚያ በሰማይ ለራሳችሁ ሀብት አከማቹ፤ ሀብትህ ባለበት ልብህም በዚያው ይሆናልና::»

11. በአንድ ጊዜ ሁለት ጌቶችን ማገልገል አትችሉም::

ማቴ. 6:24:: «አንድ ሰው ሁለት ጌቶችን ማገልገል አይችልም፤ አንዱን ጠልቶ ሌላውን ይወዳል፤ ወይም አንዱን አክብሮ ሌላውን ይንቃል:: እግዚአብሔርንና ገንዘብን በአንድነት ማገልገል አይቻልም::»

12. አስቀድማችሁ የእግዚአብሔርን መንግሥት ፈልጉ::

ማቴ. 6:33:: «ከሁሉ አስቀድማችሁ ግን የእግዚአብሔርን መንግሥትና ጽድቅ እሹ፤ እነዚህ ሁሉ ይጨመሩላችኋል::»

13. ደቀ መዛሙርቱ እንዳደረጉት፣ የክብርን ቦታ አትፈልጉ::

ሉቃ. 9:46-48:: «ከእነርሱ ማን እንደሚበልጥ በደቀ መዛሙርቱ መካከል ክርክር ተነሣ:: ኢየሱስም የልባቸውን ሐሳብ ተረድቶ፣ አንድ ሕፃን ይዞ በአጠገቡ ቆመ፤ እንዲህም አላቸው፤ «ይህን ሕፃን በስሜ የሚቀበል ማንም ቢኖር እኔን ይቀበላል፤ እኔን የሚቀበል ደግሞ የላከኝን ይቀበላል፤ ከሁላችሁ የሚያንስ እርሱ ከሁሉ ይበልጣልና::»

14. ሀብት ኖሮ በቤት ውስጥ መለያየት ከሚሆን ይልቅ ቀለል ያለ ኑሮ መኖር ይሻላል::

ምሳ. 15:16-17:: «እግዚአብሔርን ከመፍራት ጋር ያለ ጥቂት ነገር፣ ሁከት ካለበት ትልቅ ሀብት ይበልጣል:: ፍቅር ባለበት ጐመን መብላት፣ ጥላቻ ባለበት የሰባ ፍሪዳ ከመብላት ይሻላል::»

ምሳ. 17:1:: «ጠብ እያለ ግብዣ ከሞላበት ቤት ይልቅ በሰላምና በጸጥታ የእንጀራ ድርቆሽ ይሻላል::»

15. ለሀብት ስትል ራስህን አታድክም::

ምሳ. 23:4-5:: «ሀብት ለማግኘት ስትል ራስህን አታድክም፤ ሐሳብህን የመግታት ጥበብ ይኑርህ:: በሀብት ላይ ዐይንህን ብትጥል፤ ወዲያው ይጠፋል፤ ወደ ሰማይ እንደሚበርር ንስር፣ በርግጥ ክንፍ

ለውጥቶ ይበራል::»

ምሳ. 28:6:: «በአካሄዱ ነውር የሌለበት ድኻ፣ መንገዱ ጠማማ ከሆነ ባለጠጋ ይሻላል::»

መክ. 4:6:: በድካምና ነፋስን በመከተል ከሚገኝ ሁለት ዕፍኝ ይልቅ፣ በርጋታ የሚገኝ አንድ ዕፍኝ ይሻላል::

16. ሀብትንም ሆነ ድኽነትን አትፈልግ::

ምሳ. 30:8-9:: «ሐሰትንና ሐሰት መናገርን ከእኔ አርቅልኝ፤ ድኽነትንም ሆነ ብልጽግናን አትስጠኝ፤ ብቻ የዕለት እንጀራዬን ስጠኝ:: ያለዚያ ግን ያለ ልክ እጠግብና እክድሃለሁ፤ እግዚአብሔር ማን ነው? እላለሁ፤ ወይም ድኻ እሆንና እሰርቃለሁ፤ የአምላኬንም ስም አሰድባለሁ::»

17. ሀብት ከማከማቸት ይልቅ ጠቢብ መሆን ይሻላል::

ምሳ. 16:16-17:: «ከወርቅ ይልቅ ጥበብን ማግኘት፣ ከብርም ማስተዋልን መምረጥ ምንኛ ይበልጣል! የቅኖች ጐዳና ከክፋት የራቀ ነው፤ መ[illegible]ዱንም የሚጠብቅ ሕይወቱን ይጠብቃል::

18. መልካም ስም ከብዙ ሀብት ይልቅ ተፈላጊ ነው::

ምሳ. 22:1:: መልካም ስም ከብዙ ብልጽግና ይመረጣል፤ መከበርም ከብርና ከወርቅ ይበልጣል::

19. የንጉሥ አክአብ ያልተመረመረ ምኞት በስተመጨረሻ ወደ ግድያ ተግባር መራው::

1ኛ ነገ. 21:1-14::

1ኛ ነገ. 21:2-4:: አክዓብም ናቡቴን፣ «የወይን ተክል ቦታህ ከቤተ መንግሥቴ አጠገብ ስለ ሆነ፣ የአትክልት ቦታ እንዳደርገው ልቀቅልኝ፤ በምትኩ ከዚህ የበለጠ የወይን ተክል ቦታ እሰጥሃለሁ፤ የተሻለ ሆኖ ከታየህም የሚያወጣውን ገንዘብ እከፍልሃለሁ» አለው:: ናቡቴ ግን፣ «ዐፅመ ርስቴን እለቅልህ ዘንድ እግዚአብሔር አይበለው» ሲል መለሰለት:: ኢይዝራኤላዊው ናቡቴ፣ «ዐፅመ ርስቴን አልለቅልህም» ስላለው፣ አክዓብ ተበሳጭቶና ተቈጥቶ ወደ ቤቱ



ገባ፤ አኩርፎም በዐልጋው ላይ ተኛ፤ ምግብም መብላት ተወ::

20. ንጉሥ ሕዝቅያስ ማስቀደም የነበረበትን አስከተለ:: በትዕቢትም ምድራዊ ሀብቱን አሳየ፣ በዚህም ምክንያት ተፈረደበት::

2ኛ ነገ. 20:12-19::

2ኛ ነገ. 20:14-19:: ከዚያም ነቢዩ ኢሳይያስ ወደ ሕዝቅያስ ሄዶ፣ «እነዚያ ሰዎች ምን አሉህ? የመጡትስ ከወዴት ነው?» ሲል ጠየቀው:: ሕዝቂያስም መልሶ፣ «የመጡት ከሩቅ አገር ከባቢሎን ነው» አለው:: ነቢዩም፣ «በቤተ መንግሥትህ ምን ምን አዩ?» ሲል ጠየቀው:: ሕዝቅያስም፣ «በቤተ መንግሥቴ ያለውን ሁሉ አይተዋል፤ በግምጃ ቤቶቼ ሳላሳያቸው የቀረ ምንም ነገር የለም» አለ:: ከዚያም ኢሳይያስ ሕዝቅያስን እንዲህ አለው፤ «የእግዚአብሔርን ቃል ስማ፤ በቤተ መንግሥትህ ያለው ሁሉ አባቶችህም እስከ ዛሬ ድረስ ያከማቹት በሙሉ ወደ ባቢሎን የሚወሰድበት ጊዜ በርግጥ ይመጣል፤ አንዳች የሚቀር ነገር የለም ይላል እግዚአብሔር:: የሥጋህ ቁራጭ የአጥንትህ ፍላጭ ከሚሆኑት፣ ከምትወልዳቸው ልጆች አንዳንዶቹ በምርኮ ይወሰዳሉ፤ በባቢሎንም ቤተ መንግሥት ጃንደረቦች ይሆናሉ::» ሕዝቅያስም፣ «የተናገርኸው የእግዚአብሔር ቃል መልካም ነው» ሲል መለሰ፤ «እኔ እስካለሁ ድረስ ሰላምና ጸጥታ ከተገኘ የሆነው ይሁን» ብሎ አሰበአልና::

21. ዕንባቆም በእግዚአብሔር መንገድ ረክቷል:: እንዲሁም ሁኔታዎች ከባድ የሆኑ በመሰሉ ጊዜም እንኳ በእርሱ ታምኗል::

ዕን. 3:17-19:: «ምንም እንኳ የበለስ ዛፍ ባያፈራ፣ ከወይን ተክልም ፍሬ ባይገኝ፣ የወይራም ዛፍ ፍሬ ባይሰጥ፣ ዕርሻዎችም ሰብል ባይሰጡ፣ የበጎች ጕረኖ እንኳ ባዶውን ቢቀር፣ ላሞችም በበረት ውስጥ ባይገኙ፣ እኔ ግን በእግዚአብሔር ደስ ይለኛል፤ በድነቴ አምላክ ሐሤት አደርጋለሁ:: ጌታ እግዚአብሔር ኀይሌ ነው፤ እግሮቼን እንደ ዋላ እግሮች ያደርጋል፤ በከፍታዎችም ላይ ያስሄደኛል::»

22. እግዚአብሔር ስለ ምኞቱ ግያዝን ክፉኛ ቀጣው፡፡

2ኛ ነገ. 5፡19-27፡፡ (ግያዝ በማታለል ከንዕማን ስጦታን አገኘ፡፡)

2ኛ ነገ. 5፡19-20፡፡ «ኤልሳዕም፣ «በሰላም ሂድ» አለው፡፡ ንዕማንም ጥቂት ራቅ ብሎ እንደ ሄደ፣ የእግዚአብሔር ሰው አገልጋይ ግያዝ፣ «ጌታዬ፣ ይህ ሶርያዊ ንዕማን ያመጣውን ባለመቀበል በነጻ ሰደደው፤ ሕያው እግዚአብሔርን! ተከትዬ ሄጄ ከእርሱ አንድ ነገር ማግኘት አለብኝ» ብሎ አሰበ፡፡

2ኛ ነገ. 5፡27፡፡ ስለዚህ የንዕማን ለምጽ በአንተ ላይ ይጣበቃል፤ ለዘላለምም ወደ ዘርህ ይተላለፋል፡፡ ከዚያም ግያዝ ከኤልሳዕ ፊት ወጣ፤ እንደ በረዶ እስኪነጣም ድረስ ለምፃም ሆኖ ወጣ፡፡

23. ሀብት ትርጉም የለሽ ነው፤ ብልጽግናም ብልጭታ ነው፡፡

መክ. 5፡8-17፡፡

መክ. 5፡10-11፡፡ «ገንዘብን የሚወድ፣ ገንዘብ አይበቃውም፤ ብልጽግናም የሚወድ፣ በትርፉ አይረካም፤ ይህም ከንቱ ነው፡፡ ሀብት በበዛ ቍጥር፣ ተጠቃሚውም ይበዛል፤ በዐይኑ ብቻ ከማየት በቀር ታዲያ፣ ለባለቤቱ ምን ይጠቅመዋል?»

መክ. 5፡15-17፡፡ «ሰው ከእናቱ ማሕፀን ዕራቍቱን ይወለዳል፤ እንደ መጣው እንዲሁ ይመለሳል፡፡ ከለፋበትም ነገር፣ አንድም እንኳ በእጁ ይዞ ሊሄድ አይችልም፡፡ ይህ ደግሞ እጅግ ክፉ ነገር ነው፤ ሰው እንደ መጣ እንዲሁ ይሄዳል፤ የሚደክመው ለነፋስ ስለ ሆነ፣ ትርፉ ምንድን ነው? በብዙ ጭንቀት፣ መከራና ብስጭት፣ ዘመኑን ሁሉ በጨለማ ውስጥ ይበላል፡፡»

24. በሕይወት ውስጥ ቀዳሚው ግብ እግዚአብሔርን መፍራትና ትእዛዙንም መጠበቅ መሆን ይኖርበታል፡፡

መክ. 12፡13-14፡፡ «እነሆ፣ ሁሉ ነገር ከተሰማ ዘንድ፣ የነገሩ ሁሉ ድምዳሜ ይህ ነው፤ እግዚአብሔርን ፍራ፤ ትእዛዛቱንም ጠብቅ፤ ይህ የሰው ሁለንተናዊ ተግባሩ ነውና፡፡ መልካምም ይሁን ክፉ፣ ስውር የሆነውን ነገር ሁሉ አንድ ሳይቀር፣ ማንኛውንም ሥራ እግዚአብሔር ወደ ፍርድ ያመጣዋልና፡፡»



ማቴ. 6፡33፡፡ «ከሁሉ አስቀድማችሁ ግን የእግዚአብሔርን መንግሥትና ጽድቁን እሹ፤ እነዚህ ሁሉ ይጨመሩላችኋል፡፡»

25. አሁን የሚታየው ነገር የጊዜው ነው፣ የማይታየው ግን የዘላለም ነው፡፡

2ኛ ቆሮ. 4፡18፡፡ ስለዚህ ዐይናችን የሚያተኵረው በሚታየው ነገር ላይ ሳይሆን በማይታየው ላይ ነው፤ የሚታየው ጊዜያዊ ነውና፤ የማይታየው ግን ዘላለማዊ ነው፡፡

26. አሳባችሁን በላይኛዎቹ ነገሮች ላይ አድርጉ እንጂ በምድራዊ ነገሮች ላይ አታድርጉ፡፡

ቈላ. 3፡1-3፡፡ እንግዲህ ከክርስቶስ ጋር ከተነሣችሁ፣ ክርስቶስ በእግዚአብሔር ቀኝ በተቀመጠበት በላይ ያሉ ነገሮችን እሹ፤ አሳባችሁም በላይ ባለው ላይ እንጂ በምድራዊ ነገር ላይ አይሁን፡፡ ሞታችኋልና፤ ሕይወታችሁም ከክርስቶስ ጋር በእግዚአብሔር ዘንድ ተሰውሮአልና፡፡

27. ጻድቅ ከመመኘት ይልቅ ነጻነትን ለመስጠት የተዘጋጀ ነው፡፡

ምሳ. 21፡6፡፡ «በሐሰተኛ አንደበት የተገኘ ሀብት፣ በኖ የሚጠፋበትን ለሞትም የሚያበቃ ወጥመድ ነው፡፡»

# ሞት፣ የዘላለም ሕይወት

የልጆችን ሞት በተመለከተ፣ በተጨማሪ ልጆች የሚለውን በገጽ 35 ላይ ተመልከቱ።

1. ሞትን ያለፍርሃት ልትጋፈጡ ትችላላችሁ።

መዝ. 23:4። «በሞት ጥላ ሸለቆ ውስጥ፤ ብሄድ እንኳ፣ አንተ ከእኔ ጋር ስለ ሆንህ፣ ክፉን አልፈራም፤ በትርህና ምርኩዝህ፣ እነርሱ ያጽናኑኛል።»

2. አማኝ ለዘላለም በእግዚአብሔር ቤት ይኖራል።

መዝ. 23:6። «በሕይወቴ ዘመን ሁሉ፣ በጎነትና ምሕረት በእርግጥ ይከተሉኛል፤ እኔም በእግዚአብሔር ቤት፣ ለዘላለም እኖራለሁ።»

ዮሐ. 14:1-4። «ልባችሁ አይጨነቅ፤ በእግዚአብሔር እመኑ፤ በእኔም ደግሞ እመኑ። በአባቴ ቤት ብዙ መኖሪያ አለ፤ ይህ ባይሆንማ ኖሮ እነግራችሁ ነበር፤ የምሄደውም ስፍራ ላዘጋጅላችሁ ነው። ሄጄም ስፍራ ካዘጋጀሁላችሁ በኋላ፣ እኔ ባለሁበት እናንተም ከእኔ ጋር እንድትሆኑ ልወስዳችሁ ዳግመኛ እመጣለሁ። እኔ ወደምሄድበትም ስፍራ የሚያደርሰውን መንገድ ታውቃላችሁ።»

3. ሕይወት ክርስቶስ ነው፣ ሞትም ጥቅም ነው።

ፊል. 1:21። «ለእኔ፣ መኖር ክርስቶስ ነው፤ ሞትም ማትረፍ ነው።»

4. ጳውሎስ እዚህ መኖርን፣ እንዲሁም ከጌታ ጋር ለመሆን ወደ ቤት ለመሄድ ያውም ወደ ተሻለው ቦታ ለመሄድ ፈለገ።

ፊል. 1:22-26።

ፊል. 1:23-24። «በእነዚህ በሁለቱ እጨነቃለሁ፤ ልሄድ፣ ከክርስቶስም ጋር ልሆን እናፍቃለሁ፤ ይህ እጅግ የተሻለ ነውና። ነገር ግን በሥጋ መኖሬ ለእናንተ ይበልጥ አስፈላጊ ነው።»

5. የእግዚአብሔር ምርጦች ሞት የከበረ ነው።

መዝ. 116:15። «የቅዱሳኑ ሞት፣ በእግዚአብሔር ፊት የተከበረ ነው።»



6. በጌታ የሞቱ ቅዱሳን ናቸው።

ራእይ 14:13። «ከዚያም፣ «ከእንግዲህ ወዲህ በጌታ ሆነው የሚሞቱ ብፁዓን ናቸው ብለህ ጻፍ» የሚል ድምፅ ከሰማይ ሰማሁ። መንፈስም፣ «አዎ፣ ሥራቸው ስለሚከተላቸው ከድካማቸው ያርፋሉ» ይላል።

7. የሞቱትንና በኢየሱስ ሆነው ያንቀላፉትን ሰዎች በተመለከተ መጽናናትን ልታገኝ ትችላለህ።

1ኛ ተሰ. 4:13-18።

1ኛ ተሰ. 4:16-18። ጌታ ራሱ በታላቅ ትእዛዝ፣ በመላእክት አለቃ ድምፅና በእግዚአብሔር የመለከት ድምፅ ከሰማይ ይወርዳልና። በክርስቶስ የሞቱትም አስቀድመው ይነሣሉ። ከዚያም በኋላ እኛ የቀረነው፣ በሕይወትም የምንኖረው ጌታን በአየር ላይ ለመቀበል ከእነርሱ ጋር በደመና እንነጠቃለን፤ በዚህም መሠረት ለዘላለም ከጌታ ጋር እንሆናለን። ስለዚህ በዚህ ቃል እርስ በርሳችሁ ተጽናኑ።

8. የሞቱ አማኞች ከሥጋው ተለይተው ይኖራሉ፣ ነገር ግን ከጌታ ጋር በቤቱ ናቸው።

2ኛ ቆሮ. 5:1-8። *(በሰማያዊ ማረፊያችን)*

2ኛ ቆሮ. 5:6-8። «ስለዚህ ሁልጊዜ በመታመን እንኖራለን፤ በሥጋ እስካለን ድረስ ከጌታ ርቀን እንደምንገኝ እናውቃለን፤ ምክንያቱም የምንኖረው በእምነት እንጂ በማየት አይደለም። ከሥጋ ተለይተን ከጌታ ጋር መኖርን እንደምንመርጥ እርግጠኛ ሆኜ እናገራለሁ።»

9. በሕይወትም ሆነ በሞት እኛ የጌታ ነን።

ሮሜ 14:8። «ብንኖር ለጌታ እንኖራለን፤ ብንሞትም ለጌታ እንሞታለን፤ ስለዚህ ብንኖርም ብንሞትም የጌታ ነን።»

10. ኢየሱስ፣ አልአዛር ከሞተ በኋላ ማርታንና ማርያምን አጽናናቸው። እርሱ ትንሣኤና ሕይወት ነው።

ዮሐ. 11:17-26::

ዮሐ. 11:23-26:: ኢየሱስም፣ «ወንድምሽ ይነሣል» አላት:: ማርታም፣ «በመጨረሻው ቀን፣ በትንሣኤ እንደሚነሣ ዐውቃለሁ» አለችው:: ኢየሱስም እንዲህ አላት፤ «ትንሣኤና ሕይወት እኔ ነኝ፤ በእኔ የሚያምን ቢሞት እንኳ በሕይወት ይኖራል፤ በእኔ የሚኖር፣ የሚያምንብኝም ከቶ አይሞትም፤ ይህን ታምኚለሽን?»

11. የሚጠፋው የማይጠፋውን ይለብሳል፤ ሞትም ድል በመነሣት ይዋጣል::

1ኛ ቆሮ. 15:54-57:: የሚጠፋው የማይጠፋውን፣ የሚሞተውም የማይሞተውን በሚለብስበት ጊዜ፣ «ሞት በድል ተዋጠ» ተብሎ የተጻፈው ቃል ይፈጸማል:: እንዲሁም፣ «ሞት ሆይ፣ ድል መንሣትህ የት አለ? ሞት ሆይ መንደፊያህስ የት አለ?» የሞት መንደፊያ ኀጢአት ነው፤ የኀጢአትም ኀይል ሕግ ነው:: ነገር ግን በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል ድልን ለሚሰጠን ለእግዚአብሔር ምስጋና ይሁን::

12. አማኞች ከክርስቶስ ጋር ወራሾች ናቸው::

ሮሜ 8:16-17:: «የእግዚአብሔር ልጆች መሆናችንን ያ መንፈስ ራሱ ከመንፈሳችን ጋር ሆኖ ይመሰክርልናል:: ልጆች ከሆን ወራሾች ደግሞ ነን፤ የክብሩ ተካፋዮች እንሆን ዘንድ በእርግጥ የመከራው ተካፋዮች ብንሆን፣ የእግዚአብሔር ወራሾች፣ ከክርስቶስ ጋር አብረን ወራሾች ነን::»

13. ሞትም እንኳን ቢሆን፣ ምንም ነገር ከእግዚአብሔር ፍቅር ሊለየን አይችልም::

ሮሜ 8:35-39::

ሮሜ 8:38-39:: «ይህን ተረድቻለሁ፤ ሞትም ይሁን ሕይወት፣ መላእክትም ይሁኑ አጋንንት፣ ያለውም ይሁን የሚመጣው፣ ወይም ማንኛውም ኀይል፣ ከፍታም ይሁን ጥልቀት፣ ወይም የትኛውም ፍጥረት፣ በጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ካለው ከእግዚአብሔር ፍቅር ሊለየን አይችልም::»



14. ዳዊት፣ ሕፃን ልጁ ሲሞትበት፣ አንድ ቀን ወደ እርሱ እንደሚሄድ በማወቁ ተጽናና::

2ኛ ሳሙ. 12:18-23::

2ኛ ሳሙ. 12:23:: «አሁን ግን ሕፃኑ ስለ ሞተ፣ የምጾመው ለምንድን ነው? መልሼ ላመጣው እችላለሁን? እኔ ወደ እርሱ እሄዳለሁ እንጂ፣ እርሱ ወደ እኔ አይመለስ!»

15. መልካሙ እረኛ ኢየሱስ ነፍሱን ለበጎቹ አኖረ::

ዮሐ. 10:14-15:: «መልካም እረኛ እኔ ነኝ፤ በጎቼን ዐውቃለሁ፤ እነርሱም ያውቁኛል፤ ይህም አብ እኔን እንደሚያውቀኝ እኔም አብን እንደማውቀው ነው:: ሕይወቴንም ስለ በጎቼ አሳልፌ እሰጣለሁ::»

16. የኢየሱስ በጎች ድምፁን ሰምተው ይከተሉታል፣ እርሱም የዘላለምን ሕይወት ይሰጣቸዋል:: ማንም ከእጁ ነጥቆ ሊወስዳቸው አይችልም::

ዮሐ. 10:27-30:: «በጎቼ ድምፄን ይሰማሉ፤ እኔ ዐውቃቸዋለሁ፤ እነርሱም ይከተሉኛል፤ እኔ የዘላለም ሕይወት እሰጣቸዋለሁ፤ ከቶ አይጠፉም፤ ከእጄም ሊነጥቃቸው የሚችል ማንም የለም:: እነርሱን የሰጠኝ አባቴ ከሁሉ ይበልጣል፤ ከአባቴም እጅ ማንም ሊነጥቃቸው አይችልም:: እኔና አብ አንድ ነን::»

17. በውስጣቸው መከራም ሆነ ኀዘን የማይኖርባቸው አዲስ ሰማይና አዲስ ምድር ይኖራሉ::

ራእይ 21:1-4:: ከዚህ በኋላ አዲስ ሰማይና አዲስ ምድር አየሁ፤ የመጀመሪያው ሰማይና የመጀመሪያዪቱ ምድር ዐልፈዋልና፤ ባሕርም ከእንግዲህ ወዲህ አይኖርም:: ቅድስቲቱ ከተማ፣ አዲሲቱ ኢየሩሳሌም ለባሏ እንደ ተዋበች ሙሽራ ተዘጋጅታ ከሰማይ ከእግዚአብሔር ዘንድ ስትወርድ አየሁ:: ደግሞም እንዲህ የሚል ታላቅ ድምፅ ከዙፋኑ ሲወጣ ሰማሁ፤ «እነሆ፤ የእግዚአብሔር ማደሪያ በሰዎች መካከል ነው፤ እርሱ ከእነርሱ ጋር ይኖራል፤ እነርሱም ሕዝቡ ይሆናሉ፤ እግዚአብሔር

ራሱም ከእነርሱ ጋር ይኖራል፤ አምላካቸውም ይሆናል:: እንባን ሁሉ ከዐይናቸው ያብሳል፤ ከእንግዲህ ወዲህ ሞት ወይም ሐዘን ወይም ልቅሶ ወይም ሥቃይ አይኖርም፤ የቀድሞው ሥርዐት አልፎአልና::

**18. እኛ ከእርሱ ጋር ለዘላለም እንኖር ዘንድ ኢየሱስ ሞተ:: እርስ በርሳችሁ በዚህ እውነት ተጽናኑ::**

1ኛ ተሰ. 5:9-11:: «እግዚአብሔር ድነትን በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ አማካይነት እንድናገኝ ነው እንጂ ለቍጣ ወስኖ አላስቀመጠንምና:: ብንነቃም ሆነ ብናንቀላፋ ከእርሱ ጋር በሕይወት እንድንኖር እርሱ ስለ እኛ ሞተ:: ስለዚህ በእርግጥ አሁን እንደምታደርጉት ሁሉ እርስ በርሳችሁ ተጽናኑ፤ አንዱም ሌላውን ያንጽ::»

**19. በኢየሱስ የሚያምኑ ሁሉ የዘላለም ሕይወት ያገኛሉ::**

ዮሐ. 3:14-15:: «ሙሴ በምድረ በዳ እባብን እንደ ሰቀለ፣ የሰው ልጅም እንዲሁ ሊሰቀል ይገባዋል፤ ይኸውም በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው ነው::»

ዮሐ. 3:16:: በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ እግዚአብሔር አንድያ ልጁን እስከ መስጠት ድረስ ዓለምን እንዲሁ ወዶአልና::

ዮሐ. 3:36:: «በወልድ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት አለው፤ በወልድ የማያምን ግን የእግዚአብሔር ቍጣ በላዩ ይሆናል እንጂ ሕይወትን አያይም::»

1ኛ ዮሐ. 5:11-12:: «ምስክርነቱም ይህ ነው፤ እግዚአብሔር የዘላለምን ሕይወት ሰጠን፤ ይህም ሕይወት ያለው በልጁ ነው:: ልጁ ያለው ሕይወት አለው፤ የእግዚአብሔር ልጅ የሌለው ሕይወት የለውም::»

**20. ኢየሱስ ተመልሶ ሲመጣ በጎቹን ከፍየሎቹ ይለያል::**

ማቴ. 25:31-46::

ማቴ. 25:31-34:: «የሰው ልጅ ከመላእክቱ ሁሉ ጋር በክብሩ



ሲመጣ፣ በክብሩ ዙፋን ላይ ይቀመጣል፤ ሕዝቦች ሁሉ በፊት ይሰበሰባሉ፣ እርሱም፣ እረኛ በጎችን ከፍየሎች እንደሚለይ፣ ሕዝቡን አንዱን ከሌላው ይለያል፤ በጎቹን በቀኙ፣ ፍየሎቹን ግን በግራው ያቆማቸዋል:: በዚያን ጊዜ ንጉሡ በቀኙ በኩል ያሉትን እንዲህ ይላቸዋል፤ «እናንት አባቴ የባረካችሁ ኑ፤ ዓለም ከተፈጠረ ጀምሮ የተዘጋጀላችሁን መንግሥት ውረሱ::

ማቴ. 25:41:: «ከዚያም በግራው በኩል ላሉት ደግሞ እንዲህ ይላቸዋል፤ <እናንተ የተረገማችሁ፤ ለዲያብሎስና ለመላእክቱ ወደ ተዘጋጀው የዘላለም እሳት ከእኔ ተለይታችሁ ሂዱ::>

ማቴ. 25:46:: «እነዚህም ወደ ዘላለም ፍርድ፣ ጻድቃን ግን ወደ ዘላለም ሕይወት ይሄዳሉ::»

**21. ኢየሱስ ከመጣ በኋላ አማኞች እርሱን ይመስላሉ::**

1ኛ ዮሐ. 3:1-2:: «የእግዚአብሔር ልጆች ተብለን እንድንጠራ አብ አትረፍርፎ ያፈሰሰልን ፍቅር ምንኛ ታላቅ ነው! እኛም እንዲሁ ልጆቹ ነን:: ዓለም እኛን የማያውቀንም እርሱን ስላላወቀው ነው:: ወዳጆች ሆይ፤ እኛ አሁን የእግዚአብሔር ልጆች ነን፤ ወደ ፊት ምን እንደምንሆን ገና አልተገለጠም:: እርሱ በሚገለጥበት ጊዜ እናየዋለንና እርሱን እንደምንመስል እናውቃለን::»

**22. ይህ ተስፋ ያለው ሁሉ በእርግጠኝነት ንጹሕ ሕይወትን ለመምራት ይጥራል::**

1ኛ ዮሐ. 3:3:: «በእርሱ ይህን ተስፋ የሚያደርግ ሁሉ፣ እርሱ ንጹሕ እንደ ሆነ ራሱን ያነጻል::»

**23. ክርስቲያኖች የማይጠፋ ርስት እንደሚሰጣቸው ቃል ተገብቶላቸዋል::**

1ኛ ጴጥ. 1:3-9::

1ኛ ጴጥ. 1:3-5:: «የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ አባትና አምላክ ይባረክ፤ እርሱ ከታላቅ ምሕረቱ የተነሣ በኢየሱስ ክርስቶስ ከሞት መነሣት ምክንያት ለሕያው ተስፋ በሚሆን አዲስ ልደት፣ እንዲሁም በሰማይ ለማይጠፋ፣ ለማይበላሽና ለማይለወጥ ርስት

እንደገና ወለደን:: እናንተም በመጨረሻው ዘመን ሊገለጥ የተዘጋጀው ድነት እስኪመጣ ድረስ በእምነት አማካይነት በእግዚአብሔር ኃይል ተጠብቃችኋል::»

24. የእምነት መልካም ገድል ልክ እንደ ጳውሎስ የተጋደለ ሁሉ የጽድቅን አክሊል ይቀበላል::

2ኛ ጢሞ. 4:7-8:: «መልካሙን ገድል ተጋድያለሁ፤ ሩጫውን ጨርሻለሁ፤ ሃይማኖትንም ጠብቄአለሁ:: ወደ ፊት የጽድቅ አክሊል ተዘጋጅቶልኛል፤ ይህንም ጻድቅ ፈራጅ የሆነው ጌታ በዚያ ቀን ለእኔ ይሰጠኛል፤ ደግሞም ለእኔ ብቻ ሳይሆን፣ የእርሱን መገለጥ ለናፈቁ ሁሉ ነው::»

25. ልክ እንደ መንፈሳዊ አባታችን አብርሃምና እንደ መንፈሳዊ ተጓዦች፣ እግዚአብሔር የፈጠራትንና የሠራትን ከተማ ማየት እንችላለን::

ዕብ. 11:9-10:: «በባዕድ አገር እንዳለ መጻተኛ በተስፋዩቱ ምድር በእምነቱ ተቀመጠ፤ የተስፋውን ቃል አብረውት እንደሚወርሱት እንደ ይስሐቅና እንደ ያዕቆብ በድንኳን ኖረ፤ ምክንያቱም መሠረት ያላትን፣ እግዚአብሔር የሠራትንና የፈጠራትን ከተማ ይጠባበቅ ነበር::»

26. አገራችን በሰማይ ነው:: እዚያም የእኛ አካል የኢየሱስ ክርስቶስን የከበረ አካል ይመስላል::

ፊል. 3:20-21:: «እኛ ግን አገራችን በሰማይ ነው፤ ከዚያ የሚመጣውንም አዳኝ፣ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን በናፍቆት እንጠባበቃለን:: እርሱም ሁሉን ለራሱ ባስገዛበት ኃይል፣ ክብር ሥጋውን እንዲመስል የተዋረደውን ሥጋችንን ይለውጣል::»

27. የኢየሱስ ትንሣኤ የእኛንም ትንሣኤ እርግጠኛ ያደርገዋል::

1ኛ ቆሮ. 15:12-23::

1ኛ ቆሮ. 15:20-23:: «ነገር ግን ክርስቶስ ላንቀላፉት ሁሉ በኵራት ሆኖ በእርግጥ ከሙታን ተነሥቶአል:: ሞት በአንድ ሰው በኩል እንደ መጣ፣ የሙታንም ትንሣኤ በአንድ ሰው በኩል



ሆኖአልና:: ሰዎች ሁሉ በአዳም እንደሚሞቱ፣ እንደዚሁም ሰዎች ሁሉ በክርስቶስ ሕያዋን ይሆናሉ፤ ነገር ግን እያንዳንዱ በራሱ ተራ ይሆናል፤ መጀመሪያ በኵራት የሆነው ክርስቶስ፣ ከዚያም በኋላ እርሱ ሲመጣ የክርስቶስ የሆኑት::

28. ጳውሎስ፣ የማይጠፋውንና የማይበሰብሰውን የትንሣኤ አካላችንን ውበትና ክብር በመግለጽ ሞት ድል በመነሣት እንደሚዋጥ ያውጃል::

1ኛ ቆሮ. 15:35-57::

29. ኢየሱስ፣ ድል ለሚነሡ፣ ከኃጢአት ጋር ተዋግተው በማሸነፍ ለክርስቶስ ባላቸው ፍቅር ለሚጸኑ ሰዎች አስደናቂ ቃል ይገባል::

ራእይ 2:11:: «መንፈስ ለአብያተ ክርስቲያናት የሚናገረውን ጆሮ ያለው ይስማ፤ ድል የሚነሣም በሁለተኛው ሞት ከቶ አይጐዳም::»

ራእይ 2:26-28:: «ድል ለሚነሣና ሥራዬንም እስከ መጨረሻው ለሚፈጽም በአሕዛብ ላይ ሥልጣን እሰጠዋለሁ፤ እርሱም:- በብረት በትር ይገዛቸዋል፤ እንደ ሸክላ ዕቃም ይፈጫቸዋል፤ ይህም ልክ እኔ ከአባቴ ዘንድ ሥልጣንን እንደ ተቀበልሁ ነው፤ እኔም የንጋትን ኮከብ እሰጠዋለሁ::»

ራእይ 3:4-5:: «ነገር ግን ልብሳቸውን ያላሳደፉ ጥቂት ሰዎች በሰርዴስ ከአንተ ጋር አሉ፤ እነርሱም ነጭ ልብስ ለብሰው ከእኔ ጋር ይሄዳሉ፤ ይህ የሚገባቸው ነውና:: ድል የሚነሣም እንደ እነርሱ ነጭ ልብስ ይለብሳል፤ እኔም በአባቴና በመላእክቱ ፊት እመሰክርለታለሁ፤ ስሙንም ከሕይወት መጽሐፍ አልደመስስም::»

ራእይ 3:12:: «ድል የሚነሣውን በአምላኬ ቤተ መቅደስ ውስጥ ዐምድ አደርገዋለሁ::»

ራእይ 3:21-22:: «እኔ ድል ነሥቼ ከአባቴ ጋር በእርሱ ዙፋን ላይ እንደ ተቀመጥሁ፣ ድል የሚነሣውንም ከእኔ ጋር በዙፋኔ ላይ እንዲቀመጥ አደርገዋለሁ:: መንፈስ ለአብያተ ክርስቲያናት የሚናገረውን ጆሮ ያለው ይስማ::»

# ውሳኔ መስጠት

1. ኢያሱ እስራኤላውያን ውሳኔ እንዲያደርጉ ጠራቸው::

ኢያሱ 24:14-27::

ኢያሱ 24:14-15:: «አሁንም እግዚአብሔርን ፍሩ፤ በፍጹም ታማኝነትም ተገዙለት:: የቀድሞ አባቶቻችሁ ከወንዙ ማዶና በግብፅ ያመለኳቸውን አማልክት ከእናንተ አርቁ፤ እግዚአብሔርን ብቻ አምልኩ:: እግዚአብሔርን ማምለክ የማያስፈልግ መስሎ ከታያችሁ ግን፣ የቀድሞ አባቶቻችሁ ከወንዙ ማዶ ካመለኳቸው አማልክት ወይም በምድራቸው የምትኖሩባቸው አሞራውያን ከሚያመልኳቸው አማልክት ታመልኩ እንደ ሆነ የምታመልኩትን ዛሬውኑ ምረጡ፤ እኔና ቤተ ግን እግዚአብሔርን እናመልካለን::»

2. የእግዚአብሔር ሰዎች የቃል ኪዳን ውሳኔ ያደርጋሉ::

ኢያሱ 24:19-27::

ኢያሱ 24:24-25:: «ሕዝቡም ኢያሱን፣ «እኛ አምላካችንን እግዚአብሔርን፤ እናመልካለን እንታዘዝለታለንም» አሉት:: በዚያን ቀን ኢያሱ ከሕዝቡ ጋር ቃል ኪዳን አደረገ፤ የሚመሩበትንም ደንብና ሥርዐት እዚያው ሴኬም ሰጣቸው::»

3. ኤልያስ የእግዚአብሔር ሰዎች መወላወላቸውን እንዲያቆሙ ነገራቸው::

1ኛ ነገ. 18:16-39::

1ኛ ነገ. 18:21:: «ኤልያስም በሕዝቡ ፊት ቀርቦ፣ «በሁለት ሐሳብ የምትዋልሉት እስከ መቼ ድረስ ነው? አምላክ እግዚአብሔር ከሆነ እግዚአብሔርን ተከተሉ፤ በኣል አምላክ ከሆነም በኣልን ተከተሉ» አለ::»

4. ዛሬ ድምፁን ብትሰሙ ልባችሁን እልከኛ አታድርጉት (ባለማመንና በዓመፅ ላይ የተላለፈ ማስጠንቀቂያ)::

ዕብ. 3:7-11:: ስለዚህ መንፈስ ቅዱስ እንደሚል፣ «ዛሬ ድምፁን ብትሰሙ፣ በምድረ በዳ በፈተና ቀን፣ በዐመፅ እንዳደረጋችሁት፣



ልባችሁን አታደንድኑ:: አባቶቻችሁ በዚያ ተፈታተኑኝ፤ መረመሩኝ፤ ያደረግሁትንም ሁሉ ለአርባ ዓመት አዩ:: በዚያም ትውልድ ላይ የተቈጣሁት ለዚህ ነበር፣ እንዲህም አልሁ፤ «ልባችሁ ሁልጊዜ ይስታል፤ መንገዴንም አላወቁም፤» ስለዚህ በቍጣዬ እንዲህ ብዬ ማልሁ፤ «ወደ ዕረፍቴ ከቶ አይገቡም::»

5. የሙሴ ውሳኔ ሊከተሉት የሚገባ መልካም ምሳሌ ነው::

ዕብ. 11:24-26:: ሙሴ ካደገ በኋላ፣ የፈርዖን የልጅ ልጅ መባልን በእምነት እምቢ አለ:: ለጥቂት ጊዜ በኀጢአት ከሚገኝ ደስታ ይልቅ፣ ከእግዚአብሔር ሕዝብ ጋር መከራን መቀበል መረጠ:: ከግብፅ ሀብት ይልቅ ስለ ክርስቶስ መከራን መቀበል እጅግ የሚበልጥ ሀብት መሆኑን ተገነዘበ፤ ወደ ፊት የሚቀበለውን ብድራት ከሩቅ ተመለከቶአልና::

6. ሙሉ ለሙሉ የተሰጣችሁ ሁኑ::

ሮሜ 12:1-2:: «እንግዲህ ወንድሞች ሆይ፤ ሰውነታችሁን ቅዱስና እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኝ ሕያው መሥዋዕት አድርጋችሁ ታቀርቡ ዘንድ በእግዚአብሔር ርኅራኄ እለምናችኋለሁ፤ ይህም እንደ ባለ አእምሮ የምታቀርቡት አምልኮአችሁ ነው:: መልካም፣ ደስ የሚያሰኝና ፍጹም የሆነውን የእግዚአብሔር ፈቃድ ምን እንደ ሆነ ፈትናችሁ ታውቁ ዘንድ በአእምሮአችሁ መታደስ ተለወጡ እንጂ ይህን ዓለም አትምሰሉ::»

# መጨፍገግ/ድብርት

በተጨማሪ መጽናናትን በገጽ 46፣ ጸሎትን በገጽ 166፣ የእግዚአብሔር መጋቢነትን በገጽ 176፣ እንዲሁም መታመንን በገጽ 224 ላይ ተመልከቱ::

**1. ኃጢአትን መደበቅ አብዛኛውን ጊዜ ወደ መጨፍገግ ይመራል:: ኃጢአታችሁን ብትናዘዙና ከእነርሱም ዘወር ብትሉ ምሕረትን ታገኛላችሁ::**

ምሳ. 28:13:: «ኀጢአቱን የሚሰውር አይለማም፤ የሚናዘዝና የሚተወው ግን ምሕረትን ያገኛል::»

**2. የቃየን የበደለኝነት ስሜት (መጨፍገግ) በበደል ምክንያት የመጣ ነበር::**

ዘፍ. 4:6-7:: «እግዚአብሔር አምላክም (ያህዌ ኤሎሂም) ቃየንን እንዲህ አለው፤ «ለምን ተናደድህ? ለምንስ ፊትህ ጠቈረ? መልካም ብታደርግ ተቀባይነትን አታገኝምን? መልካም ባታደርግ ግን፣ ኀጢአት በደጅህ እያደባች ናት፤ ልታሸንፍህ ትፈልጋለች፤ አንተ ግን ተቈጣጠራት::»

**3. ዳዊት የአመንዝራነት ኃጢአቱን እስከተናዘዘበት ጊዜ ድረስ የበደለኝነት ስሜት ይሰማው ነበር::**

መዝ. 32:3-4:: «ቀኑን ሙሉ ከመቃተቴ የተነሣ፣ ዝም ባልሁ ጊዜ፣ አጥንቶቼ ተበላሹ፤ በቀንና በሌሊት፣ እጅህ ከብዳብኛለችና::»

**4. በበደል ምክንያት ከተከሠተ የመጨፍገግ ስሜት መውጫው መንገድ መናዘዝና የእግዚአብሔርን ይቅርታ መጠየቅ ነው::**

መዝ. 32:5:: «ኀጢአቴን ለአንተ አስታወቅሁ፤ በደሌንም አልሸሸግሁም፤ ደግሞም «መተላለፌን ለእግዚአብሔር እናዘዛለሁ» አልሁ፤ አንተም የኀጢአቴን በደል፣ ይቅር አልህ::»

መዝ. 32:1-2፣ 11:: «መተላለፉ ይቅር የተባለለት፣ ኀጢአቱም የተሸፈነለት፣ እንዴት ብሩክ ነው! <u>እግዚአብሔር</u> ኀጢአቱን የማይቈጥርበት፣ በመንፈሱም ሽንገላ የሌለበት ሰው፣ እርሱ ብሩክ ነው:: . . . ጻድቃን ሆይ፤ በእግዚአብሔር ደስ ይበላችሁ፤ ሐሤትም



አድርጉ፤ ቅን ልብ ያላችሁም ሁሉ እልል በሉ::»

**5. በምትተክዙበት ጊዜ ተስፋችሁን በእግዚአብሔር ላይ ጣሉት::**

መዝ. 42::

መዝ. 42:5-6:: «ነፍሴ ሆይ፤ ለምን ትተክዢያለሽ? ለምንስ በውስጤ ትታወኪያለሽ? ተስፋሽን በአምላክ ላይ አድርጊ፤ አዳኜና <u>አምላኬን</u>፣ ገና አመሰግነዋለሁና:: ነፍሴ በውስጤ ተክዛለች፤ ስለዚህ በዮርዳኖስ ምድር፣ በአርሞንኤም ከፍታ፣ በሚዛር ተራራ አስብሃለሁ::»

**6. የእስራኤል ታማኞች በባቢሎን ምርኮ በበደለኝነት ስሜት ውስጥ ሳሉ የመጽናናት ቃላት ተሰጣቸው:: በጨለመባቸው ጊዜ እምነታቸውን በሥራ ላይ እንዲያውሉት ጥሪ ቀረበላቸው::**

ኢሳ. 40::

**7. አንዳንድ ከባድ ሁኔታዎችን ብንለማመድም እንኳ፣ ጠሊቅ የሆነ መጨፍገግን ግን ማስወገድ እንችላለን::**

2ኛ ቆሮ. 4:8-9:: «ከየአቅጣጫው ብንገፋም አንንኰታኰትም፤ ግራ ብንጋባም ተስፋ አንቈርጥም፤ ብንሰደድም ተጥለን አንቀርም፤ መትተው ቢጥሉንም አንጠፋም::»

2ኛ ቆሮ. 4:16-18:: «ስለዚህ ተስፋ አንቈርጥም፤ ውጫዊው ሰውነታችን እየጠፋ ቢሄድም እንኳ፣ ውስጣዊው ሰውነታችን ዕለት ዕለት ይታደሳል፤ ምክንያቱም ቀላልና ጊዜያዊ የሆነው መከራችን ወደር የማይገኝለት ዘላለማዊ ክብር ያስገኝልናል:: ስለዚህ ዐይናችን የሚያተኵረው በሚታየው ነገር ላይ ሳይሆን በማይታየው ላይ ነው፤ የሚታየው ጊዜያዊ ነውና፤ የማይታየው ግን ዘላለማዊ ነው::»

**8. ጳውሎስ በእግዚአብሔር ጸጋ ተደግፎ ግራ ሳይገባው (ሳይጨፈግግ) ያለፈባቸውን ጉዳዮች እስቲ ተመልከቷቸው::**

2ኛ ቆሮ. 11:23-28:: «የክርስቶስ ከአገልጋዮች ናቸውን? እንደ አበደ ሰው ልናገርና እኔ እበልጣቸዋለሁ፤ ደግሞም ብዙ ጊዜ በሥራ ደክሜአለሁ፤ ብዙ ጊዜ ታስሬአለሁ፤ ብዙ ጊዜ ተገርፌአለሁ፤ ብዙ ጊዜ ለሞት ተቃርቤአለሁ:: አይሁድ ለአርባ ጅራፍ አንድ የቀረው

**እምስት ጊዜ ገርፈውኛል:: ሦስት ጊዜ በዱላ ተደብድቤአለሁ፤ አንድ ጊዜ በድንጋይ ተወግሬአለሁ፤ ሦስት ጊዜ የመርከብ አደጋ ደርሶብኛል፤ አንድ ሌሊትና ቀን በባሕር ላይ አድሬአለሁ፤ ብዙ ጊዜ በጉዞ ተንከራትቻለሁ፤ ደግሞም ለወንዝ ሙላት አደጋ፣ ለወንበዴዎች አደጋ፣ ለገዛ ወገኖቼ አደጋ፣ ለአሕዛብ አደጋ፣ ለከተማ አደጋ፣ ለገጠር አደጋ፣ ለባሕር አደጋ፣ እንዲሁም ለሐሰተኞች ወንድሞች አደጋ ተጋልጬ ነበር:: ብዙ ጥሬአለሁ፤ ብዙ ደክሜአለሁ፤ ብዙ ጊዜ እንቅልፍ አጥቻለሁ፤ ተርቤአለሁ፣ ተጠምቻለሁ፤ ብዙ ጊዜ ምግብ ሳልቀምስ ኖሬአለሁ፤ በብርድና በራቍትነት ተቈራምጃለሁ:: ሌላውን ነገር ሳልቈጥር፣ ዕለት ዕለት የሚያስጨንቀኝ የአብያተ ክርስቲያናት ሁሉ ሐሳብ ነው::**



# ፍቺ

በተጨማሪ ጋብቻ፣ የባልና የሚስት ግንኙነቶች የሚለውን በገጽ 129 ላይ ተመልከቱ::

1. **እግዚአብሔር ጋብቻን ሲመሠርት የጋብቻ ትሥሥር ቋሚ መሆኑን ግልጽ አድርጓል::**

   ዘፍ. 2:24:: «ስለዚህ ሰው ከአባቱና ከእናቱ ተለይቶ ከሚስቱ ጋር ይጣመራል፤ ሁለቱም አንድ ሥጋ ይሆናሉ::»

2. **እግዚአብሔር፣ እስራኤላውያን የፍቺን ኃጢአት ስለፈጸሙ ገሠጻቸው፤ ለጋብቻ ቃል ኪዳናቸውም ታማኞች እዲሆኑ አዘዛቸው::**

   ሚል. 2:13-16::

3. **እግዚአብሔር መፋታትን ይጠላል::**

   ሚል. 2:16:: «ፍችን እጠላለሁ» ይላል የእስራኤል <u>አምላክ እግዚአብሔር</u>፤ ልብሱን በግፍ ድርጊት የሚሸፍነውንም ሰው እጠላለሁ» ይላል እግዚአብሔር ጸባኦት:: ስለዚህ በመንፈሳችሁ ራሳችሁን ጠብቁ፤ ታማኝነታችሁም አይጓደል::

4. **ኢየሱስ ያለ ዝሙት ምክንያት ፍቺ አይቻልም አለ::**

   ማቴ. 5:31-32:: «ሚስቱን የሚፈታ ሁሉ የፍቺ ወረቀት መስጠት አለበት:: እንደተባለ ሰምታችኋል:: እኔ ግን እላችኋለሁ፤ በላዩ ላይ ስታመነዝር ካላገኛት በስተቀር፣ ሚስቱን የሚፈታ ሁሉ እንድታመነዝር ያደርጋታል፤ በዚህ ሁኔታ የተፈታችውን ሴት ያገባም እንዳመነዘረ ይቈጠራል::»

   ማቴ. 19:3-9::

   ማቴ. 19:4-6:: «እርሱም መልሶ እንዲህ አላቸው፤ <ፈጣሪ በመጀመሪያ ወንድና ሴት አድርጎ አንደ ፈጠራቸው አላነበባችሁምን? እንዲህም አለ፤ «ሰው አባቱንና እናቱን ይተዋል፤ ከሚስቱም ጋር ይጣመራል፣ ሁለቱም አንድ ሥጋ ይሆናሉ የተባለው በዚህ ምክንያት አይደለምን? ከእንግዲህ አንድ ሥጋ ናቸው እንጂ ሁለት አይደሉም፤

ስለዚህ እግዚአብሔር ያጣመረውን ሰው አይለየው::»

5. ባልና ሚስት ሞት እስኪለያያቸው ድረስ የተጣመሩ ናቸው::

ሮሜ 7:1-3:: «ወንድሞች ሆይ፤ ሕግን ለማያውቁ ሰዎች እናገራለሁ፤ ሕግ በአንድ ሰው ላይ ሥልጣን የሚኖረው፣ ሰውዬው በሕይወት እስካለ ድረስ ብቻ መሆኑን አታውቁምን? እንዲት ያገባች ሴት ከባሏ ጋር በሕግ የታሠረች የምትሆነው እርሱ በሕይወት እሳካለ ድረስ ነው፤ ባሏ ቢሞት ግን ከጋብቻ ሕግ ነጻ ትሆናለች:: ነገር ግን ባሏ በሕይወት እያለ ሌላ ሰው ብታገባ አመንዝራ ትባላለች፤ ባሏ ቢሞት ግን ሌላ ሰው ብታገባም እንኳ፣ ከዚያ ሕግ ነጻ ትሆናለች፤ አመንዝራ አትባልም::»

6. የሙሴ ሕግ ስለ ፍቺ ጽሕፈት ይናገራል::

ዘዳ. 24:1-4::

7. አማኝ ሰው ከማታምን ሚስቱ ጋር ለመፋታት መንሥኤ ሲሆን አይገባውም::

1ኛ ቆሮ. 7:10-16::

8. የማያምነው የትዳር ጓደኛ ሊለይ ቢፈልግ፣ ሊያደርግ ይችላል::

1ኛ ቆሮ. 7:15:: «ነገር ግን የማያምነው ወገን መለየት ከፈለገ ይለይ፤ አንድ ወንድም ወይም እኅት በዚህ ሁኔታ የታሰሩ አይደሉም፤ እግዚአብሔር የጠራን በሰላም እንድንኖር ነው::»

9. በትዳር ውስጥ ችግር በተነሣ ቁጥር የሚያምነው ወገን ሁልጊዜ እርቅ መፈለግ አለበት::

ሮሜ 12:18:: «ቢቻላችሁስ በበኩላችሁ ከሰው ሁሉ ጋር በሰላም ኑሩ::»

ማቴ. 5:23-24:: «ስለዚህ መባህን በመሠዊያው ላይ ለእግዚአብሔር በምታቀርብበት ጊዜ ወንድምህ የተቀየመብህ ነገር መኖሩ ትዝ ቢልህ፣ መባህን በዚያው በመሠዊያው ፊት ተወው፤ በመጀመሪያ ሄደህ ከወንድምህ ጋር ተስማማ፤ ከዚያም ተመልሰህ መባህን ለእግዚአብሔር አቅርብ::»



ማቴ. 18:15-18:: «ወንድምህ ቢበድልህ ሄደህ አንተና እርሱ ብቻ ሆናችሁ ጥፋቱን ንገረው:: ቢሰማህ፣ ወንድምህን እንደ ገና የራስህ ታደርገዋለህ:: ባይሰማህ ግን ቃል ሁሉ በሁለት ወይም በሦስት ምስክሮች ፊት ስለሚጸና፣ አንድ ወይም ሁለት ሰው ይዘህ አነጋግረው:: እነርሱን ባይሰማ ለቤተ ክርስቲያን ንገር፤ ቤተ ክርስቲያንንም ባይሰማ እንደ አሕዛብና እንደ ቀረጥ ሰብሳቢ ቊጠረው:: እውነት እላችኋለሁ፤ በምድር ያሰራችሁት ሁሉ በሰማይ የታሰረ ይሆናል፤ በምድርም የፈታችሁት ሁሉ በሰማይ የተፈታ ይሆናል::»

# ምሳሌነት (መልካም ወይም ክፉ)

**1. ሌሎች ይከተሏችሁ ዘንድ መንፈሳዊ ምሳሌዎች ሁኑላቸው::**

1ኛ ጢሞ. 4:12:: «ወጣትነትህን ማንም አይናቅ፤ ነገር ግን ለሚያምኑት በንግግርና በኑሮ፣ በፍቅር፣ በእምነትና በንጽሕና አርኣያ ሁንላቸው::»

**2. መጋቢዎችና ሽማግሌዎች ለመንጋው መልካም ምሳሌዎች ሊሆኑ ይገባል::**

1ኛ ጴጥ. 5:2-4:: «በእናንተ ኀላፊነት ሥር ያለውን የእግዚአብሔርን መንጋ ጠብቁ፤ የምጥጠብቁትም ከእግዚአብሔር እንደሚጠብቅባችሁ በግድ ሳይሆን በፈቃደኝነት፣ ለጥቅም በመስገብገብ ሳይሆን ለማገልገል ባላችሁ ጽኑ ፍላጎት ይሁን፤ እንዲሁም በዐደራ ለተሰጣችሁ መንጋ መልካም ምሳሌ በመሆን እንጂ በላያቸው በመሠልጠን አይሁን:: የእረኞች አለቃ በሚገለጥበት ጊዜ የማይጠፋውን አክሊል ትቀበላላችሁ::»

**3. ሐዋርያው ጳውሎስ ክርስቲያኖች እንዴት መመላለስ እንደሚገባቸው ሌሎችን ለማስተማር መንፈሳዊ ምሳሌነት አሳይቶአል::**

1ኛ ቆሮ. 4:15-16:: «ምንም እንኳ በዐሥር ሺህ የሚቈጠሩ ሞግዚቶች በክርስቶስ ቢኖራችሁም፣ ብዙ አባቶች ግን የሏችሁም፤ በወንጌል አማካይነት በክርስቶስ ኢየሱስ ወልጄአችኋለሁና:: ስለዚህ እኔን እንድትመስሉ እለምናችኋለሁ::»

1ኛ ቆሮ. 11:1:: «እኔ የክርስቶስን ምሳሌ እንደምከተል እናንተም የእኔን ተከተሉ::»

2ኛ ተሰ. 3:7-8:: «የእኛን ምሳሌ እንዴት መከተል እንደሚገባችሁ እናንተ ራሳችሁ ታውቃላችሁና:: ከእናንተ ጋር በነበርንበት ጊዜ ሥራ ፈቶች አልነበርንም፤ ደግሞም የማንንም እንጀራ በነፃ አልበላንም፤ ነገር ግን ከእናንተ በአንዳችሁም ላይ ሸክም እንዳንሆን ሌሊትና ቀን እንደክምና እንሠራ ነበር::»

**4. ጳውሎስ በተሰሎንቄ የነበሩትን አዳዲስ ክርስቲያኖች በመንፈሳዊ**



**ምሳሌነቱ ስላስተማራቸው እነርሱም ብዙ ሳይቆዩ ለሌሎች መልካም ምሳሌዎች ሆኑ::**

1ኛ ተሰ. 1:5-7:: «ምክንያቱም ወንጌላችን ወደ እናንተ የመጣው በኀይልና በመንፈስ ቅዱስ በብዙም መረዳት እንጂ በቃል ብቻ አይደለም:: ደግሞ ስለ እናንተ ስንል በመካከላችሁ እንዴት እንደኖርን ታውቃላችሁ:: እናንተ እኛንና ጌታን መስላችኋል፤ ምንም እንኳ ብርቱ መከራ ቢደርስባችሁም ቃሉን በመንፈስ ቅዱስ ደስታ ተቀብላችኋል:: ከዚህም የተነሣ በመቄዶንያና በአካይያ ለሚገኙ ምእምናን መልካም ምሳሌ ሆናችኋል::»

**5. ኢየሱስ መጥፎ ምሳሌዎች እንዳንሆንና ሌሎችን ወደ ኃጢአት እንዳንመራ ያስጠነቅቀናል::**

ማቴ. 5፤19:: «ስለዚህ ማንም ከእነዚህ ትእዛዛት አነስተኛዪቱን እንኳን ቢተላለፍ፣ ሌሎችንም እንዲተላለፉ ቢያስተምር በመንግሥተ ሰማይ ታናሽ ተብሎ ይጠራል፤ ነገር ግን እነዚህን ትእዛዛት እየፈጸመ ሌሎችንም እንዲፈጽሙ የሚያስተምር በመንግሥተ ሰማይ ታላቅ ይባላል::»

ማቴ. 18:6:: «ነገር ግን በእኔ ከሚያምኑት ከእነዚህ ከታናናሾቹ አንዱን የሚያሰናክል ሰው፣ ከባድ የወፍጮ ድንጋይ በዐንገቱ ታስሮ ወደ ጥልቅ ባሕር ተጥሎ ቢሰጥም ይሻለዋል::

ሉቃ. 17:1-3:: ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱን እንዲህ አላቸው፤ «ሰዎችን የሚያሰናክል መምጣቱ አይቀርም፤ ነገር ግን ለመሰናከሉ መምጣት ምክንያት ለሚሆን ለዚያ ሰው ወዮለት:: ይህ ሰው ከእነዚህ ከታናናሾች አንዱን ከሚያሰናክል የወፍጮ ድንጋይ በአንገቱ ታስሮ ወደ ባሕር ቢጣል ይሻለው ነበር:: ስለዚህ ለራሳችሁ ተጠንቀቁ::»

**6. በሌላው ሰው መንገድ ላይ የማሰናከያ እንቅፋት ፈጽሞ አታኑሩ::**

ሮሜ 14:13:: «ስለዚህ እርስ በርሳችን፣ አንዱ በሌላው ላይ ከመፍረድ እንቈጠብ፤ በዚህ ፈንታ ግን በወንድምህ መንገድ ላይ የማሰናከያ ድንጋይ ወይም ወጥመድ እዳታስቀምጥ ቍርጥ ሐሳብ

አድርግ::»

7. **አንድ ሰው ሌላውን ሰው ኀጢአት እንዲሠራ ከሚያሰናክለው ይልቅ በራሱ ቸልተኝነት የሆነውን ነገር ለመተው መዘጋጀት አለበት::**

ሮሜ 14:1-21::

ሮሜ 14:19-21:: «ስለዚህ ሰላም የሚገኝበትንና እርስ በርሳችንም የምንታነጽበትን ማንኛውንም ጥረት እናድርግ:: ለምግብ ስትል የእግዚአብሔርን ሥራ አታፍርስ:: ሁሉ ንጹሕ ነው፤ ነገር ግን ለሌላው ሰው የመሰናከያ ምክንያት የሚሆነውን መብላት ስሕተት ነው:: ለወንድምህ መሰናከል ምክንያት የሚሆነውን ሥጋን አለመብላት፣ ወይንን አለመጠጣት፣ ወይም አንዳች ነገርን አለማድረግ መልካም ነው::»

1ኛ ቆሮ. 8:1-13:: (ጳውሎስ ለጣዖት የተሠዋውን ምግብ ስለመብላት ጉዳይ መልስ ይሰጣል::)

1ኛ ቆሮ. 8:9-13:: «ነገር ግን ከነጻነታችሁ የተነሣ የምታደርጉት ለደካሞች ዕንቅፋት እንዳይሆን ተጠንቀቁ:: አንተ ይህን የመሰለ ዕውቀት ኖሮህ፣ ደካማ ኅሊና ያለው ሰው፣ በቤተ ጣዖት ስትበላ ቢያይህ፣ ለጣዖት የተሠዋውን ምግብ ለመብላት አይደፋፈርምን? ስለዚህ ክርስቶስ የሞተለት ይህ ደካማ ወንድም በአንተ ዕውቀት ምክንያት ጠፋ ማለት ነው:: በዚህ መንገድ ወንድሞቻችሁን በመበደልና ደካማ ኅሊናቸውን በማቍሰል፣ ክርስቶስን ትበድላላችሁ:: ስለዚህ እኔ የምበላው ነገር ወንድሜን የሚያሰናክለው ከሆነ፣ ወንድሜን ላለማሰናከል ስል ከቶ ሥጋ አልበላም::»



# ሐሰተኛ ነቢያት፣ ሐሰተኛ አስተማሪዎች

ማስታወሻ:- ሐሰተኛ ነቢያትና ሐሰተኛ አስተማሪዎች የሚነሡት ከቤተ ክርስቲያን ውስጥ ነው:: ሁልጊዜ ሐሰተኛ ነገርን በማስቀደም እውነትን ይቀላቅላሉ:: ስለዚህም እነርሱን ለይቶ ለማወቅ ብዙ ጊዜ አስቸጋሪ ነው:: ይህም ነቅቶ መጠባበቅን ይጠይቃል::

1. **ሐሰተኛ ነቢያት ሰላም በሌለበት ሥፍራ ሰላም ታገኛላችሁ የሚል ተስፋ ይሰጣሉ:: በኃጢአት ብትኖሩም እንኳን እግዚአብሔር አይቀጣችሁም ብለው ይናገራሉ::**

ኤር. 14:11-16::

ኤር. 14:13-14:: «እኔም፣ «ጌታ እግዚአብሔር ሆይ፤ ወዮ!፣ ነቢያቱ <ሰይፍ አታዩም፤ ራብም አያገኛችሁም፤ ነገር ግን በዚህ ስፍራ ዘለቄታ ያለው ሰላም እሰጣችኋለሁ> ይላል ይሏቸዋል» አልሁ:: እግዚአብሔርም እንዲህ አለኝ፤ «ነቢያቱ በስሜ የሐሰት ትንቢት ይናገራሉ፤ እኔ አልላክኋቸውም፤ አላዘዝኋቸውም፤ አልተናገርኋቸውምም::»

2. **እግዚአብሔር፣ ሐሰተኛ ነቢያት በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የሚያደርሱትን ጥፋት ይገልጣል፤ ያስጠነቅቃልም::**

ኤር. 23:1-40::

3. **እግዚአብሔር መንጋውን ያጠፉትንና የበተኑትን እረኞች ያስጠነቅቃቸዋል::**

ኤር. 23:1-4:: «በማሰማሪያ ቦታዬ ያሉትን በጎቼን ለሚያጠፉና ለሚበትኑ እረኞች ወዮላቸው!» ይላል እግዚአብሔር:: ስለዚህ የእስራኤል አምላክ እግዚአብሔር ሕዝቤን ስለሚጠብቁ እረኞች እንዲህ ይላል፤ «መንጋዬን ስለ በተናችሁ፣ ስላባረራችሁና ተገቢውን ጥንቃቄ ስላላደረጋችሁላቸው፣ ለክፋታችሁ ተገቢውን ቅጣት አመጣባችኋለሁ» ይላል እግዚአብሔር፤ የመንጋዬንም ቅሬታ ካባረርሁባቸው አገሮች ሁሉ እኔ ራሴ ሰብስቤ፣ ወደ መሰማሪያቸው እመልሳቸዋለሁ፤ በዚያም ፍሬያማ ይሆናሉ፤ ይበዛሉም:: የሚጠብቋቸውን እረኞች አስነሣላቸዋለሁ፤ ከእንግዲህም አይፈሩም፤

አይደነግጡም ከእነርሱም አንዱ እንኳ አይጎድልም» ይላል እግዚአብሔር።

4. እግዚአብሔር ሕዝቡ፣ ንስሐ ያልገቡ ኃጢአተኞችን አይፈርድባችሁም የሚሏቸውን ሐሰተኛ ነቢያት እንዳይሰሟቸው ያስጠነቅቃል።

ኤር. 23:16-24።

ኤር. 23:16-20። «የሰራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፤ «እነዚህ ነቢያት የሚተነብዩላችሁን አትስሙ፤ በባዶ ተስፋ ይሞሏችኋል፤ ከእግዚአብሔር አፍ የወጣ ሳይሆን፣ ከገዛ ልባቸው የሆነውን ራእይ ይናገራሉ። እኔን ለሚንቁኝ፣ <እግዚአብሔር ሰላም ይሆንላችኋል ብሏል> ይላሉ። የልባቸውን እልኸኝነት ለሚከተሉም ሁሉ፣ <ክፉ ነገር አይነካችሁም> ይሏቸዋል። ቃሉን ለማየትና ለመስማት፣ እነማን የእግዚአብሔር ምክር ባለበት ቆመዋል? ቃሉን ያደመጠ፣ የሰማስ ማን ነው? እነሆ፣ የእግዚአብሔር ዐውሎ ነፋስ በቍጣ ይነሣል፤ ብርቱም ማዕበል፣ የክፉዎችን ራስ ይመታል። እግዚአብሔር የልቡን ሐሳብ፣ ሙሉ በሙሉ ሳይፈጽም፣ ቍጣው እንዲሁ አይመለስም፤» በኋለኛው ዘመን ይህን በግልጽ ትረዳላችሁ።

ሕዝ. 13:1-16።

ሕዝ. 13:10-12። «ሰላም ሳይኖር፣ <ሰላም አለ>እያሉ ሕዝቤን ያስታሉ፤ ሕዝቡ ካብ ሲሰራ እነርሱ በኖራ ይለስናሉ፤ ስለዚህ በኖራ ለሚለስኑት ካቡ እንደሚወድቅ ንገራቸው። ዶፍ ይወርዳል፤ ታላቅ ድንጋይ እሰዳለሁ፤ ዐውሎ ነፋስም ይነሣል። እነሆ ካቡ ሲፈርስ ሕዝቡ <የለሰናችሁበት ኖራው ወዴት ሄደ?> ብለው አይጠይቁአችሁምን?

5. ኢየሱስ፣ የበጎችን ለምድ ለብሰው የሚመላለሱ፣ ተኩላዎች የሆኑትን ሐሰተኛ ነቢያት ይቃወማል።

ማቴ. 7:15። «በውስጣው ነጣቂ ተኵሎች ሆነው ሳሉ የበግ ለምድ ለብሰው መካከላችሁ በመግባት ከሚያሸምቁ ሐሰተኛ ነቢያት ተጠንቀቁ።»

6. ጳውሎስ፣ ከቤተ ክርስቲያን ውስጥ እንኳ ለመንጋው የማይራሩ



ጨካኝ ተኩላዎች እንደሚመጡ ያስጠነቅቃል።

ሐዋ. 20:29-31። «እኔ ከሄድሁ በኋላ፣ ነጣቂ ተኵላዎች መጥተው በመካከላችሁ ሰርገው እንደሚገቡና ለመንጋውም እንደማይራሩ ዐውቃለሁ። ከእናንተው መካከል እንኳ የራሳቸውን ደቀ መዛሙርት ለማፍራት እውነትን የሚያጣምሙ ይነሣሉ። ስለዚህ ተጠንቀቁ፤ ሦስት ዓመት ሙሉ ሌሊትና ቀን ምንም ያህል ሳላቋርጥ በእንባ እያንዳንዳችሁን እንደ መከርኋችሁ አስታውሱ።»

7. ጳውሎስ፣ ሐሰተኛ አስተማሪዎችን በቤተ ክርስቲያን መካከል ተነሥተው አፍራሽ የሆኑ ሐሰቶችን በድብቅ እንደሚያስተምሩ አስጠንቅቋል።

2ኛ ጴጥ. 2:1-3። «ነገር ግን ሐሰተኞች ነቢያት በሕዝቡ መካከል እንደ ነበሩ እንዲሁም በእናንተ መካከል ሐሰተኞች መምህራን ይነሣሉ፤ እነርሱም የዋጃቸውን ጌታ እንኳ ክደው ጥፋት የሚያስከትል የስሕተት ትምህርት በስውር ያስገባሉ፤ በዚህም በራሳቸው ላይ ድንገተኛ ጥፋት ያመጣሉ። ብዙዎች አስነዋሪ ድርጊቶቻቸውን ይከተላሉ፤ በእነርሱም ምክንያት የእውነት መንገድ ይሰደባል። እነዚህ ሐሰተኞች መምህራን እየተስገበገቡ በፈጠራ ታሪካቸው ይበዘብዙዋችኋል። ፍርዳቸው ከጥንት ጀምሮ ዝግጁ ነው፤ መጥፊያቸውም አያንቀላፋም።»

8. ሐሰተኛ አስተማሪዎች የብርሃንን መልአክ ሊመስሉ ይችላሉ።

2ኛ ቆሮ. 11:1-15።

2ኛ ቆሮ. 11:13-15። «እንደነዚህ ያሉ ሰዎች የክርስቶስን ሐዋርያት ለመምሰል ራሳቸውን የሚለዋውጡ፣ ሐሰተኞች ሐዋርያትና አታላዮች ሠራተኞች ናቸው። ይህም የሚያስደንቅ ነገር አይደለም፤ ምክንያቱም ሰይጣን ራሱ የብርሃን መልአክ ለመምሰል ራሱን ይለዋውጣል። እንግዲህ የእርሱ አገልጋዮች፣ የጽድቅ አገልጋዮች ለመምሰል ራሳቸውን ቢለውጡ የሚያስገርም አይደለም፤ ፍጻሜአቸውም እንደ ሥራቸው ይሆናል።»

9. በሐሰተኛ አስተማሪዎች (ይሁዲ አድራጊዎች) አማካይነት

በቀላሉ ከወንጌል ንጽሕና እንደ ተሳሳቱት እንደ ገላትያ ክርስቲያኖች አትሁኑ::

ገላ. 3:1-9::

ገላ. 3:1:: «እናንተ የማታስተውሉ የገላትያ ሰዎች ሆይ! ለመሆኑ ማን መተት አደረገባችሁ? ኢየሱስ ክርስቶስ እንደ ተሰቀለ ሆኖ በፊት ለፊታችሁ በግልጥ ተሥሎ ነበር::»

10. መናፍስት ከእግዚአብሔር ዘንድ እንደሆኑ ወይም እንዳልሆኑ በእግዚአብሔር ቃል ፈትኗቸው::

1ኛ ዮሐ. 4:1-3::

1ኛ ዮሐ. 4:1:: «ወዳጆች ሆይ፤ መንፈስን ሁሉ አትመኑ፤ ነገር ግን መናፍስት ከእግዚአብሔር መሆናቸውን መርምሩ፤ ምክንያቱም ብዙ ሐሰተኞች ነቢያት ወደ ዓለም ወጥተዋልና::»

11. እንደቤርያ ክርስቲያኖች ሁኑ::

ሐዋ. 17:11:: «የቤርያ ሰዎች ከተሰሎንቄ ሰዎች ይልቅ አስተዋዮች ነበሩ፤ ምክንያቱም ነገሩ እንደዚህ ይሆንን እያሉ መጻሕፍትን በየዕለቱ በመመርመር ቃሉን በታላቅ ጉጉት ተቀብለዋል::»

12. ኢየሱስ፣ የምትሰማውን ሁሉ የምትፈትነውንና ሐሰተኛ አስተማሪዎችን ልትታገሥ ያልቻለችውን ቤተ ክርስቲያን ያመሰግናታል::

ራእይ 2:2-3:: (በኤፌሶን ወዳለው ቤተ ክርስቲያን) «ሥራህን፣ ጥረትህንና ትዕግሥትህን ዐውቃለሁ:: ክፉዎችንም ችላ ብለህ እንዳላለፍሃቸው፣ ሐዋርያት ሳይሆኑ ሐዋርያት ነን የሚሉትንም መርምረህ ሐሰተኞች ሆነው እንዳገኘሃቸው ዐውቃለሁ:: ደግሞም በትዕግሥት መጽናትህንና ስለ ስሜም መከራን መቀበልህን ዐውቃለሁ፤ በዚህ ሁሉ አልታከትህም::»

13. በኤርምያስ ዘመን አስቀያሚና አስደንጋጭ ነገር ተከሰተ:: የሐሰት አስተማሪዎች ሐሰትን አስፋፉ፣ ሕዝቡ ደግሞ ሐሰቱን ወደደ::



ኤር. 5:30-31:: «የሚያስፈራና የሚያስደነግጥ ነገር፣ በምድሪቱ ላይ ሆኖአል፤ ነቢያት በሐሰት ትንቢት ይናገራሉ፤ ካህናት በነቢያቱ ምክር ያስተዳድራሉ፤ ሕዝቤም እንዲህ ያለውን ይወዳሉ፤ ፍጻሜው ሲደርስ ግን ምን ታደርጉ ይሆን?»

14. እግዚአብሔር፣ ሕዝቡ ንስሐ እንዲገቡና እውነተኛ ነቢያትን እንዲሰሟቸው ይጠራቸዋል::

ኤር. 6::

ኤር. 6:16-17:: «እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፤ «መንታ መንገድ ላይ ቁሙ፣ ተመልከቱም፤ መልካሟን፣ የጥንቷን መንገድ ጠይቁ፤ በእርሷም ላይ ሂዱ:: ለነፍሳችሁ ዕረፍት ታገኛላችሁ፤ እናንተ ግን፣ <በእርሷ አንሄድም> አላችሁ:: ጠባቂዎችን አቆምሁላችሁ፤ <የመለከትንም ድምፅ ስሙ> አልኋችሁ፤ እናንተ ግን፣ <አንሰማም> አላችሁ፤፤

15. ሐሰተኛ ነቢያት ወደ ኃጢአት ባርነት ውስጥ ጠልፈው እንዲጥሏችሁ አትፍቀዱ::

2ኛ ጴጥ. 2:17-22::

2ኛ ጴጥ. 2:18-19::

ከንቱ ቃል እየደረደሩ በስሕተት ከሚኖሩት መካከል አምልጠው የመጡትን ሰዎች በሴሰኛ ሥጋዊ ምኞት በማባበል ያታልላሉና:: እነርሱ ራሳቸው የጥፋት ባሪያዎች ሆነው ሳሉ፣ ሌሎችን ነጻ ትወጣላችሁ እያሉ ተስፋ ይሰጧቸዋል፤ ሰው ለተገዛለት ለዚያ ነገር ባሪያ ነውና::

16. በአመፀኞች ሰዎች ትምህርት እንዳትወሰዱ ለራሳችሁ ተጠንቀቁ::

2ኛ ጴጥ. 3:17-18:: እንግዲህ ወዳጆች ሆይ፤ ይህን አስቀድማችሁ ስላወቃችሁ፣ ጸንታችሁ ከቆማችሁበት መሠረት በዐመፀኞች ስሕተት ተስባችሁ እንዳትወድቁ ተጠንቀቁ:: ነገር ግን በጌታችንና በአዳኛችን በኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋና ዕውቀት እደጉ፤ ለእርሱ አሁንም፣ ለዘላለም ክብር ይሁን፤ አሜን::

# ፍርሃት

በተጨማሪ መጽናናትን በገጽ 46፤ ጸሎትን በገጽ 166፤ እንዲሁም መታመንን በገጽ 224 ተመልከቱ::

1. አማኞች ለፍርሃት ባሪያ መሆን የለባቸውም::

ሮሜ 8:15:: «እንደ ገና የፍርሀት ባሪያ የሚያደርጋችሁን መንፈስ ሳይሆን፣ «አባ፣ አባት» ብለን የምንጠራበትን የልጅነት መንፈስ ተቀብላችኋልና፤»

2ኛ ጢሞ. 1:7:: «እግዚአብሔር የኀይልና የፍቅር፣ ራስንም የመግዛት መንፈስ እንጂ የፍርሀት መንፈስ አልሰጠንምና::»

2. እግዚአብሔር ረዳታችሁ ከሆነ መፍራት የለባችሁም::

ዕብ. 13:5-6:: «ራሳችሁን ከፍቅረ ንዋይ ጠብቁ፤ ባላችሁ ነገር ረክታችሁ ኑሩ፤ ምክንያቱም እግዚአብሔር፣ «ከቶ አልተውህም፤ በፍጹም አልጥልህም» [ዘዳ. 31:6] ብሎአል:: ስለዚህ በሙሉ ልብ፣ «ጌታ ረዳቴ ነው፤ አልፈራም፤ ሰው ምን ሊያደርገኝ ይችላል?» [መዝ. 118:6-7] እንላለን::»

3. እግዚአብሔር የአማኝ ብርሃን ስለሆነ፣ አማኝ መፍራት የለበትም::

መዝ. 27:1:: «እግዚአብሔር ብርሃኔና መድኀኒቴ ነው፤ የሚያስፈራኝ ማን ነው? እግዚአብሔር ለሕይወቴ ዐምባዋ ነው፤ ማንን እፈራለሁ?»

4. በእግዚአብሔር መታመን ፍርሃትን አውጥቶ ይጥላል::

መዝ. 56:3-4:: «ፍርሃት በሚይዘኝ ጊዜ፣ እምነቴን በአንተ ላይ አደርጋለሁ:: ቃሉን በማመሰግነው አምላክ፣ በእግዚአብሔር ታምኛለሁ፤ አልፈራም፤ ሥጋ ለባሽ ምን ሊያደርገኝ ይችላል?»

መዝ. 56:10-11:: «ቃሉን በማመሰግነው አምላክ፣ ቃሉን በማመሰግነው በእግዚአብሔር፣ በአምላክ ታምኛለሁ፤ አልፈራም፤ ሥጋ ለባሽ ምን ሊያደርገኝ ይችላል?»

5. ሥጋን መግደል የሚችሉትን አትፍሩ::



ማቴ. 10:28:: «ሥጋን መግደል እንጂ ነፍስን መግደል የማይችሉትን አትፍሩ፤ ይልቁንስ ነፍስንና ሥጋን በገሃነም ማጥፋት የሚቻለውን ፍሩ::»

6. አትፍሩ፤ እግዚአብሔር ለድንቢጦች ይጠነቀቃል፣ ለእናንተም በእርግጥ ይጠነቀቃል::

ማቴ. 10:29-30:: «በአንድ ሳንቲም ከሚሸጡት ሁለት ድንቢጦች አንዲቷ እንኳ ያለ አባታችሁ ፈቃድ ምድር ላይ አትወድቅም:: የራስ ጠጕራችሁ እንኳ አንድ ሳይቀር የተቈጠረ ነው::»

7. ፍጹም ፍቅር ፍርሃትን አውጥቶ ይጥላል::

1ኛ ዮሐ. 4:18:: «በፍቅር ፍርሃት የለም፤ ፍጹም ፍቅር ግን ፍርሃትን አውጥቶ ይጥላል፤ ፍርሀት ከቅጣት ጋር የተያያዘ ነውና:: የሚፈራም ሰው ፍቅሩ ፍጹም አይደለም::»

# የኃጢአቶች ይቅርታ
# (የእግዚአብሔር ይቅርታ)

በተጨማሪ ደኅንነትን በገጽ 192 ላይ ይመልከቱ።

**1. አማኞች እንደ በረዶ ነጭ እንዲሆኑ ተደርገዋል።**

ኢሳ. 1:18። «ኑና፤ እንዋቀስ» ይላል እግዚአብሔር፤ «ኀጢአታችሁ እንደ ዐለላ ቢቀላ እንደ በረዶ ይነጣል፤ እንደ ደም ቢቀላም እንደ ባዘቶ ነጭ ይሆናል።»

**2. ዳዊት የአመንዝራነቱ ኃጢአቱን ከተናዘዘና እግዚአብሔር ይቅር ካለው በኋላ በደስታ ለእግዚአብሔር ዘመረ።**

መዝ. 32:1-2። «መተላለፉ ይቅር የተባለለት፣ ኀጢአቱም የተሸፈነለት፣ እንዴት ቡሩክ ነው! እግዚአብሔር ኀጢአቱን የማይቈጥርበት፣ በመንፈሱም ሽንገላ የሌለበት ሰው፣ እርሱ ቡሩክ ነው።»

**3. ዳዊት ንስሐ እስኪገባና ይቅር እስኪባል ድረስ የበደለኝነት ስሜት ነበረው።**

መዝ. 32:3-4። «ቀኑን ሙሉ ከመቃተቴ የተነሣ፣ ዝም ባልሁ ጊዜ፣ አጥንቶቼ ተበላሹ፤ በቀንና በሌሊት፣ እጅህ ከብዳብኛለችና፣ ኀይሌም የበጋ ትኵሳት እንደላሰው ነገር፣ ከውስጤ ተሟጠጠ።»

**4. ዳዊት ንስሐ ሲገባና ኃጢአቱን ሲናዘዝ እግዚአብሔር ወዲያውኑ ይቅር አለው።**

መዝ. 32:5። «ኀጢአቴን ለአንተ አስታወቅሁ፤ በደሌንም አልሸሸግሁም፤ ደግሞም «መተላለፌን ለእግዚአብሔር እናዘዛለሁ» አልሁ፤ አንተም የኀጢአቴን በደል፣ ይቅር አልህ።»

**5. የዳዊት የኃጢአቱ ኑዛዜና ይቅርታን ለማግኘት ያደረገው ጩኸት የተከሰተው በእግዚአብሔር ጸጋ ብቻ ነው።**

**6. እግዚአብሔር የተሰበረውንና የተዋረደውን ልብ አይንቅም።**

መዝ. 51:17። «እግዚአብሔር የሚቀበለው መሥዋዕት የተሰበረ



መንፈስ ነው፤ እግዚአብሔር ሆይ፤ አንተ የተሰበረውንና የተዋረደውን ልብ አትንቅም።

**7. የእግዚአብሔር ይቅርታ ምንኛ ታላቅ ነው!**

መዝ. 103:8-12። «እግዚአብሔር መሓሪና ይቅር ባይ፣ ለቍጣ የዘገየ፣ ፍቅሩም የበዛ ነው። እርሱ ሁልጊዜ በደልን አይከታተልም፤ ለዘላለምም አይቈጣም። እንደ ኀጢአታችን አልመለሰልንም፤ እንደ በደላችንም አልከፈለንም። ሰማይ ከምድር ከፍ እንደሚል፣ እንዲሁ ለሚፈሩት ምሕረቱ ታላቅ ናት። ምሥራቅ ከምዕራብ እንደሚርቅ፣ መተላለፋችንን በዚያው መጠን ከእኛ አስወገደ።»

**8. እግዚአብሔር ርኅሩኅና ይቅር ባይ አምላክ ነው።**

መዝ. 86:4-7። «የባሪያህን ነፍስ ደስ አሰኛት፤ ጌታ ሆይ፤ ነፍሴን ወደ አንተ አነሣለሁና። ጌታ ሆይ፤ አንተ ቸርና ይቅር ባይ ነህ፤ ለሚጠሩህ ሁሉ ምሕረትህ ወሰን የለውም። እግዚአብሔር ሆይ፤ ጸሎቴን አድምጥ፤ የልመናዬን ጩኸት ስማ። አንተ ስለምትመልስልኝ በመከራዬ ቀን ወደ አንተ እጣራለሁ። ጌታ ሆይ፤ ከአማልክት መካከል እንደ አንተ ያለ የለም፤ ከአንተም ሥራ ጋር ሚወዳደር ሥራ የለም።»

**9. እግዚአብሔር ኃጢአተኞች እንዲፈልጉት ይጠራቸዋል፤ ንስሐ ሲገቡም ይቅር እንደሚላቸው ቃል ይገባላቸዋል።**

ኢሳ. 55:6-7። «እግዚአብሔር በሚገኝበት ጊዜ ፈልጉት፤ ቀርቦም ሳለ ጥሩት። ክፉ ሰው መንገዱን፣ በደለኛም ሐሳቡን ይተው። ወደ እግዚአብሔር ይመለስ፤ እርሱም ምሕረት ያደርግለታል፤ ወደ አምላካችን ይመለስ፤ ይቅርታው ብዙ ነውና።»

**10. ኢየሱስ የፍቅር ግብዣውን አቅርቦአል።**

ማቴ. 11:28-30። «እናንተ ሸክም የከበዳችሁና የደከማችሁ ሁሉ ወደ እኔ ኑ፤ እኔም ዕረፍት እሰጣችኋለሁ። ቀንበሬን ተሸከሙ፤ ከእኔም ተማሩ፤ እኔ በልቤ የዋህና ትሑት ነኝና፤ ለነፍሳችሁም ዕረፍት ታገኛላችሁ፤ ቀንበሬ ልዝብ ሸክሜም ቀላል ነውና።»

**11. ኢየሱስ የተጸጸተችውን ሴት ይቅር አላት።**

ሉቃ. 7:36-50

ሉቃ. 7:47-50:: «ስለዚህ እልሃለሁ፤ እጅግ ወዳለችና ብዙው ኀጢአቷ ተሰርዮላታል፤ በትንሹ የተሰረየለት ግን የሚወደው በትንሹ ነው:: ኢየሱስም ሴቲቱን፣ «ኀጢአትሽ ተሰርዮልሻል» አላት:: አብረውት በማእድ ተቀምጠው የነበሩ እንግዶችም፣ «ይህ ኀጢአትን እንኳ የሚያስተሰረይ እርሱ ማን ነው?» ብለው በልባቸው አሰቡ:: ኢየሱስም ሴቲቱን፣ «እምነትሽ አድኖሻል፤ በሰላም ሂጂ» አላት::

12. ኢየሱስ ነፍሰ ገዳዩን በመስቀል ላይ ይቅር አለው (ይህም አንድ ሰው በጸጋ ብቻ እንደሚድን የሚያሳይ ምሳሌ ነው)::

ሉቃ. 23:43:: «ኢየሱስም፣ «እውነት እልሃለሁ፤ ዛሬ ከእኔ ጋር በገነት ትሆናለህ» አለው::»

13. ኃጢአተኞች ንስሐ ገብተው በኢየሱስ ሲያምኑ ይቅር ይባላሉ::

ሉቃ. 15:11-32:: (የጠፋው ልጅ ምሳሌ)

14. ኢየሱስ ለይቅርታ እንድንጸልይ ይናገረናል::

ማቴ. 6:12:: «እኛም ደግሞ የበደሉንን ይቅር እንደምንል፣ በደላችንን ይቅር በለን::»

15. እኛ በኢየሱስ በማመናችን ጸድቀናል (ከክስ ነጻ ሆነናል)፣ በእርሱም በኩል ሰላም እናገኛለን::

ሮሜ 3:21-25:: «አሁን ግን ሕግና ነቢያት የመሰከሩለት፣ ከሕግ ውጭ የሆነ፣ የእግዚአብሔር ጽድቅ ተገልጦአል:: ይህ የእግዚአብሔር ጽድቅ ኢየሱስ ክርስቶስን በማመን የሚገኝ ጽድቅ ነው:: ልዩነት የለም፤ ምክንያቱም ሁሉም ኀጢአትን ሠርተዋል፤ የእግዚአብሔርም ክብር ጐድሉአቸዋል፤ በኢየሱስ ክርስቶስ በሆነው ቤዛነት እንዲያው በጸጋው ጸድቀዋል፤ በደሙም በሆነው እምነት፣ እግዚአብሔር የማስተሰሪያ መሥዋዕት አድርጎ አቅርቦታል፤ ይህንም ያደረገው ቀድሞ የተፈጸመውን ኀጢአት ሳይቀጣ በትዕግሥት በማለፍ ጽድቁን ለማሳየት ነው::»



ሮሜ. 5:1:: «እንግዲህ በእምነት ስለ ጸደቅን፣ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል ከእግዚአብሔር ጋር ሰላም አለን::»

ሮሜ 8:1-4:: «ስለዚህ በክርስቶስ ኢየሱስ ያሉት አሁን ኩነኔ የለባቸውም፤ ምክንያቱም የሕይወት መንፈስ ሕግ በክርስቶስ ኢየሱስ ከኀጢአትና ከሞት ሕግ ነጻ አውጥቶአችኋል:: ሕግ ከሥጋ ባሕርይ የተነሣ ደክሞ ሊፈጽም ያልቻለውን፤ እግዚአብሔር የገዛ ልጁን በኀጢአተኛው ሰው አምሳል፣ የኀጢአት እንዲሆን በመላክ ፈጽመው በዚያም ኀጢአትን በሥጋ ኰነነ፤ ይኸውም በሥጋ ሳይሆን በመንፈስ በምንመላለስ በእኛ፣ ሕጉ የሚጠይቀው ጽድቅ ሙሉ በሙሉ እንዲፈጸም ነው::»

16. በፍቅር፣ እኛን ይቀድሰን ዘንድ ኢየሱስ ሞተ፤ እኛ ያለ እንከን ነን::

ኤፌ. 5:25-27:: «ባሎች ሆይ፤ ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያንን እንደ ወደዳትና ራሱንም ስለ እርሷ አሳልፎ እንደ ሰጠ፣ እናንተም ሚስቶቻችሁን ውደዱ፤ በቃሉ አማካይነት በውሃ አጥቦ በማንጻት እንድትቀደስ፣ እንዲሁ ጒድፍ ወይም የፊት መጨማደድ ወይም አንዳች እንከን ሳይገኝባት ቅድስትና ነውር አልባ የሆነች ክብርት ቤተ ክርስቲያን አድርጎ ለራሱ ሊያቀርባት ነው::»

ዕብ. 10:10:: «በዚህ ፈቃድ በኢየሱስ ክርስቶስ ሥጋ አማካይነት ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ በቀረበው መሥዋዕት ተቀድሰናል»

17. የኢየሱስ ክርስቶስ ደም ከኃጢአት ሁሉ ያነጻል::

1ኛ ዮሐ. 1:7:: «ነገር ግን እርሱ በብርሃን እንዳለ፣ እኛም በብርሃን ብንመላለስ እርስ በእርሳችን ኅብረት አለን፤ የልጁም የኢየሱስ ክርስቶስ ደም ከኀጢአት ሁሉ ያነጻናል::»

18. እኛ ኃጢአታችንን በፊቱ ስንናዘዝ እግዚአብሔር በጸጋ ይቅር ይለናል::

1ኛ ዮሐ. 1:9:: «ኀጢአታችንን ብንናዘዝ ኀጢአታችንን ይቅር ሊለን፣ ከዐመፃ ሁሉ ሊያነጻን እርሱ ታማኝና ጻድቅ ነው::»

ምሳ. 28፡13-14። «ኃጢአቱን የሚሰውር አይለማም፤ የሚናዘዝና የሚተወው ግን ምሕረትን ያገኛል። እግዚአብሔርን ዘወትር የሚፈራ ሰው ቡሩክ ነው፤ ልቡን የሚያደነድን ግን መከራ ላይ ይወድቃል።»

19. እግዚአብሔር ሁሉንም ዓይነት ኃጢአተኞች ይቅር ይላል፤ እንዲሁም ያድናል። ምንም ዓይነት ክፉዎች ቢሆኑም እንኳ ይለውጣቸዋል።

1ኛቆሮ. 6፡9-11። «ዐመፀኞች የእግዚአብሔርን መንግሥት እንደማይወርሱ አታውቁምን? በዚህ ነገር አትታለሉ፤ ሴሰኞች፣ ጣዖትን አምላኪዎች፣ አመንዝሮች፣ ወንደቃዎች፣ ግብረ ሰዶማውያን፣ ወይም ሌቦች፣ ስግብግቦች፣ ሰካራሞች፣ ተሳዳቢዎችና ቀማኞች የእግዚአብሔርን መንግሥት አይወርሱም። ከእናንተ አንዳንዶቻችሁ እንደዚህ ነበራችሁ፤ አሁን ግን በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ስምና፣ በአምላካችን መንፈስ ታጥባችኋል፤ ተቀድሳችኋል፤ ጸድቃችኋል።»

20. ዘካርያስ በራእይ፣ እድፋም ልብስ ለብሶ የነበረው ሊቀ ካሕን ልብሱ ተገፎ በነጭ መጐናጸፊያ ሲለወጥ አይቷል።

ዘካ. 3፡1-5። «እርሱም ሊቀ ካሕኑን ኢያሱን በእግዚአብሔር መልአክ ፊት ቆሞ፣ ሰይጣንም ሊከሰው በስተ ቀኙ ቆሞ አሳየኝ። እግዚአብሔርም ሰይጣንን፣ «አንተ ሰይጣን፤ እግዚአብሔር ይገሥጽህ፤ ኢየሩሳሌምን የመረጠ እግዚአብሔር ይገሥጽሕ፤ ይህ ሰው ከእሳት የተነጠቀ ትንታግ አይደለምን?» አለው። ኢያሱም ያደፈ ልብስ ለብሶ በመልአኩ ፊት ቆሞ ነበር። መልአኩም ከፊቱ ቆመው የነበሩትን፣ «ያደፉ ልብሶቹን አውልቁለት» አላቸው። ኢያሱንም፣ «እነሆ፤ ኃጢአትህን ከአንተ አስወግጃለሁ፤ ጥሩ ልብስም አለብስሃለሁ» አለው። እኔም «ንጹሕ ጥምጥም በራሱ ላይ አድርጉለት» አልሁ። የእግዚአብሔርም መልአክ በአጠገቡ ቆሞ እያለ፣ ንጹሕ ጥምጥም በራሱ ላይ አደረጉለት፤ ልብስም አለበሱት።»



21. አመንዝራይቱ ሰማርያዊት በኢየሱስ መዳንን አገኘች፤ የሕይወትን ውኃ አገኘች።

ዮሐ. 4፡4-26።

ዮሐ. 4፡13-14። «ኢየሱስም እንዲህ ሲል መለሰላት፤ «ከዚህ ውሃ የሚጠጣ እንደ ገና ይጠማል፤ እኔ ከምሰጠው ውሃ የሚጠጣ ግን ከቶ አይጠማም፤ እኔ የምሰጠው ውሃ በውስጡ የሚፈልቅ የዘላለም ሕይወት ውኃ ምንጭ ይሆናል።»

22. ኢየሱስን የካደው ጴጥሮስ ይቅር ተበሏል፣ ወደ አገልግሎቱም ተመልሶአል።

ዮሐ. 21፡15-19። (ኢየሱስ ለጴጥሮስ የሞተለትን ክቡር ሕዝብ እንኳን አስረከቦታል።) ኢየሱስም፣ «ጠቦቶቼን መግብ. . . በጎቼን ጠብቅ» አለው።

23. ኢየሱስ የፈሪሳውያንና የቀረጥ ሰብሳቢውን ምሳሌ ተናገረ።

ሉቃ. 18፡9-14። (ትዕቢተኛውና በራሱ ጽድቅ የሚመካው ፈሪሳዊ አልጸደቀም፣ ይቅር አልተባለም። ነገር ግን ራሱን ዝቅ ያደረገው ቀረጥ ሰብሳቢ ጸድቆ እንዲሁም ልቡ በሰላም ተሞልቶ ወደ ቤቱ ተመልሷል።)

ሉቃ. 18፡13-14። «ቀረጥ ሰብሳቢው ግን በርቀት ቆሞ፣ ወደ ሰማይ ቀና ብሎ ማየት እንኳ አልፈለገም፤ ነገር ግን ደረቱን እየደቃ፣ <እግዚአብሔር ሆይ፤ እኔን ኃጢአተኛውን ማረኝ> ይል ነበር። «እላችኋለሁ፤ ከፈሪሳዊው ይልቅ ይኸኛው በእግዚአብሔር ዘንድ እንደ ጻድቅ ተቈጥሮ ወደ ቤቱ ተመለሰ፤ ራሱንም ከፍ ከፍ የሚያደርግ ሁሉ ዝቅ ይላልና፤ ራሱን ዝቅ ዝቅ የሚያደርግ ግን ከፍ ይላል።»

24. የተጨነቁ ኃጢአተኞች ምሕረትን ይጠይቃሉ፣ እግዚአብሔርም በጸጋ ይቅር ይላቸዋል፤ ወደ ራሱ ፍቅርና ሞገስም ያድሰናል። መዝ. 130።

መዝ. 130፡3-4። «እግዚአብሔር ሆይ፤ ኀጢአትን ብትቈጣጠር፣ ጌታ ሆይ፤ ማን ሊቆም ይችላል? ነገር ግን በአንተ ዘንድ ይቅርታ አለ፤ ስለዚህም ልትፈራ ይገባሃል።»

25. አማኞች ከጨለማው ግዛት ድነዋል። ወደ ኢየሱስም ዘላለማዊ መንግሥት ተሸጋግረዋል፣ ለኃጢአታቸውም ሁሉ ይቅርታን አግኝተዋል።

ቈላ. 1:13-14። «እርሱ ከጨለማ ግዛት ታደገን፤ ወደሚወደው ልጁ መንግሥትም አሻገረን፤ በእርሱም መዋጀትን አግኝተናል፤ ይህም የኀጢአት ይቅርታ ነው።»

26. እግዚአብሔር፣ ኃጢአታችንን ሁሉ በፈሰሰው በኢየሱስ ክርስቶስ ደም ይቅር በማለት በጸጋው ወድዶናል፣ መርጦናል።

ኤፌ. 1:3-10።

ኤፌ. 1:7-8። «በእርሱም እንደ እግዚአብሔር ጸጋ ባለ ጠግነት መጠን፣ በደሙ በተደረገ ቤዛነት፣ የኀጢአትን ይቅርታ አገኘን፣ ጸጋውንም በጥበብና በማስተዋል ሁሉ አበዛልን።»

27. የይቅርታ ጸሎት በንስሐ ሊታጀብ ይገባል።

1ኛ ነገ. 8:33-36፣ 46-53 (ሰሎሞን፣ ቤተ መቅደሱ ሲመረቅ ሕዝቡ ንስሐ ገብተው ቢያገለግሉት እግዚአብሔር ይቅር እንዲላቸው ጸልዮአል።)

1ኛ ነገ. 8:33-36። «ሕዝብህ እስራኤል አንተን ከመበደላቸው የተነሣ፤ በጠላቶቻቸው ድል በሚሆኑበት ጊዜ፣ ወደ አንተም ተመልሰው ስምህን ቢጠሩ፣ በዚህም ቤተ መቅደስ ወደ አንተ ቢጸልዩና ልመናቸውን ቢያቀርቡ፣ በሰማይ ሆነህ ስማ፤ የሕዝብህ የእስራኤልን ኀጢአት ይቅር በል፤ ለአባቶቻቸው ወደ ሰጠሃቸውም ምድር መልሰህ አግባቸው። ሕዝቡም አንተን ከመበደላቸው የተነሣ፣ ሰማዩ ተዘግቶ ዝናብ ሳይዘንብ ቢቀር፣ ወደዚህ ስፍራ ቢጸልዩና ስምህን ቢጠሩ፣ ስላስጨነቅሃቸውም ከበደላቸው ቢመለሱ፣ በሰማይ ሆነህ ስማ፤ የባሪያዎችህን የሕዝብህን የእስራኤልን ኀጢአት ይቅር በል፤ የሚሄዱበትን ቀናውን መንገድ አስተምራቸው፤ ርስት አድርገህ ለሕዝብህ ለሰጠሃትም ምድር ዝናብ አውርድ።»

28. ነህምያ አለቀሰና የእግዚአብሔርን ሕዝብ ኃጢአት ተናዘዘ።

ነህ. 1:6-7። «ባሪያህ ስለ አገልጋዮችህ ስለ እስራኤል ሕዝብ



ቀንና ሌሊት በፊትህ የሚጸልየውን ጸሎት ለመስማት ጆሮህ ይንቃ፤ ዐይንህም ይከፈት። እኔንና የአባቴን ቤት ጨምሮ እኛ እስራኤላውያን አንተን በመበደል የሠራነውን ኀጢአት እናዘዛለሁ። በአንተ ላይ እጅግ ክፉ ሥራ ሠርተናል፤ ለባሪያህም ለሙሴ የሰጠኸውን ትእዛዝ፣ ሥርዓትና ሕግ አልጠበቅንም።»

29. እግዚአብሔር ኃጢአታችንን ሁሉ ያስወግዳል፣ በደስታ እንድንዘምርም ይፈልጋል!

ኢሳ. 44:22-23። «መተላለፍህን እንደ ደመና፣ ኀጢአትህን እንደ ማለዳ ጭጋግ ጠርጌ አስወግጃለሁ፣ ተቤዥቼሃለሁና ወደ እኔ ተመለስ።» ሰማያት ሆይ፤ እግዚአብሔር ይህን አድርጎአልና ዘምሩ፤ የምድር ጥልቆች ሆይ፤ በደስታ ጨኹ። እናንት ተራሮች፣ እናንት ደኖችና ዛፎቻችሁ ሁሉ እልል በሉ፤ እግዚአብሔር ያዕቆብን ተቤዥቶአል፣ በእስራኤልም ክብሩን ገልጦአልና።

30. ዳዊት፣ እግዚአብሔር የወጣትነት ዘመኑን ኃጢአት ይቅር እንዲል ጸለየ።

መዝ. 25:7። «የልጅነቴን ኀጢአት፣ መተላለፌንም አታስብብኝ፤ እግዚአብሔር ሆይ፤ እንደ ቸርነትህ ብዛት፣ እንደ ምሕረትህም መጠን አስበኝ።

31. በኢየሱስ በኩል በሆነው እምነት የኃጢአት ይቅርታ እንዳለን ነቢያት ሁሉ ይመሰክራሉ።

ሐዋ. 10:43። «በእርሱ የሚያምን ሁሉ በስሙ የኀጢአትን ስርየት እንደሚቀበል ነቢያት ሁሉ ይመሰክሩለታል።»

32. አንድ ሰው የሚድንበትና የኃጢአቱን ይቅርታ የሚያገኝበት ብቸኛው መንገድ ኢየሱስ ነው።

ሐዋ. 4:12። «ድነት በሌላ በማንም አይገኝም፤ እንድንበት ዘንድ ለሰዎች የተሰጠ ከዚህም ስም በስተቀር ሌላ ስም ከሰማይ በታች የለምና።»

1ኛ ጢሞ. 2:5-6። «አንድ እግዚአብሔር አለና፤ ደግሞም በእግዚአብሔርና በሰዎች መካከል አንድ አስታራቂ አለ፤ እርሱም

ሰው የሆነው ክርስቶስ ኢየሱስ ነው፤ ራሱንም ለሰዎች ሁሉ ቤዛ አድርጎ ሰጠ፤ ይህም በትክክለኛው ጊዜ ተመስክሮለታል።»

33. ደኅንነት፣ የኃጢአት ይቅርታ፣ የሚገኘው በጸጋና በኢየሱስ ክርስቶስ በማመን ብቻ ነው።

ኤፌ. 2:8-9። «በእምነት፣ በጸጋ ድናችኋልና፤ ይህም የእግዚአብሔር ስጦታ ነው እንጂ ከእናንተ አይደለም፤ ማንም እንዳይመካ በሥራ አይደለም፤»

34. ሰዎች ንስሐ ሲገቡና በእምነት ጌታን ሲፈልጉ፣ እርሱ በጸጋ ኃጢአታቸውን ይቅር ይላል፣ መተላለፋቸውንም እንዳለ ወደ ባሕር ጥልቅ ይጥላል፣ ሁለተኛም አያስታውሰውም።

ሚክ. 7:18-19። «የርስቱን ትሩፍ፣ ኀጢአት ይቅር የሚል፣ የሚምር እንደ አንተ ያለ አምላክ ማነው? ለዘላለም አትቆጣም፤ ነገር ግን ምሕረት በማድረግ ደስ ይልሃል። ተመልሰህ ትራራልናለህ፤ ኀጢአታችንን በእግርህ ትረግጣለህ፤ በደላችንንም ሁሉ ወደ ጥልቁ ባሕር ትጥላለህ።»

35. እግዚአብሔር በክርስቶስ ሆኖ እኛን ከራሱ ጋር ያስታርቃል። ኃጢአታችንንም አይቆጥርብንም።

2ኛ ቆሮ. 5:18-19። «ይህ ሁሉ ከእግዚአብሔር ነው፤ እርሱ በክርስቶስ አማካይነት ከራሱ ጋር አስታረቀን፤ የማስታረቅንም አገልግሎት ሰጠን፤ እግዚአብሔር በክርስቶስ ዓለምን ከራሱ ጋር ሊያስታርቅ የሰዎችን በደል አይቈጥርባቸውም ነበር፤ ለእኛም ደግሞ የማስታረቅ ቃል ሰጠን።»



# ሌሎችን ይቅር ማለት

1. የበደሉንን ይቅር ማለት አለብን።

ማቴ. 6:12። «እኛም ደግሞ የበደሉንን ይቅር እደምንል፣ በደላችንን ይቅር በለን።»

2. ሌሎችን ይቅር ማለት እጅግ አስፈላጊ ነገር ነው።

ማቴ. 6:14-15። «እናንተ የበደሏችሁን ይቅር ብትሉ የሰማዩ አባታችሁ ደግሞ እናንተን ይቅር ይላችኋል። ነገር ግን የሰዎችን ኀጢአት ይቅር የማትሉ ከሆነ፣ አባታችሁም ኀጢአታችሁን ይቅር አይልላችሁም።»

3. ኢየሱስ በተደጋጋሚ ይቅር ማለት እንዳለብን ተናገረ።

ማቴ. 18:21-22። «በዚህ ጊዜ ጴጥሮስ ወደ ኢየሱስ ቀርቦ፣ «ጌታ ሆይ፤ ወንድሜ ቢበድለኝ ስንት ጊዜ ይቅር ልበለው? እስከ ሰባት ጊዜ ነውን?» አለው? ኢየሱስም «እስከ ሰባ ጊዜ ሰባት እንጂ እስከ ሰባት ጊዜ ብቻ አልልህም» አለው።»

ሉቃ. 17:3-4። «ስለዚህ ለራሳችሁ ተጠንቀቁ። ወንድምህ ቢበድል ገሥጸው፤ ቢጸጸት ይቅር በለው። በቀን ሰባት ጊዜ ቢበድልህና ሰባት ጊዜ፣ «ተጸጽቻለሁ» እያለ ወደ አንተ ቢመለስ ይቅር በለው።»

4. ይቅርታን የነፈገው ባሪያ ምሳሌ ይቅር አለማለት ምን ያህል የከፋ ኃጢአት እንደሆነ ያሳያል፤ እግዚአብሔር በዚህ ኃጢአት ላይ ፍርዱን ይልካል።

ማቴ. 18:23-25።

5. መራርነትንና ቁጣን አስወግዱ፣ እግዚአብሔር ይቅር እንዳላችሁ ይቅር ተባባሉ።

ኤፌ. 4:31-32። «መራርነትን ሁሉ፣ ቍጣና ንዴትን፣ ጭቅጭቅና ስድብን ከማንኛውም ክፋት ጋር ከእናንተ ዘንድ አስወግዱ። እግዚአብሔር በክርስቶስ ይቅር እንዳላችሁ፤ እናንተም ይቅር ተባባሉ፤ እርስ በርሳችሁ ቸሮችና ርኅሮኆች ሁኑ።»

6. እግዚአብሔርን የምትመስሉ ሁኑ።

ኤፌ. 5:1-2:: «እንግዲህ እንደ ተወደዱ ልጆች እግዚአብሔርን ምሰሉ፤ ክርስቶስ እንደ ወደደን ራሱንም ስለ እኛ መልካም መዐዛ ያለው መባና መሥዋዕት አድርጎ ለእግዚአብሔር እንደሰጠ እናንተም በፍቅር ተመላለሱ።»

7. የጠፋው ልጅ አባት ይቅር አለው ከዚያ በፊትም ምንም ዓይነት ኃጢአት ሠርቶ እደማያውቅ አድርጎ ተቀበለው። ይህ አባት እግዚአብሔርን ይወክላል። በዚህም ኢየሱስ ንስሐ የሚገባን ኃጢአተኛ እግዚአብሔር እንዴት አድርጎ እንደሚቀበለው ገለጸ።

ሉቃ. 15:20-24።

8. ኢየሱስ ሌሎችን ይቅር እንድንል አዘዘን።

ማር. 11:25። «እንዲሁም ለጸሎት በምትቆሙበት ጊዜ፣ የሰማዩ አባታችሁ ኀጢአታችሁን ይቅር እንዲልላችሁ፣ እናንተም በሰው ላይ ያላችሁን ሁሉ ይቅር በሉ።»

9. ፍቅር በደልን አይቆጥርም።

1ኛ ቆሮ. 13:5። «ፍቅር በደልን አይቈጥርም።»

10. ፍቅር የኃጢአትን ብዛት ይሸፍናል (ያልፋል)።

1ኛ ጴጥ. 4:8። «ፍቅር ብዙ ኀጢአትን ይሸፍናልና ከሁሉ በላይ እርስ በርሳችሁ ከልብ ተዋደዱ።

11. በበደል ውስጥ የወደቀውን ሰው በገርነት አድሱት።

ገላት. 6:1። «ወንድሞች ሆይ፤ አንድ ሰው በኀጢአት ውስጥ ገብቶ ቢገኝ፣ መንፈሳውያን የሆናችሁ እናንተ በገርነት ልትመልሱት ይገባል።»

12. ጳውሎስ የበደለንን ሰው ይቅር እንድንለውና እንድንመልሰው ይነግረናል።

2ኛ ቆሮ. 2:5-11።

13. ንስሐ የሚገባን ኃጢአተኛ ይቅር በሉ፣ ፍቅራችሁንም አጽኑለት።



2ኛ ቆሮ. 2:7-8። «ደግሞም ከልብ በላይ አዝኖ ተስፋ እንዳይቈርጥ፣ ይቅር ልትሉትና ልታጽናኑት ይገባችኋል። ስለዚህ አሁንም የምትወዱት መሆናችሁን እንድትገልጹለት እለምናችኋለሁ።»

14. ሌሎችን ይቅር ስንል፣ ሰይጣንን እናሞኘዋለን።

2ኛ ቆሮ. 2:10-11። «እናንተ ይቅር የምትሉትን ሰው እኔም ይቅር እለዋለሁ፤ በእርግጥ ይቅር የምለው ነገር ካለ፣ በክርስቶስ ፊት ይቅር የምለው ስለ እናንተ ስል ነው። ይህንንም የምናደርገው ሰይጣን መግቢያ ቀዳዳ እንዳያገኝ ነው፤ የእርሱን ዕቅድ አንስተውምና።»

15. ዮሴፍ ወንድሞቹ ወደ ባርነት በመሸጥ ስለ ፈጸሙበት በደል ይቅር አላቸው፣ እንዲሁም በመልካም ተናገራቸው።

ዘፍ. 45።

ዘፍ. 45:4-5። «ዮሴፍም ወንድሞቹን፣ «እስቲ ወደ እኔ ቀረብ በሉ» አላቸው፤ ወደ እርሱም በቀረቡ ጊዜ እንዲህ አለ፤ «ወደ ግብፅ የሸጣችሁኝ ወንድማችሁ እኔ ዮሴፍ ነኝ፤ አሁንም በመሸጣችሁ አትቈጩ፤ በራሳችሁም ዐትዘኑ፤ ምክንያቱም እግዚአብሔር (ኤሎሂም) ሕይወትን ለማዳን ሲል ከእናንተ አስቀድሞ እኔን ወደዚህ ልኮኛል።»

ዘፍ. 45:9-11። «አሁንም በፍጥነት ወደ አባቴ ተመልሳችሁ እንዲህ በሉት፤ ልጅህ ዮሴፍ እንዲህ ይላል፤ እግዚአብሔር (ኤሎሂም) የመላው ግብፅ ጌታ አድርጎኛል፤ ስለዚህ ሳትዘገይ ወደ እኔ ና።»

ዘፍ. 50:15-21።

ዘፍ. 50:19-21። «ዮሴፍ ግን እንዲህ አላቸው፤ «አትፍሩ፤ እኔን በእግዚአብሔር (ኤሎሂም) ቦታ ማን አስቀመጠኝ? እናንተ እኔን ለመጕዳት አስባችሁ አድርጋችሁት ነበር፤ እግዚአብሔር (ኤሎሂም) ግን ዛሬ እንደሚታየው ሁሉ የብዙዎችን ሕይወት ለማዳን ለበጎ ነገር አዋለው። አሁንም ቢሆን አትፍሩ፤ ለእናንተና ለልጆቻችሁ የሚያስፈልጋችሁን ሁሉ አደርግላችኋለሁ» በማለት አረጋግጦ፣ በደግ ቃል አናገራቸው።»